የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ ውጤታማ የሆነው ማህበር

ገጽ 10

የኮሪደር ልማቱንም በግዙፍ ፕሮጀክቶች የግንባታ ፍጥነት

ገጽ 17

በቦኮሃራም የታገተችው ናይጄሪያዊት ተማሪ ከ10 ዓመት በኋላ ሦስት ልጆችን ወልዳ ነፃ ወጣች

ገጽ 12


# አዲስ ዘመን

እፎይ

83ኛ ዓመት ቁጥር 222 ሚያዝያ 12 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












## በንግድ ሥርዓቱ የውጭ ባለሀብቶችን ማሳተፍ ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

**ፋንታነሽ ክንዴ**

**ዜና ትንታኔ**

በኢንቨስትመንት ደምብ 474/2012 ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ተከልለው የቆዩት የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላና የችርቻሮ የንግድ ሥራ ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆኑ ተደርጓል። ዘርፎቹ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በብዛት ለማፍራት፤ ከዓለም-አቀፉ የንግድ ትስስር ሥርዓት ጋር ይበልጥ እንዲተዋወቁ ለማስቻል ዝግ ተደርገው ቆይተዋል፡፡

በተጨማሪም የሀገር ውስጥ ነጋዴዎች እሴትን ወደሚጨምሩ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሸጋገሩ በማድረግ በሀገር ውስጥ አቅሞች ላይ የተመሠረተ ዘላቂ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት ያለመ ነበር፡፡

በንግድ ሥርዓቱ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “የአፍሪካ ቀንድን የተረጋጋ ለማድረግ ከሀገራዊ ወሰን የዘለለ የጋራ ርምጃ ያስፈልጋል”

- አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ

**በአዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ ቀንድ ቀጣናን የበለጠ አስተማማኝና የተረጋጋ ለማድረግ ከሀገራዊ ወሰን የዘለለ የጋራ ርምጃ እንደሚያስፈልግ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ተናገሩ፡፡ ትኩረቱን በአፍሪካ ቀንድ ላይ ያደረገ ውይይት ትናንት በአዲስ አበባ ተካሂዷል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምሥጋኑ አርጋ በዚሁ ወቅት ባደረጉት ንግግር፤ በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና የሚስተዋሉ የፀጥታ ችግሮችን ለመቅረፍ መሰባሰብና ገንቢ ውይይት ማድረግ እንደሚጠበቅ ገልጸዋል፡፡ የጋራ ጥበብን በመጠቀም ለበለጠ አስተማማኝ፣ የተረጋጋና የተቀናጀ የአፍሪካ ቀንድ በጋራ መሥራት እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያለውን የዕድገት ሁኔታ የሚገዳደሩ ችግሮችን ለመቅረፍ መነጋገር አስፈላጊ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ቀጣናው

የአፍሪካ ቀንድ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ደረጀ ድጉማ (ዶ/ር)

## በኢትዮጵያ 55 ሚሊዮን ዜጎች የጤና መድኅን ተጠቃሚ ሆነዋል

- አገልግሎቱ በአንድ ሺህ 22 ወረዳዎች ተዳርሷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዳማ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ 55 ሚሊዮን ዜጎችን የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የጤና ሚኒስትር ዴኤታና የጤና መድኅን አገልግሎት ምክትል ሰብሳቢ ደረጀ ድጉማ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

በኢትዮጵያ 55 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## “ከተማዋ ባልተገራ የልማት ሥርዓት ውስጥ በማለፏ ስተለያዩ ጉዳቶች ተዳርጋለች”

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

ገጽ 4




# በሌማት ትሩፋት ከሰባት ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት እና ከአራት ቢሊዮን በላይ የእንቁላል ምርት ተገኘ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት በሌማት ትሩፋት መርሐግብር ከሰባት ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት እና ከአራት ቢሊዮን በላይ የእንቁላል ምርት መገኘቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። 564 ሺህ ቶን ቀይ ሥጋና 127 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋ ምርት መገኘቱም ተመላክቷል።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አማካሪ ዮሐንስ ግርማ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብር የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በመጨመር የቤተሰብ ብሎም በሀገር ደረጃ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል፡፡

በዚህም በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ሰባት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ሊትር ወተት፣ 564 ሺህ ቶን ሥጋ፣ 127 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋ፣ 191 ሺህ ቶን ማር፣ 111 ሺህ ቶን ዓሣ እና አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን የእንቁላል ምርት ተገኝቷል ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለጻ፣ የሌማት ትሩፋት ዋና ዓላማ በሀገሪቱ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በቤተሰብ ብሎም በሀገር ደረጃ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥና የአመጋገብ ሥርዓትን ማሻሻል ነው። በዚህም የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያ፣ ዘመናዊ የንብ ቀፎ፣ የአንድ ቀን የዶሮ ጫጩት፣ የዓሳ ጫጩት እና ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ መደረጉን አስታውቀዋል።

የወተት ላም ዝርያ ማሻሻል በሌማት ትሩፋት ፕሮግራም በተለየ ትኩረት ከሚሠሩ ተግባራት መካከል አንዱ ነው ያሉት አማካሪው፤ የተሻሻሉ የእንስሳት



ዝርያዎችን የማቅረብ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ብቻ ከአንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ላሞችን በማዳቀል የወተት ምርትን ማሳደግ ተችሏል ብለዋል።

የዓሣ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በኩሬ፣ በሐይቅና ግድቦች ላይ ከአምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን በላይ የዓሳ ጫጩት ስርጭት መከናወኑንም አስረድተዋል፡፡

ከአንድ ሺህ 100 በላይ የንብ ቀፎዎችን ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት የማር ምርትን መጨመር መቻሉን ገልጸው፤ የወተት፣ የዶሮ፣ የዓሣና የማር መንደሮችን በመመስረት ወጣቶች፣ አርሶና አርብቶ አደሩን ተጠቃሚ የማድረግና የገበያ ትስስር እየተፈጠረ ነው ብለዋል።

የሌማት ትሩፋት የሥነ-ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ እና ገበያውን ከማረጋጋት ባሻገር የወጪ ንግድ ገቢን ለማሳደግ፣ ከውጭ የሚገባ ምርትን በሀገር ውስጥ ለመተካት እና የሥራ ዕድልን በመፍጠር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ጉልህ አስተዋፅዖ አለው ብለዋል።

ሁሉም ክልሎች የሌማት ትሩፋትን በተመሳሳይ ሁኔታ አለመተግባራቸው፣ የገበያ ትስስር የመኖ አቅርቦትና የግብዓት እጥረት ለመርሐግብሩ ተግዳሮት መሆናቸውን ገልጸዋል።

የሌማት ትሩፋት አርሶ አደሩን፣ አርብቶ አደሩን እና ሸማቹን የሚያገናኝ ድልድይ ሲሆን፤ በቀጣይ በወተት፣ በዶሮ፣ በዓሣና የማር መንደሮችን ወጣቶች፣ አርሶና አርብቶ አደሩን በማሳተፍ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ምርትን በጥራትና በብዛት አምርቶ ከምግብ ዋስትናው የሚተርፈውን ለገበያ አቅርቦ ተጠቃሚ መሆን እንዲችል በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያ፣ ዘመናዊ የንብ ቀፎ፣ የአንድ ቀን የዶሮ ጫጩት፣ የዓሣ ጫጩት፣ ቴክኖሎጂና የግብዓት አቅርቦትን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉም ጨምረው ገልጸዋል።

# ስምምነቱ ከውጭ ለሚመጡ ቱሪስቶች ቀላል የክፍያ አማራጭን ይፈጥራል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ራይድ የትራንስፖርት ድርጅትና ዓለም አቀፍ የዲጂታል ክፍያ ተቋም ቪዛ የፈጸሙት ስምምነት ከውጭ ለሚመጡ ቱሪስቶች ቀላል የትራንስፖርት የክፍያ አማራጭን የሚፈጥር መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ራይድ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅራቢ ድርጅት እና ዓለም አቀፍ የዲጂታል ክፍያ ተቋም ቪዛ የትራንስፖርት ክፍያን በራይድ መተግበሪያ አማካኝነት መፈጸም የሚያስችለውን ስምምነት ትናንትና አድርገዋል።

በስምምነቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ይሽሩን አለማየሁ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሦስተኛ የዲፕሎማቲክ መቀመጫ እንደመሆኗ በርካታ የውጭ ሀገር ዜጎችና ቱሪስቶች ይጎበኟታል ፡፡



**ይሽሩን ዓለማየሁ (ዶ/ር)**

ይሁን እንጂ ለቱሪስቶች የሚመጥን የክፍያ ሥርዓት ባለመስፋፋቱ ጎብኚዎች የተሳካ ቆይታ እንዲኖራቸው ለነሱ የሚመች የክፍያ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ላይ ከተቀመጡ ግቦች መካከል የዲጂታል ክፍያ ሥርዓትን ማዘመን አንዱ መሆኑ የገለጹት ይሽሩን (ዶ/ር)፤ ራይድና ቪዛ የፈጸሙት ስምምነት ለጎብኚዎች፣ በኢትዮጵያ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ዜጎች እንዲሁም የዲያስፖራው ማኅበረሰብ አባላት ፈጣን የክፍያ አገልግሎትን ለማቅረብ እንደሚረዳ አመላክተዋል።

ስምምነቱ የዲጂታል ክፍያን በማሳለጥ በዘርፉ ያለውን ችግር በተወሰነ የሚያቃልል መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የራይድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ ሳምራዊት ፍቅሩ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ራይድ አስተማማኝና ቀልጣፋ የክፍያ አማራጭ ለመስጠት ከቪዛ ጋር ያደረገው ስምምነት መንገደኞች ስለ ጥሬ ገንዘብና ምንዛሪ ሳይጨነቁ የትራንስፖርት ክፍያቸውን መፈጸም ያስችላቸዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ቱሪስቶች ለትራንስፖርት የሚከፍሉት በኢትዮጵያ ምንዛሪ የነበረ ሲሆን ይህ ስምምነት ግን የቪዛ አካውንታቸውን ወደ አሽከርካሪው በማስገባት ብቻ የአገልግሎት ክፍያቸውን ከአካውንቱ ላይ ተቀናሽ የሚያደርግ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ስምምነቱ አገልግሎቱን ከማዘመን በተጨማሪም ሀገሪቷ የውጭ ምንዛሪ እንድታገኝ አስተዋፅዖ ያደርጋል ሲሉ አስረድተዋል። በኢትዮጵያ የቪዛ ክፍያ ተቋም ዳይሬክተር ያሬድ እንዳለ በበኩላቸው፤ ቪዛ በዓለም ዙሪያ ከ200 በላይ ሀገራት የአገልግሎት ተጠቃሚዎች እንዳሉት ገልጸው፤ ስምምነቱ አስተማማኝ የክፍያ ሥርዓትን በማቅረብ በዓለም አቀፍ ጎብኚዎች ዘንድ የኢትዮጵያ የጉዞና የቱሪዝም ዘርፍን ይደግፋል ብለዋል፡፡

# ኢትዮጵያን የአፍሪካ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተምሳሌት ለማድረግ እየተሠራ ነው



**አቶ መላኩ አለበል**

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በ2022 ኢትዮጵያን በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በተሻሻለው አምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ዙሪያ ከፌዴራል ተቋማት ሥራ ኃላፊዎች፣ ከአምራች ኢንዱስትሪ የዘርፍ ማኅበራት አመራሮችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የግንዛቤ ማስጨበጫ የውይይት መድረክ ትናንት ተካሂዷል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ በ2022 ኢትዮጵያን የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት የሚያደርጉ እቅዶች ተግባራዊ እየተደረጉ ነው፡፡

በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የማድረግ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ በ2022 በተለይ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ኢትዮጵያን የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት የሚያደርጉ እቅዶች ተግባራዊ እየተደረጉ ነው ብለዋል፡፡

ሀገራዊ እቅዶችን ለማሳካት ፖሊሲዎችን፣ አሠራሮችን፣ መሠረተ ልማቶችን፣ የሰው ኃይሉን ማሻሻል እንደሚጠይቅ ጠቅሰው፤ የአምራች ዘርፉን ሊመራ የሚችል ወጥና ሁሉን አቀፍ ፖሊሲ በማውጣት ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የፖሊሲው ይዘት ገበያ መር፣ በግሉ ዘርፍ የሚመራና የመንግሥትን ሚና በግልፅ ያመላከተ መሆኑን በመግለጽ፤ የኢንዱስትሪ ክላስተር፣ ለወጪና ተኪ ምርት የተመጣጠነ ትኩረት የሰጠ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የፖሊሲው ዓላማ የምርት ልማትና ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ፣ የሰው ኃብት ልማትና አስተዳደር ማሳደግ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ፣ ፋይናንስ አቅርቦትና ተደራሽነትን ጨምሮ፣ ማክሮ ኢኮኖሚና የቢዝነስ ሥነ- ምሕዳር ማሳደግ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በዘርፉ በኢንዱስትሪ ባሕልና በሥራ አመራር ክህሎት የዳበረ የሰው ኃይል ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ በፋይናንስ አቅርቦትና ተደራሽነት የብድር አቅርቦት፣ የውጪ ምንዛሪ፣ የመድን ሽፋንና ሌሎች የፋይናንስ ምንጮችን ለመጠቀም ትኩረት መደረጉን አመላክተዋል።

ፖሊሲው የኢንዱስትሪ ክላስተር አሠራርን በመከተል የግብዓት ምርት ልማት ትስስርን የሚደግፍ መሆኑን ገልጸው፤ ለወጪ ንግድና ለተኪ ምርት ልማት እንዲሁም ለምርት ጥራት ትኩረት እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡

ማክሮ ኢኮኖሚና የቢዝነስ ሥነ-ምሕዳርን መነሻ በማድረግ የተረጋጋና ተገማች የማክሮ ኢኮኖሚ ሥርዓት መፍጠር እንደሚገባ በመግለጽ፤ ፖሊሲው አስቻይ የቢዝነስ ሥነ- ምሕዳር መፍጠር የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል።

የአምራች ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ የአሠራር ማሻሻያዎችን ማየት ያስፈልጋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የዘርፉን ልማት ለማረጋገጥ የሁሉንም ተቋማት ርብርብና ድጋፍ ይጠይቃል ብለዋል።

በሀገሪቱ በአሁኑ ጊዜ በሁሉም ዘርፎች ተስፋ ሰጪ ተግባራት እየተከናወኑ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ የዘርፉን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል አሠራርና አደረጃጀት መፈጠሩን ገልጸዋል።

በመድረኩ ላይ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሀሰን መሐመድን ጨምሮ የአምራች ኢንዱስትሪው ማኅበራት አመራሮችና ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል።

# የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በማበራከት የአየር ብክለትን የመከላከል ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**


ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተጀመሩ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በማበራከት የአየር ብክለትን የመከላከል ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ።

ከንቲባዋ ከተማ አስተዳደሩ 150 የኤሌክትሪክ ሚኒ ባስ ተሽከርካሪዎችን በስሩ ላሉ መሥሪያ ቤቶች ባስተላለፈበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ከተማ አስተዳደሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለስድስት ወራት የሚቆየውን የአየር ብክለት የመከላከል ንቅናቄ ይፋ ያደረገ ሲሆን ይህንን ንቅናቄ ወጤታማ ለማድረግ ከሚሠሩት ቀዳሚ ተግባራት መካከል በአሮጌ ተሽከርካሪዎች አማካኝነት የሚመጣውን የአየር ብክለት መከላከል አንዱ ነው። ለዚህም በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች፤ ሞተር ሳይክልና ብስክሌቶችን በስፋት መጠቀም ይጠበቃል።

ይህንንም ከግምት በማስገባት በከተማ አስተዳደሩ ስር ላሉ መሥሪያ ቤቶች በዋናነትም ለወረዳዎች 150 በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ገዝተን አስረክበናል ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ በዚህ ቁጥር ደረጃ በአንድ ግዜ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ወደ ሥራ ሲገቡ እንደ አዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገርም የመጀመሪያ ነው ብለዋል።

እነዚህ ተሽከርካሪዎች የአካባቢ ብክለትን ከመከላከል ባለፈም ወጪን በመቀነስ ረገድም የሚኖራቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመው፤ ከተማ አስተዳደሩ በሚያካሄደው የኮሪደር ልማት የኤሌክትሪክ ሞተር ሳይክልና ብስክሌቶችን በስፋት ለመጠቀም እንዲቻል ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ መሥሪያ ቤቶች በተለይም በወረዳ ደረጃ ላሉት ተቋማት ትኩረት በተገቢው ሁኔታ ባለመሰጠቱ ምክንያት የተለያዩ ግብዓቶችን እጥረት እንዳለባቸው የጠቆሙት ከንቲባዋ፣ በዚህም የተነሳ የሕዝብ አገልግሎት ሲበደልና ሲጓተት ነበር ብለዋል።

እነዚህ ሚኒ ባሶች ለአገልግሎት መቅረባቸው ወረዳዎችን ብቁ በማድረግ ቀልጣፋና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት ለሕዝቡ ተደራሽ ለማድረግ ትልቅ አቅም እንደሚሆናቸው የጠቆሙት ከንቲባ አዳነች፣ የወረዳ ሠራተኞች ይህንን በመገንዘብ ተገቢውን ቀልጣፋ አገልግሎት ለሕዝቡ ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

ከንቲባ አዳነች እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማዋን የትራንስፖርት አገልግሎት ለማሳለጥና አቅርቦቱን ተደራሽ ለማድረግ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። ለዚህም ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ያለው በአንድ በኩል አገልግሎቱን ማዘመን ሲሆን በሌላ በኩል አቅርቦቱን መጨመር ነው። በዚህ ረገድ ባለፉት ሦስት ዓመታት ከ377 በላይ ደረጃቸውን የጠበቁ እና ዘመኑ የሚጠይቀው ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው አውቶብሶችን በመግዛት ለማኅበረሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል።



# ባለሥልጣኑ የደምብ መተላለፎችን ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ ነው

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ደምብ ማስከበር ባለሥልጣን የከተማይቱ ደምብ መተላለፎች እንዲቀንሱ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እንደሚሠራ አስታወቀ፡፡

ባለሥልጣኑ ከአዲስ አበባ ፅዳት አስተዳደር እና አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ ጋር በመተባበር ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ እንደገለጹት፤ ቆሻሻ በየቦታው የሚጥሉ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ አሳስበው ባለሥልጣኑ ደምቡን በሚጥሱ አካላት ላይ ሕጋዊ ርምጃ እንደሚወስድ ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ደምብ ማስከበር ባለሥልጣን ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ አበባ እሸቴ በዚሁ ወቅት ባቀረቡት የመወያያ ሰነድ በአዋጅ ቁጥር 150/2015 ዓ/ም ለደምብ መተላለፎች የወጡ የቅጣት ሰንጠረዦች ላይ በዝርዝር በመወያየት፤ ሚዲያዎች ለኅብረተሰቡ ተገቢውን የግንዛቤ መረጃ እንዲሰጡ ይደረጋል ብለዋል።

ከተጠቀሱት የቅጣት ዓይነቶች መካከል፤ በሕገ ወጥ መንገድ የፍሳሽ እና የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ፣ አዋኪ ድርጊት እና መሰል ተግባራትን መፈፀም፣ ሕገ ወጥ የውጭ ማስታወቂያ ማሰራጨት ተጠቃሽ መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡

በተለይ የሚበሰብሱ እና ደረቅ ቆሻሻዎችን ለይቶ በአግባቡ ማስወገድ ሲገባ ይህን የማያደርግ አካል በደምብ መተላለፍ እንደሚጠየቅ መድረኩ ላይ በቀረበው ሰነድ ተገልጿል፡፡

በመድረኩ ላይ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የተገኙ ሲሆን፤ የክፍለ ከተማ የፅዳት አስተዳደር ኃላፊዎች፣ አርቲስቶች፣ የፅዳት አምባሳደሮች በቀረበው የመወያያ ሰነድ ላይ ሰፋ ያለ ሀሳብ ሰጥተውበታል፡፡

ከተነሱት ሀሳቦች መካከል የደምብ ማስከበር ሥራን ተግባራዊ ለማድረግ ኅብረተሰቡ በሚዲያዎች በኩል በቂ ግንዛቤ ሊሰጠው እንደሚገባ እና ይህን ተላልፎ ሆን ብሎ በቸልተኝነት ደምብ ለማያከብር አካል ቅጣት ተገቢ እንደሆነ ተነስቷል፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ ሰው እና ተቋም ደምብ የማስከበር ግዴታ እንዳለበት በመረዳት በተለይ ቆሻሻን በተመለከተ ለረጅም ጊዜ ቢሠራበትም መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ያልተቻለበትን ምክንያት በማወቅ፤ ግንዛቤ ከመስጠት ባለፈ ባለሥልጣኑ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ተጠያቂነት እንዲኖር ይሰራል ብለዋል፡፡

የውይይት መድረኩን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደምብ ማስከበር ባለሥልጣን፣ የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር እና አዲስ ሚዲያ ኔትወርክ በጋራ አዘጋጅተውታል፡፡

# ስዊድን ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ትብብር አጠናክራ እንደምትቀጥል አስታወቀች

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ስዊድን ከረጅም ዘመናት ወዳጇ ኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዘርፈ ብዙ ትብብር አጠናክራ እንደምትቀጥል አስታወቀች።

የሀገራቱን የ70 ዓመታት የሁለትዮሽ ግንኙነት የሚዘክር "የኢትዮጵያና ስዊድን አንድነት በአሁነኛው ዘመን" በሚል መሪ ሃሳብ የፓናል ውይይት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥናትና ምርምር ተቋም ውስጥ ተካሂዷል፡፡

በውይይቱ የተገኙት በኢትዮጵያ የስዊድን አምባሳደር ሐንስ ሄንሪክ እንደተናገሩት፤ የኢትዮ-ስዊድን ሁለትዮሽ ግንኙነት 70 ዓመታትን ተሻግሯል፡፡ በነዚህ ሰባ ዓመታት ውስጥም ሀገራቱ እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት እያሳደጉ መጥተዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ ስዊድንና ኢትዮጵያ በነበራቸው የሁለትዮሽ ግንኙነት በተለያዩ ዘርፎች ትብብር ያደርጋሉ፡፡ ግብርና፣ ጤና፣ ንግድና ኢንቨስትመንትም ዋንኞቹ ናቸው፡፡ ሀገራቱ በተለያዩ ዘርፎች ውስጥ ያላቸው ትብብር በቀጣይም ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

አምባሳደር ሀንስ እንዳመለከቱት፤ ስዊድን ከኢትዮጵያ ጋር በነበራት የረጅም ዘመን ግንኙነት በተለይም ከ1960 ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ከስድስት ሺህ በላይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ለኢትዮጵያ ገንብታለች፡፡

የሀገራቱ የትብብር መንገድ ዘርፈ ብዙ መሆኑን ጠቁመው፤ በዋነኛነት በትምህርት ዘርፉ ሰፊ ግንኙነት እንዳላቸው አመላክተዋል።

ስዊድን ለኢትዮጵያውያን እስከ ሦስተኛ ዲግሪ የሚደርሱ የትምህርት ዕድሎችን በማመቻቸት በርካታ ዜጎች የዕድሉ ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉም አምባሳደሩ አንስተዋል።

በቀጣይም መንግሥታቸው በስፋት የትምህርት ዕድሎችን በማመቻቸት እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

በኢትዮጵያ በተለያዩ መስኮች የተሠማሩ ከ30 በላይ የስዊድን ድርጅቶች መኖራቸውን አምባሳደሩ አመላክተው፤ ተቋማቱ የሀገራቱን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ዘርፈ ብዙ ግንኙነቶች በማጠናከር ረገድ አወንታዊ አስተዋፅዖ እየተወጡ መሆኑን ጠቁመዋል።


**አምባሳደር ሐንስ ሄንሪክ**

የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት በመልካም መሠረት ላይ የተጣለ በመሆኑ የወደፊት ግንኙነታቸውም መልካም እንደሚሆን ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያና ስዊድን ባላቸው የረጅም ዘመን ግንኙነት ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶች ቢኖሩም የገጠሙ መሰናክሎች ወዳጅነታቸውን ሳያግዱ ለዛሬ መብቃት መቻላቸው በሀገራቱ መካከል ላለው ግንኙነት ጥንካሬ ማሳያ መሆኑንም አምባሳደር ሀንስ ገልጸዋል።

# “ከተማዋ ባልተገራ የልማት ሥርዓት ውስጥ በማለፏ ለተለያዩ ጉዳቶች ተዳርጋለች”

**- ከንቲባ አዳነች አቤቤ**

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባ ከተማ ባለፉት ጊዜያት ባልተገራ የከተማ ልማት ሥርዓት ውስጥ በማለፏ ለተለያዩ ጉዳቶች ተዳርጋለች ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ገለጹ፡፡

በከተማው ለቀጣዮቹ ስድስት ወራት የሚቆይ የአካባቢ ብክለት የመከላከል ንቅናቄ ትናንት ተጀምሯል፡፡

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዕለቱ እንደገለጹት፤ ከተማዋ ባለፉት ጊዜያት ባልተገራ የከተማ ልማት እድገት ሥርዓት ውስጥ በማለፏ ለተለያዩ ጉዳቶች ተዳርጋለች፡፡

አዲስ አበባ ከተማ ለመመሥረቷና ለስያሜዋ ምክንያት የሆኑ በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች ቢኖሯትም፤ በአግባቡ ባለመያዛቸው የተፈጥሮ ሀብቷን ጠብቆ ማቆየትም ሆነ ተጠቃሚ መሆን እንዳልተቻለ ከንቲባ አዳነች ተናግረዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች አክለውም፤ ከተማዋ ለከፍተኛ ብክለት በመዳረጓ በከተማዋና በዙሪያዋ በወንዞች አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎቿ ላይ የዕለት ተዕለት ኑሮ ከማጎሳቀል በተጨማሪ ከፍተኛ የደኅንነት ስጋት ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለጻ፤ ከተማዋ ከ600 ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመት ያላቸው 76 ወንዞች፣ በርካታ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብቶች፣ ጥብቅ ደን እንዲሁም ሌሎች ሀብቶች ቢኖራትም በነበረው ያልተገራ የከተማ ልማት ሥርዓት በአግባቡ መጠቀም አልተቻለም፡፡

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ በመገምገም ችግሩን ለመቅረፍና የከተማዋን ሥነ-ምሕዳር ለማሻሻል የሚረዱ ትላልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ርብርብ በልዩ ትኩረት ሲተገበሩ ቆይተዋል ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ አሁን ላይ በከተማው የተጀመረው የወንዝ ዳር ፕሮጀክት ወንዞችን ከመጥፋት እየታደገ ይገኛል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ የነበረውን የከተማዋን የአረንጓዴ ሽፋን የታደገውና ከነበረበት ሁለት ነጥብ ስምንት ወደ 15 በመቶ ያሳደገው የአረንጓዴ አሻራ፤ ከተሽከርካሪዎች የሚወጣውን በካይ ጋዝ ለመቀነስ በኤሌክትሪክ መኪና መተካት የሚያስችለው ፖሊሲ መዘጋጀት እና የኮሪደር ልማት ኢኒሼቲቮች የከተማዋን ገጽታ ከመቀየራቸው በላይ የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነት በመቀነስ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከታቸውን አብራርተዋል፡፡

በከተማው እየጨመረ ከመጣው የሕዝብ ብዛት ጋር ተያይዞ የፕላስቲክ አጠቃቀም ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ በመሆኑ አካባቢን በማይበክሉ ተለዋጭ ምርቶች መተካት አስፈላጊ መሆኑንም ነው ከንቲባ አዳነች ያስረዱት፡፡

የአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን "ብክለት ይብቃ ውበት ይንቃ" በሚል መሪ ሃሳብ ከሚያዚያ 2016 እስከ መስከረም 2017 ዓ.ም የሚቆይ የአካባቢ ብክለት መከላከል ንቅናቄ እንደሚያካሄድ መግለጹ የሚታወስ ነው።

# በንግድ ሥርዓቱ የውጭ ባለሀብቶችን ማሳተፍ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ይሁን እንጂ ከለላ የተሰጣቸው የንግድ ዘርፎች ሰፊ የአገልግሎት ተደራሽነት፣ የጥራት እና የብቃት ችግሮች የሚታይባቸውና ለሕገ-ወጥ ድርጊት መጋለጣቸው ንግድ ሥርዓቱ ላይ ተግዳሮት መፍጠሩን መንግሥት አስታውቋል።

የተከለሉት የንግድ ሥራ ዘርፎች ከቁጥጥር ሥርዓቱ አተገባበር ውስንነት ጋር በተገናኘ የፖሊሲ አፈጻጸሙን የሚገዳደሩ ክፍተቶች መስተዋላቸው ተጠቁሟል፡፡ በዚህም ምክንያት በገቢ ንግድ ከማዳበሪያና ነዳጅ፣ ከማዳበሪያ ጅምላ ንግድ በስተቀር የውጭ ባለሀብቶች በሁሉም የገቢና የጅምላ ንግድ ኢንቨስትመንት ላይ መሠማራት እንደሚችሉ መመሪያ ወጥቷል፡፡

በተጨማሪም የውጭ ባለሀብቶች ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ተከልለው በቆዩት በሁሉም የችርቻሮ ንግድ ላይ መሠማራት እንደሚችሉ መንግሥት ይፋ አድርጓል።

ለመሆኑ እነዚህ ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መሆናቸው የሚኖረው ፋይዳ ምንድነው? ከመመሪያው አፈጻጸም ጋር ተያይዞ ሊኖሩ የሚችሉ ስጋቶችና አስፈላጊ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ምን መምሰል አለባቸው በሚሉ ጉዮች ላይ የዘርፉን ባለሙያዎች ማብራሪያ ጠይቋል፡፡

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ከፍተኛ ተመራማሪ አረጋ ሹመቴ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚያቸውን ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ አድርገው ከቆዩ ሀገሮች መካከል አንዷ ነበረች። አሁን ላይ በአንጻሩ ኢኮኖሚውን በስፋት ለውጭ ባለሃብቶች ክፍት የማድረግ ሂደትን ጀምራለች።

ኢኮኖሚውን ክፍት ባደረግን ቁጥር ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት፣ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር እንዲኖር በማድረግ በኩል ትልቅ ዕድል እንደሚፈጠር የጠቆሙት ዶክተር አረጋ፤ ገበያን ለማረጋጋትና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ለተሻለ ሥራ እንዲነሳሱ በማድረግ በኩልም ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ይላሉ፡፡

በተለይ በንግዱ ዘርፍ የውጭ ሀገር ባለሀብቶች መግባታቸው ሸቀጦች በብዛት እንዲገቡ ያግዛል የሚሉት ተመራማሪው፤ ይህም ተጠቃሚው የሚኖረውን አማራጭ በማስፋትና ተወዳዳሪነትን በመፍጠር ምክንያታዊ ያልሆኑ ዋጋ ጭማሪዎችን በመቀነስ የዋጋ ንረቱን ለመቆጣጠር እንደሚረዳ ይገልጻሉ።

መመሪያው ከሚኖረው ጠቀሜታ ጎን ለጎን ስጋቶችም እንደሚኖሩ ጠቅሰው፤ የሚገቡት ባለሀብቶች የጠነከረ ልምድና የካፒታል አቅም ይዘው ስለሚመጡ የሀገር ውስጥ ነጋዴዎችንና አምራቾችን ገቢ ሊያቀጭጩ የሚችልበት ዕድል እንደሚኖርም ነው ያመላከቱት።

በተጨማሪም የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ራሱ ከማምረት ይልቅ ከውጭ በሚመጡ ሸቀጦች ላይ ይበልጥ ጥገኛ እንዲሆን ሊያደርግም ይችላል ሲሉ ስጋታቸውን አስቀምጠዋል፡፡ በተጨማሪ ምርቶችን ገዝቶ ለማስገባት በሚል ወደ ውጭ የሚደረግ የውጭ ምንዛሪ ፍሰትን በመጨመር የሚስተዋለውን የምንዛሪ እጥረት እንዳያባብስ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግም ይጠቁማሉ፡፡

የውጭ ምንዛሪው ወደ ውጭ እንዳይወጣ ለመከላከል ደግሞ ጥብቅ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ያነሳሉ፡፡

እነዚህን ስጋቶች ለመቀነስና ሀገሪቱ ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ መሥራት ይገባል የሚሉት ተመራማሪው፤ ለዚህም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፣ የውጭ ነጋዴዎች ደግሞ ተጨማሪ ግብር እንዲከፍሉ የሚያስገድድ ሥርዓት ማበጀት ይገባል ይላሉ፡፡

ወደሀገራችን የሚመጡት ኢንቨስተሮች የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታና ያለውን አዋጭነት በደንብ አጥንተው ነው የሚሉት ዶክተር አረጋ፤ በሀገሪቱ በስፋት የሚስተዋለውን የሠላም እጦት፣ የሙስና መስፋፋት፣ የሕግ የበላይነት አለመከበርና የመሠረተ ልማት በሚፈለገው ልክ አለመስፋፋትና ሌሎችንም ለሥራ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ችግሮችን መቅረፍ እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪው ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገዳ በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ ማንኛውም የንግድ እንቅስቀሴ በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ቢያዝ ጥሩ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የእኛ ነጋዴዎች መቶ በመቶ ማትረፍ ስለሚፈልጉ ነዋሪው ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠሩ ነው፡፡ ይህም መሆኑ ዋጋ ንረትን በማባባስ በኩል ትልቅ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ፡፡

ጤናማ የንግድ ሥርዓት ያላቸው የበርካታ ሀገራት የትርፍ ህዳግ ከ10 በመቶ ያልበለጠ ነው የሚሉት ተመራማሪው፤ ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ ሆነው የቆዩ ዘርፎች ክፍት መደረጋቸው ትልቅ ውድድር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ የሚስተዋለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት ያስችላል ይላሉ፡፡

ይሁን እንጂ ሥራውን የውጭ ባለሀብቶች ብቻ ጠቅልለው እንዳይወስዱት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በማደራጀት አቅም እንዲፈጥሩና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀጥሉ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያነሳሉ።

ኬንያን ለአብነት በማንሳት ሁለት ትልልቅ የችርቻሮ ማዕከላት እንዳሏት የሚጠቅሱት ፕሮፌሰር ዓለማየሁ፤ በየትኛውም የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች የሚገበዩትም ከእነዚህ ድርጅቶች በመሆኑና ቁጥጥር በመኖሩ ባለፉት 15 ዓመታት ውስጥ በአንዳንድ እቃዎች ላይ የሚታየው የዋጋ ጭማሪ ከ30 በመቶ ያነሰ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

እኛ ሀገር ግን የአንድ እቃ ዋጋ በየእለቱ 30 በመቶ የሚጨምርበት ሁኔታ እንደሚስተዋል የሚጠቅሱት ፕሮፌሰሩ፤ በመሆኑም አዲሱ መመሪያ የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር የሕዝቡን ጫና ለመቀነስ ትልቅ አቅም እንደሚሆን ያስረዳሉ፡፡

በቀጣይ በሥራ ላይ የሚገኙ ትልልቅ የገበያ ማዕከላትን መደገፍና ጥሩ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀጥሉ ማድረግ ይጠበቅብናል የሚሉት ተመራማሪው፤ የሚስተዋሉ ዋጋ ለውጦችን ለምን ማለት የሚችል ጠንካራ የሸማች ማኅበራት መፍጠርም ያስፈልጋል ሲሉ ይገልጻሉ።

ሸማች ማኅበራት በነጋዴዎች ላይ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችሉት የነጋዴዎችን ቁጥር ሰብሰብ አድርጎ የተጠናከሩትን መያዝ ሲቻል ነው፤ ይህም ለቁጥጥር ከማገዙ ባሻገር አቅማቸውን አሰባስበው ከውጭ ባለሀብቶች ሊገጥማቸው የሚችለውን ውድድር ለመቋቋም ያግዛቸዋል ይላሉ፡፡

በሌላ በኩል ዘርፉን ለባለሀብቶች መክፈት ትልቅ ርምጃ ቢሆንም ስለተፈቀደ ብቻ ይገባሉ ማለት አይደለም ያሉት ተመራማሪው፤ በመሆኑም ዘላቂ ሀገራዊ ሠላም ማስፈንና በአጭር ጊዜ ወደ ትግበራ ገብተው የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያስመዘግቡ የሚያስችል ምቹ ሀገራዊ ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ ያመላክታሉ፡፡

እንደ ባለሙያዎቹ ማብራሪያ፤ ለውጭ ሀገር ባለሀብቶች ዝግ ሆነው የቆዩ ዘርፎች መከፈታቸው ትልቅ ርምጃ ቢሆንም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ላይ ሊደርስ የሚችለውን የመዋጥና በገቢ የመቀጨጭ ስጋት ለመቀነስ እንዲያጠናክሩ ማገዝና አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ኢንቨስተሮች ገብተው የሚፈለገውን ውጤት እንዲስመዘግቡ ዘላቂ ሠላምና ምቹ የሥራ ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ ያስታወቁት ባለሙያዎቹ፤ የውጭ ምንዛሪን ከሀገር ማስወጣት ችግር እንዳያጋጥምም ጠንካራ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት እንደሚያስፈልግ አፅንዖት ሰጥተዋል።

# በኢትዮጵያ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አገልግሎቱ በሀገሪቱ በሚገኙት አንድ ሺህ 22 ወረዳዎች ተደራሽ መሆኑም ተመልክቷል።

የኢትዮጵያ ጤና መድኅን አገልግሎት የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር አፈጻጸምን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት በአዳማ ከተማ ገምግሟል።

የጤና ሚኒስትር ዴኤታ ደረጀ ድጉማ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ የጤና መድኅን አገልግሎት በሀገር አቀፍ ደረጃ የጤና ተደራሽነትን፣ ጥራትን እና የፋይናንስ ድጋፍን ለማረጋገጥ ጉልህ ሚና አለው።

ባለፉት ዓመታት በተሠሩት ሥራዎች 55 ሚሊዮን ዜጎችን የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድኅን አባል በማድረግ የጤና ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ መደረጉን አስታውቀዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የጤና መድኅን አገልግሎት ከተጀመረ በኋላ ጤና ተቋም የሚመጡ ዜጎች ቁጥር በእጥፍ መጨመሩን ገልጸው፤ የጤና መድኅን አገልግሎት ተደራሽነትን ለማስፋፋት ጤና ሚኒስቴር የፋይናንስና ቴክኒካል ድጋፍ እያደረገ ነው ብለዋል፡፡ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችም በባለቤትነትና በቁርጠኝነት ሊሠሩ እንደሚገባ ተናግረዋል።

በቀጣይም ተደራሽ ያልሆኑ ወረዳዎችንና ቀበሌዎችን ተደራሽ ማድረግ፣ የተሰበሰቡ ገንዘቦችን በአግባቡ መጠቀም፣ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን ማዘመን፣ የሕክምና አሰጣጥ ሥርዓትን ማሻሻል፣ የመድኃኒትና የግብዓት አቅርቦትን ማሟላት ላይ ትኩረት ሊደረግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የኢትዮጵያ ጤና መድህን አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ወርቁ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የጤና ተደራሽነትን ለማስፋፋት በተሠራው ሥራም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም በአንድ ሺህ 22 ወረዳዎች 10 ነጥብ ስምንት እማወራና አባወራ ተጠቃሚ ሆነዋል።

በማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አገልግሎት 12 ሚሊዮን እማወራና አባወራን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 10 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን እማወራና አባ ወራዎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስረድተዋል።

በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ብቻ መክፈል የማይችሉ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን እማወራና አባወራዎች የማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድኅን አባል ማድረግ መቻሉንም ጨምረው ገልጸዋል።

የጤና መድኅን አገልግሎት ተደራሽ ያልሆነባቸውን አካባቢዎች ተደራሽ ለማድረግ እና ሰዎች ገንዘብ የለኝም ብለው ከጤና አገልግሎት እንዳይርቁ በትኩረት እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 30 ወረዳዎችን በአዲስ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ለጤና አገልግሎት የሚውል የመድኃኒት አቅርቦትን ለማሟላት በተለይ በርካታ የሕዝብ ቁጥር ባለባቸው አማራና ኦሮሚያ ክልሎችን ጨምሮ በየአካባቢው የማኅበረሰብ መድኃኒት ቤት እንዲኖር እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በማኅበረሰብ አቀፍ የጤና መድን አገልግሎት ያሉትን ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# “የአፍሪካ ቀንድን የተረጋጋ ለማድረግ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለመካከለኛው ምሥራቅ እና እስያም ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን አንስተዋል፡፡ ከሀገራዊ ወሰን የዘለለ የጋራ እርምጃ በማስቀመጥ ለሀገራቱ ሰላም፣ መረጋጋትና ብልፅግና መሥራት እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ በአሁን ወቅት አፍሪካ ቀንድ ዘርፈ ብዙ የፀጥታ ችግሮች፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የአየር ንብረት ለውጥና ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እያጋጠመ ይገኛል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ስር ከሰደዱ የታሪክ ቅሬታዎች፣ የብሔር ግጭቶችና የአስተዳደር ጉድለቶች የመነጩ ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ የውጭ ተዋናዮች ግልጽና ስውር አጀንዳ ያላቸው የፀጥታውን ገጽታ የበለጠ እያወሳሰቡ ይገኛሉ፡፡

በሰዎች ላይ የሚደርሰው የፀጥታ ችግር እጅግ አስደንጋጭ መሆኑን፤ ይህም ልማትን እንደሚያደናቅፍ፣ ሰብዓዊ ቀውሶችን እንደሚያባብስ፣ ቀጣናዊ መረጋጋትን እንደሚያዳክም ጠቅሰዋል፡፡

የታጠቁ ቡድኖች እና አሸባሪ ድርጅቶች ስቃይ ከማድረስ ባለፈ የልማት ጥረቶችን በማደናቀፍና አስፈላጊ የንግድ መስመሮችን በማወክ የቀጣናዊ ኢኮኖሚያዊ ውሕደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደሩ መሆናቸውንም ነው ሚኒስትር ዴኤታው የገለጹት፡፡

ሆኖም፣ በእነዚህ ተግዳሮቶች መካከል፣ የተስፋ ጭላንጭል አለ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ እንደ ባለድርሻ አካላት መንግሥታትን፣ የቀጣናውን ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ አጋሮችን ያቀፈ የጋራ ሥራ ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡። ”የፀጥታ ስጋቶችን ለመፍታት ብሔራዊ ድንበሮችን የሚሻገር የጋራ እርምጃ እንደሚጠይቅ እንረዳለን” ነው ያሉት፡፡

ውይይቱም የፀጥታ ችግሮችን ለመቅረፍ ገንቢ ሀሳቦች የሚሰጥበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጃፈር በድሩ በበኩላቸው፣ የጋራ ውይይቱ የእውቀትና የሃሳብ ልውውጥ በማድረግ ለቀጣናው ሕዝቦች አዳዲስ መፍትሔዎችን በማፈላለግ ረገድ መሠረታዊ ነው ብለዋል፡፡ የደኅንነት ፈተናዎችን ለመሻገርና ለአፍሪካ ቀንድ ሕዝቦች አስተማማኝ እና የበለፀገ ሕይወትን ለማምጣት በጋራ ለመሥራት እንደሚያስችልም ጠቅሰዋል፡፡

በምስራቅ አፍሪካ የሚያጋጥሙ ወቅታዊ ፈተናዎችን ለመሻገር መሰል ውይይቶች ትልቅ ሚና እንዳላቸው፤ ውይይቱ በሠላምና ፀጥታ፣ በሰብዓዊና ሌሎች ጉዳዮች የተለያዩ ተመራማሪዎች ሀሳባቸውን የሚሰጡበትና ለቀጣናው ሕዝብ የሚበጅ የፖሊሲ አቅጣጫዎች የሚመላከቱበት መድረክ መሆኑን አንስተዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ያዘጋጀው ውይይት “ለውስብስብ ጉዳዮች አማራጭ መንገዶችን በመፈለግ፤ በአፍሪካ ቀንድ ቀጣናዊ ደኅንነትን ማረጋገጥ” በሚል መሪ ሀሳብ የተካሄደ ሲሆን፤ በውይይት መድረኩ ሚኒስትር ዴኤታዎች፣ የዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ ተወካዮች፣ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ተወካዮች፣ ተመራማሪዎችና ባለ ድርሻ አካላት ተሳትፈዋል፡፡

## ነፃ ሃሳብ

# የተከራዮች እንባ አባሹ

በኃይሉ አበራ

መንግሥት በከተሞች በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ የሚስተዋለውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ሲያደርግ ቆይቷል። የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በመገንባትና በእጣ በማስተላለፍ፣ ነዋሪዎች ተደራጅተው የመኖሪያ ቤቶችን እንዲገነቡ ቦታ በማቅረብ እየሠራ ነው። የግሉ ዘርፍ በበኩሉ በሪል ስቴት ልማት በመሠማራት የመኖሪያ ቤቶችን እየገነባ ይገኛል። የቤት ባለቤቶች በየቤታቸው ተጨማሪ ቤቶችን በመገንባት በማስፋፋት የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ላይ የበኩላቸውን ሲያደርጉ ኖረዋል።

እንዲያም ሆኖ ግን የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና ፍላጎቱ ሊጣጣም አልቻለም። ችግሩ በተለይ በመኖሪያ ቤት ተከራዮች ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ይገኛል። በተለይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ነዋሪ ባለባት አዲስ አበባ ከተማ ችግሩ ስር የሰደደ ሆኖ በመቆየቱ ተከራዮች ለተለያዩ ችግሮች ሲዳረጉ ይስተዋላሉ።

የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋው በተለይ ዝቅተኛ ገቢ ባለው ማህበረሰብ ላይ ያሳደረው ጫና ከፍተኛ ቢሆንም መካከለኛ ገቢ ያለውም ቢሆን የችግሩ ሰላባ ሆኗል። ደላላዎችና ስግብግብ አከራዮች የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋ እንዲንር እያደረጉ ያልተገባ ጥቅም ሲያግበሰብሱ ኖረዋል። እነዚህ አካላት በትንሹም በትልቁም ምክንያት ዋጋ በመጨመር ህብረተሰቡን እያሰቃዩ ይገኛሉ።

የመኖሪያ ቤቶችን ዋጋ ጨምረው ለማከራየት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ተከራዮች ባሉበት የሚጨምሩት ዋጋ አንሷቸው አንዴ ቤቱን ራሳቸው ሊገቡበት ማሰባቸውን፣ ልጆች ወይም ዘመዶቻቸው ከውጭ ስለሚመጡ ለእነሱ ሊያውሉት ማቀዳቸውን፣ በቤቱ ላይ መሠረታዊ እድሳት ሊያደርጉ መሆናቸውን፣ ወዘተ እየጠቀሱ ተከራዮችን በማስወጣት ለሌላ ተከራይ በከፍተኛ ዋጋ ሲያከራዩ ኖረዋል።

የችግሩን አሳሳቢነት ተከራዮች ብቻም ሳይሆኑ የችግሩን አሳሳቢነት የተገነዘቡ አካላት ለመንግሥት ሲያስገነዝቡ ቆይተዋል፤ መንግሥትም የችግሩን አሳሳቢነት በመጥቀስ መፍትሔ ማኖር የሚገባ መሆኑን ሲገልጽ መቆየቱ ይታወቃል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከዚህም አለፍ ያለ ርምጃ ሲሰወድም ቆይቷል።

ከተማ አስተዳደሩ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጀምሮ ተከራዮች ላይ የሚደርሰውን የቤት ኪራይ ዋጋ መናር ለመቆጣጠር እየሠራ ነው። ለስድስት ወራት የቤት ኪራይ ዋጋ መጨመር እንደማይቻል መመሪያ አውጥቶ በየስድስት ወሩ በተደጋጋሚ በመተግበር ተከራዮችን ታድጓል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቅርቡ ያወጣው የመኖሪያ ቤት ቁጥጥር እና አስተዳደር አዋጅም በሀገሪቱ ስር የሰደደ ችግር ሆኖ የኖረውን ይህን መኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋ መናር በጊዜያዊነት ለመፍታት ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ይታመናል። በአዋጁ መሠረት በመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋ ላይ እንዳሻቸው ሲወስኑ የኖሩትን ደላላዎችን የሚያስወጣ ፣ የቤት ባለቤቶች ብቻቸውን ኪራይ እንዳይወስኑ ያደርጋቸዋል።

በሀገሪቱ በቤት ኪራይ ብቻ ሳይሆን፣ ቤት፣ መኪናና በመሳሰሉት ሽያጭ ዋጋ ላይ ጭምር እንዳሻቸው በመወሰን የሚታወቁት እነዚህ ደላላዎች ከመኖሪያ ቤት ኪራይ ተዋናይነታቸው መውጣታቸው በኪራይ ዋጋ ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ከወዲሁ እየተገመተ ነው። ደላሎች በሀገሪቱ እየታየ ላለው የኑሮ ውድነት ከዋንኛዎቹ ተጠያቂዎች መካከል የሚጠቀሱ እንደመሆናቸው በአዋጁ አማካይነት በቤት ኪራይ ውስጥ ያላቸውን ሚና ማሳጣት ማለት የኑሮ ውድነቱን በሆነ መልኩ ማርገብም ይሆናል።

መንግሥት በመኖሪያ ቤት ኪራይም ላይ እየታየ ያለውን የቤት ኪራይ ዋጋ ለማረጋጋት አዋጅ ማውጣቱ፤ እነዚህን ደላሎች ከግብይት ሰንሰለቱ በማስወጣት ጤነኛ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ምህዳር እንዲኖር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በአዲስ አበባም ሆነ በትላልቅ የሀገራችን ከተሞች በግለሰብ ቤት ተከራይቶ የሚኖረው አብዛኛው ነዋሪ በቤት ኪራይ ዋጋ በየጊዜው መናር ሲማረር ቆይቷል። ገቢውና ለመኖሪያ ቤት የሚጠየቀው የኪራይ ዋጋ ጨርሶ የሚመጣጣን አይደለም፤ ከገቢው አብዛኛውን ለቤት ኪራይ የሚያውለውን ተከራይ ቤቱ ይቁጠረው ብሎ መተው ይቀላል። ተከራዮች ሥራ ውለው የሚገቡት ለቤት ኪራይ ለመክፈል እስከሚመስል ድረስ ከገቢያቸው ከፍተኛ የሚባለውን መጠን እያዋሉ ይገኛሉ።

ተከራዮች ይህንን ክፍያ በተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ከፍለው እንዳይኖሩ ደላላዎችና አከራዮች ብዙ ጫናዎችን ያሳድሩባቸዋል። በዚህ የተነሳም ከዛሬ ነገ ቤቱን እንፈልገዋለን ልቀቁ ወይም ኪራይ ጨምሩ እንባላለን ብለው በከፍተኛ ስጋት ውስጥ ሆነው ነው የሚኖሩት። ይህ ሁኔታ ያስመረራቸው ተከራዮች ከመሀል ከተማ ወደ ዳር ብዙም ወዳልለማው አካባቢ ቤት ሲከራዩ መመልከት የተለመደ ነው።

ይህ ሁኔታ በመኖሪያ ቤት ኪራይ በኩል ያለውን ጫና ለጊዜውም ቢሆን ያቃልልላቸዋል፤ ሁኔታውን የሚቀበሉት ግን ወደ ሥራ ቦታ ለመሄድ ለመምጣት በሚያወጡት ትራንስፖርት ወጪና ጊዚያቸው ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽእኖ ዋጥ በማድረግ ነው።

በእዚህ ሂደት እቃ በመጓጓዝ ሂደት ለትራንስፖርት ከሚያወጡት በተጨማሪ ያልተገባ ዋጋ ለሚጠይቁ እቃ ጫኝና አውራጅ ለተባሉ ሌሎች በላተኞች ሲዳረጉም ኖረዋል። ጫኝ አውራጅ የሚያስከትለው ችግር በተከራይ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ባይሆንም፣ በኪራይ ዋጋ መናር ከስሩ በተነቀለው ተከራይ ላይ ግን ጫናው ከፍተኛ ነው። ይህን ችግር ፍራቻ ብዙዎች ቤት የሚለቁትም ወደ አዲስ ቤት የሚገቡት በሌሊት እስከ መሆን የደረሰበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል።

**እነዚህንና የመሳሰሉትን ችግሮች ፍራቻ ተከራዮች አካራይና ደላላ የጣሉባቸውን የቤት ኪራይ ዋጋ ተሸክመው ለመኖር የሚገደዱበት ሁኔታ በርካታ ነው:: እዚህ አናነሳውም እንጂ የአከራዮች ብዙ ያልተገቡ ባህሪዎች በተከራዮች ላይ የሚያደርሱት ችግር ከፍተኛ እንደሆነም ይታወቃል:: ይህን ሁሉ ችለውም በቤት ኪራይ ዋጋ እየተፈተኑ ያሉት**

እነዚህንና የመሳሰሉትን ችግሮች ፍራቻ ተከራዮች አካራይና ደላላ የጣሉባቸውን የቤት ኪራይ ዋጋ ተሸክመው ለመኖር የሚገደዱበት ሁኔታ በርካታ ነው። እዚህ አናነሳውም እንጂ የአከራዮች ብዙ ያልተገቡ ባህሪዎች በተከራዮች ላይ የሚያደርሱት ችግር ከፍተኛ እንደሆነም ይታወቃል። ይህን ሁሉ ችለውም በቤት ኪራይ ዋጋ እየተፈተኑ ያሉት።

አሁን ተከራዮች ለመኖሪያ ቤት የሚከፍሉት ገንዘብ የወር ደመወዝተኛ ከሆኑ ከገቢያቸው ከ70 በመቶ በላይ መሆኑን በዘርፉ ላይ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ሲገልጹ ተሰምቷል። ይህም በአማካይ የተሰላ ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ። አንዳንዶች ሙሉ ደሞዛቸውን ለመኖሪያ ቤት ኪራይ እንደሚከፍሉ ይነገራል።

ለሌሎች ወጪዎች ሲሉ ደግሞ የትርፍ ሰዓት ሥራ ውስጥ እንደሚገቡ፣ ወይም በተለያዩ ምንጮች የሚደገፉበት ሁኔታ እንዳለም ይገለጻል። ባልና ሚስት የአንዳቸውን ደሞዝ ለቤት ኪራይ ያደረጉበት ሁኔታ እንዳለ ሲነገር ሰምቻለሁ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣው አዋጅ ከቤት ኪራይ ዋጋ መናር ጋር በተያያዘ ለበርካታ ችግሮች እየተጋለጠ የሚገኘውና የተረጋጋ ኑሮን ለመምራት ለተቸገረው ለእዚህ ተከራይ እፎይታን ይሰጣል። በአከራይና ደላሎች ብቻ ሲወሰን በኖረው የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋ ላይ መንግሥት ጣልቃ ገብቶ ቁጥጥር ማድረግ ውስጥ መግባቱ የኪራይ ዋጋው እንዲረጋጋ ያደርጋል።

የመኖሪያ ቤት አቅርቦት አንገብጋቢ እና መሠረታዊ የመብት ጉዳይ ነው። መንግሥት የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን ለማሟላት በተለያዩ አማራጮች ላይ እየሠራ መሆኑም ይታወቃል። ከዚህ ጥረቱ ጎን ለጎን ደግሞ በየጊዜው እየናረ ያለውን የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋ ለማረጋጋት እንዲቻል የተከራዩን ማህበረሰብ አቅም ባገናዘበ መልኩ መኖሪያ ቤቶች የሚከራዩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ይህን አዋጅ ማውጣቱ ሊያስመሰግነው ይገባል።

በአዋጁ ላይ እንደተመለከተው፤ አዋጁ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥር እና አስተዳደር ግልጽነት፣ ተጠያቂነት ያለውና የአከራዮችንም ሆነ የተከራዮችን ጥቅም እና መሠረታዊ መብቶች ሚዛን በጠበቀ መልኩ ለማስተናገድ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በአዋጁ መሠረትም የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውል ዘመን ከሁለት ዓመት ማነስ የለበትም። የአንድ ቤት ባለቤትነት በውርስ፣ በሽያጭ፣ በዕዳ፣ ወይም በሌላ ማንኛውም ሕጋዊ ምክንያት ለሌላ ወገን ከተላለፈም የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውሉ ሊቋረጥ የሚችለው ለተከራዩ የስድስት ወር ማስጠንቀቂያ ከተሰጠ በኋላ ይሆናል።

ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውል የኪራይ ዘመኑ ሳይጠናቀቅ ያለ ማስጠንቀቂያ በአከራይ ሊቋረጥ የሚችልበት ሁኔታ ስለመኖሩ በአዋጁ ላይ ተገልጿል። ተከራዩ የቤተ ኪራዩን በውሉ በተመለከተው የመክፈያ ጊዜ ለመጀመሪያ ከሆነ ከ15 ቀን ካሳለፈ፤ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖም የቤት ኪራዩ በውሉ ከተመለከተው ቀን ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነና ሰባት ቀን ካለፈው፤ ቤቱን ካለ አከራዩ ፈቃድ ከመኖሪያነት ውጭ ለንግድ ሥራ ከተጠቀመበት፤ የአካባቢውን ሰላምና ጸጥታ በተደጋጋሚ የሚያውክ ከሆነ፣ ቤቱን ለወንጀል መፈጸሚያ የሚጠቀም ከሆነ ቤቱ ላይ አስቦበት ወይም በቸልተኝነት ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ ውሉ ሊቋረጥ የሚችል መሆኑ ተመላክቷል።

እነዚህ ሁኔታዎች ተከራዩን ብቻ ሳይሆን አከራዩንም ሊታደጉ የሚችሉ ድንጋጌዎች በአዋጁ መካተታቸውን ያመለክታሉ። አንዳንድ ተከራዮች በአከራዮች ላይ የሚያደርሱትን ሕገወጥ ተግባር ለመቆጣጠርና ለመከላከልም የሚያስችል በመሆኑ ሁለቱንም ወገኖች ተጠቃሚ የሚያደርግ አዋጅ ነው።

ያለምንም ተቆጣጣሪና አስተዳዳሪ በአከራዮችና ደላላዎች ስሜት ብቻ ሲመራ የኖረው የመኖሪያ ቤት ኪራይ ዋጋ አብዛኛውን ተከራይ በእጅጉ የፈተነ ቢሆንም፣ ከቤት ኪራይ ጋር በተያያዘ ሁሉም አከራይ በኪራይ ዋጋ ላይ ተመሳሳይ አቋም አለው ብሎ መደምደም የማያስችልበት ሁኔታ እንዳለም መጠቅስ እወዳለሁ። በቁጥር ቢያንሱም አንዳንድ አካራዮች በቤት ኪራይ ዋጋ ላይ ከተከራይ ጋር ሰላማዊ ግንኙነት ያላቸው መሆናቸውን መጥቀስ ያስፈልጋል።

እነዚህ አከራዮች ከተከራዮች ጋር ያላቸው ቤተሰባዊ ግንኙነትና በቤት ኪራይ ዋጋ በኩልም ተነጋግረው የሚወስኑበት እንዲሁም አንዳንድ ተከራዮችም አስበው ዋጋ የሚጨምሩበት ሁኔታ ሲታሰብ ሁሉንም አከራይ በአንድ ቅርጫት ውስጥ መከተት ተገቢ እንዳልሆነ እንድናሳብ ያደርገናል።

እነዚህ አከራዮች ኪራዩ የሚያዋጣቸው መሆኑን አስበው እንጂ ለጽድቅ ብለው አይደለም ከተከራዮች ጋር በገበያ ዋጋና በፍቅር አብረው እየኖሩ ያሉት። እነዚህ አከራዮች ቤት የሚያከራዩበት ዋጋ በቀጣዩ ለቤት ኪራይ የሚወጣ ዋጋ መነሻ ተደርጎ ሊያገለግል እንደሚችል ቢገመት ስህተት አይሆንም።

አንዳንድ ተከራዮች አከራዮችን አመል እንደሚያ ሰወጡም ማሰብም ያስፈልጋል። የተከራዩትን የመኖሪያ ቤት ላልተገባ ተግባር ማዋል፣ በበሮች፣ መስኮቶች፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ በኤሌክትሪክ መስመሮች፣ ወዘተ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ በሌሊት ቤት ቤቱን ለቀው የሚሄዱና አከራዮች ለቤት እድሳት ከፍተኛ ሀብት እንዲያወጡ የሚያደርጉ ተከራዮችም እንዳሉ ሲታሰቡ አከራዮችን ብቻ መወንጀሉ ተገቢነት እንደሌለው ያስገነዝባል።

ይህ አዲስ አዋጅ እነዚህን ሁለት ወገኖች በሚገባ የሚመለከት እንደሚሆን ይጠበቃል፤ አከራይና ተከራይ በሕግና ሕግ አግባብ ብቻ ዋጋ ተዋውለው የቤቱ መሠረተ ልማቶችም በሚገባ ተጠብቀው የሚቆዩበት፣ ጉዳት ደርሶባቸው ከተገኙም የሚጠገኑበትም ሁኔታንም ያያል ብዬ አስባለሁ።

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ከኢትዮጵያ ምድር የሚመነጨውን ውሃ በፍትሐዊነት የመጠቀም መብት አለን››

*- ያሲን መሐመድ(ዶ/ር)*

*በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካና የኤዢያ ጥናትና ምርምር ማዕከል መምህር እና ተመራማሪ*

ምሕረት ሞገስ

ውሃ ለሰው ልጅ መሠረታዊ ከሚባሉ ፍላጎቶች መካከል ቀዳሚው ነው። በምድር ላይ ለሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ ውሃ የእስትንፋስ መቀጠያ ትልቅ የተፈጥሮ ፀጋ ነው። ከውሃ ጋር ያልተቆራኘ አንዳችም ነገር ለማግኘት እጅጉን ያዳግታል። የእዚህን የተፈጥሮ ስጦታ ጥቅም ከሰው ልጆች ህልውና ጋር ብቻ እናስተሳስረው ብንል እንኳን፤ እጅግ ብዙ መሠረታዊ ጥቅሞችን ማግኘት እንችላለን። ውሃን ቀለል አድርገን ስንገልጸው ምግብ ንፅህና፣ መጓጓዣ እና ሌሎችም ዝርዝር ጥቅሞችን ይሰጠናል።

እነዚህን መሠረታዊ ጥቅሞች ለመገንዘብ ብዙ መመራመር አሊያም መምጠቅ አይጠይቅም። ሰው ሆኖ ብቻ መፈጠር በቂ ነው። ይሁን እንጂ ውሃ ከዚህም የዘለለ አያሌ አዎንታዊ ጎኖችን የያዘ ነው። ይህንን በግለሰብ ደረጃ ሳይሆን ሰፋ አድርገን በሀገር ደረጃ ለመመልከት ባህር፣ ውቂያኖስና ወንዞች የሚኖራቸውን ጥቅም ማየት ይቻላል። ይህንኑ መሠረት በማድረግም ውሃ ከአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ፖለቲካዊ ጥቅም አንፃር የሚኖረውን ፋይዳ፣ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ለማውራት ወድደናል። በተለይ ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ የውሃ ሀብት፣ በባህር በር ጉዳይ ሊኖራት ስለሚገባው ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ መብቶች ከጋበዝናቸው እንግዳ ጋር በስፋት ስንጨዋወት ቆይተናል። ከዚያ አስቀድመን ግን ለርእሰ ጉዳያችን ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ የባህር በር ለአንድ ሀገር ስለሚኖረው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳ የተሠሩ የጥናት ውጤቶች ምን ይላሉ የሚለውን በጥቂቱ ለመዳሰስ እንሞክር።

የባህር ወደቦች መዳረሻ በአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ ውስጥ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ዘኮንቨርሴሽን ዶትኮም የተባለ ድህረ ገፅ ጥናታዊ ጽሑፍ ውጤቶችን መሠረት አድርጎ መረጃ አውጥቷል። የመጀመሪያው ሚና የኢኮኖሚ ዕድገት እና ንግድና የውጭ ምንዛሪ ገቢ ሲሆን፤ የባህር ወደቦች ዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥን በማመቻቸት፣ ሀገሮች ወደ ውጭ በመላክና ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት የውጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ እንደሚያስችላቸው ይጠቅሳል።

ሌላኛው ጥቅም ከፍተኛ ወጪን መቀነስ ሲሆን፤ ይህም የባህር ወደብ ባለቤት መሆን ቀልጣፋ ከውጭ ለሚገቡ እቃዎች፣ የፍጆታ ምርቶች እና ጥሬ ዕቃዎች የመጓጓዣ ወጪን እንደሚቀንስ ይገልፃል።

ይሄው ድህረ ገፅ እንደሚያብራራው፤ ሌላኛው ጠቀሜታቸው ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት ነው። የባህር ወደቦችን ማግኘት (ባለቤት መሆን) የአንድ ሀገርን በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነት እንደሚያሳድግ ያስረዳል። በተጨማሪነትም ከፖለቲካ አንፃር ስልታዊ ተጽዕኖ እና ነፃነት እንዲኖር ጉልህ የሚባል አስተዋጽኦ እንዳለው ያስረዳል። በዋናነትም የባህር ዳርቻ ተደራሽነት ለሀገር የበለጠ ፖለቲካዊ ተጽእኖን ይሰጣል፣ ይህም በክልላዊ እና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ፍላጎቱን ለማስጠበቅ ያስችላል።

እነዚሁ ጥናቶች እንዳረጋገጡት የባህር በር ባለቤት መሆን የጂኦስትራቴጂክ አማራጮችን ያጎናፅፋል። የባህር ወደቦች የአንድን ሀገር የጂኦስትራቴጂክ አማራጮችን በማስፋት፣ ተለዋዋጭ የቀጣና ሁኔታዎችን በብቃት ለመምራት እንደሚያግዝ ጥናቶቹ ያስረዳሉ።

ከላይ ያነሳነው ዝርዝር መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የዛሬው የዘመን እንግዳችን ያሲን መሐመድ (ዶ/ር) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካና የኤዢያ ጥናትና ምርምር ማዕከል መምህር የሚከተሉትን ማጠናከሪያ ሃሳቦች ያነሳሉ። የዝግጅት ክፍላችንም እነዚህን ጉዳዮች የሚመለከቱ ጥያቄዎችን በማንሳት የሚከተለውን ምላሽ አቅርቦላችኋል። መልካም ንባብ፦


ፎቶ ገባቦ ገብሬ

**አዲስ ዘመን፦ በሀገር ደረጃ የውሃን ጥቅም እንዴት ይገልፁታል?**

**ዶክተር ያሲን፦** ውሃ ከግለሰብ እስከ ሀገር ድረስ የማይተካ ሚና አለው። ውቂያኖሶች አንደኛውን የዓለማችን ክፍል ከሌላኛው ክፍል ለማገናኘት ይረዳሉ። የንግድ መርከቦች ከአፍ እስከ ገደፋቸው ቁሶችን ጭነው ከተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ወደብ ጋር እየተፋተጉ ሳምንታት፣ ወራትን ጉዞ የሚያደርጉት በእነዚህ የውሃ አካላቶች ላይ ተመስርተው ነው። የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎት የሚሟላው በባህር ላይ በሚካሄዱ የንግድ መስመሮች ነው። መንግሥታት የዜጎቻቸውን ደህንነት፣ ሉዓላዊነት፣ ለማረጋገጥ የግዴታ እነዚህን የባህር ክፍሎች መቆጣጠር ይኖርባቸዋል። ከዚህ አኳያ ስንመለከተው ውሃ ከንፅህና መጠበቂያ፣ ከመጠጥ፣ ከምግብና ከማብሰያነት የዘለለ በዓለምም ሆነ በሀገር ደረጃ ትርጉሙ ላቅ እንደሚል እንረዳለን።

ይህንን መነሻ በማድረግ የዓለማችን ሀገራት የውሃ ሀብት ላይ በስፋት ይሠራሉ። ከዝናብና ከከርሰ ምድር የሚገኝ የውሃ ሀብትን በጥንቃቄ ለመጠቀም ፖሊሲ ያወጣሉ። የሚያዋስናቸውን ባህር ለመቆጣጠርና ከዚያም ጥቅም ለማግኘት አቅማቸውን ሁሉ አሟጥጠው ይሠራሉ። በጥቅሉ ውሃ ለሰው ልጆች የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ተያያዥ ጉዳዮች ቁልፍ ድርሻ ይወስዳል።

ውሃ እንደ ሀገር ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ በመሆናችን ብቻ ለምንኖረው ኖሮ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከእዚህኛው ዘመን ቀደም ብሎ በነበሩ ጊዜያት ውሃ የስልጣኔ መሠረትም ሆኖ የሚታይ ነው። ለምሳሌ በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ማህበር ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች አብዛኛውን ኑሯቸው ተፈጥሮን መሠረት ያደረገ በመሆኑና የሚመገቡትም ፍራፍሬ ለቅመው፤ አደን አድነው እንደመሆኑ መጠን ያን ያህል በስልጣኔ ሳይራመዱ ቀርተዋል። ከዛ በኋላ ግን የነበሩ ክስተቶች በሙሉ ይጓዙ የነበሩት ውሃን ተከትለው ስለነበር ወንዞች አካባቢ ሰዎች ሰፍረው የግብርና ሥራ መሥራት ጀመሩ። በዚህ ደግሞ የመጀመሪያው የስልጣኔ መነሻ ግብርና ሆነ።

ከዚህ ቀጥሎ ያሉ የዓለም ትላልቅ ስልጣኔዎች መነሻቸው ወንዝ ዳር በመስፈር የግብርና ሥራ መሥራት ሆነ። ለምሳሌ የግሪክ የሮም የሜሶፖታሚያ ቻይናና ሌሎችም የስልጣኔ መነሻቸው ግብርና ነው። የግብርና ሥራውን ከተጠቀሙ በኋላ ውሃን መሠረት አድርገው የዞሩት ወደ ትራንስፖርት ዘርፉ ነው። የተለያዩ መጓጓዣዎችን እየሠሩ በወንዞች ላይ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ጀመሩ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ደግሞ ፖርቹጋሎች በውሃ ከላይ እየተጓጓዙ ወደ አፍሪካ ኋላም ህንድ መድረሳቸው ነው። የማጂላን ጉዞ እና ሌሎችም ሁሉም የዓለምን ስፋት ያዩት እና ጉዞ ያደረጉት ውሃን በመጠቀም ነው።

በጠቅላላው ውሃ በጣም አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ወንዝ ለግብርና ሥራ ለትራንስፖርት ወዘተ ጠቀሜታው በጣም የጎላ ስለሆነ፤ እኛም በተለያዩ ጊዜያት ቁጭ ብለን ስለውሃና ውሃ ጉዳይ እያነሳን እንወያያለን። ብቻ በአጠቃላይ ቀለል ባለ መልኩ እንደሚገለጸው ውሃ ሕይወት ነው። ለሀገር ደግሞ ዕድገት አሁን ላይ ደግሞ ትልቅ የደህንነት መሳሪያም ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- ከዚህ አንጻር አንድ ሀገር ባህር አላት ማለት ትርጉሙ ምንድን ነው? ጥቅሙስ እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር ያሲን፡-** የባህር በር ባለቤት የመሆን ጠቀሜታ ልማት እና ክልላዊ ተጽእኖ ፈጣሪ መሆን መቻል እንደሆነ ጥናቶች ያስረዳሉ። የባህር ወደቦች ንግድን፣ ኢንቨስትመንትን እና ኢንደስትሪላይዜሽንን በማመቻቸት ለኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦዋቸው ከፍ ያለ ድርሻ እንደሚወስዱ ጥናቶቹ ያብራራሉ። በተጨማሪ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ላይ ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው ይገልፃሉ። ወደቦች በአጎራባች አካባቢዎች ልማትን በማበረታታት፣ የሥራ እድል በመፍጠርና እና መሠረተ ልማትን በማሻሻል የማይተካ ሚና እንዳላቸው ጥናቶቹ ይጠቁማሉ። ለምሳሌ ኢትዮጵያ የባህር በር የሌላት ሀገር ነች። በዚህም በርካታ ጉዳቶች ያጋጥሚታል።

አሁን ላይ ኢትዮጵያ የተሻለ የባህር ዳርቻ ለማግኘት ጥረት እያደረገች ነው። በአሁኑ ጊዜ ጅቡቲ ለኢትዮጵያ የውጭ ዕርዳታ ዋና ወደብ ሆና እያገለገለች ቢሆንም፤ በአንድ ወደብ ላይ መታመን ግን ውስንነት ያመጣል። አደጋ አለው። በተጨማሪ በአንድ አካል ላይ ብቻ ጥገኛ መሆን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጫናው ከፍተኛ ነው። ኢትዮጵያ ከኤርትራ፣ ጅቡቲ እና ሶማሌላንድ ጋር ፍትሃዊ የወደብ አጠቃቀምን በተመለከተ አማራጮችን እየመረመረች ነው። በተጨማሪም ከኬንያ ጋር ያለው የላሙ ፖርት ከተጠናቀቀ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ።

እንግዲህ የባህር በር ማለት ትርጉሙ ብዙ ከመሆኑም በላይ ጠቀሜታውም በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ለምሳሌ ባህርን በመጠቀም ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ጋር በቀላሉ መገናኘት እንችላለን፤ አብዛኛውን የንግድ ሥራም የሚከናወንበት ነው፤ በትራንስፖርቱ ዘርፍም ብዙ መርከቦች ይጓጓዛሉ። የዓለም ንግድ ዋናው መጓጓዣውም በባህር ላይ ነው። በመሆኑም ወደብ ለሀገራት ወሳኝ ሚና ያለውና እጅግም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው። በዚህ የተነሳም ወደብ ያላቸውና የሌላቸው ሀገራት እኩል ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ከኢትዮጵያ ምድር...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

አቅም የላቸውም። በሌሎች ሀገሮች ወደቦች መጠቀም ከከፍያ ጀምሮ ስምምነት ያስፈልገዋል፤ ስምምነቱ ደግሞ ከፍ ዝቅ የሚል ከሆነ ችግሩ የተባባሰ ይሆናል። ይህ በደንብ ሲታይ አማራጭ ወደብ የግድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ እንደሚባለው የውሃ ማማ ናት? ይህንን ያህል መጠን ያለው ውሃ ያላት ሀገር ከሆነችስ በሀብቷ ምን ያህል ተጠቅማለች ?**

**ዶክተር ያሲን፡-** ሀብቱ ቢኖራትም እስከ አሁን ብዙ ተጠቅማበታለች ለማለት አያስደፍረም። ዓባይን ያየን እንደሆነ ጉዳዩ ሰፊና የብዙዎች ፍላጎት ያለበት ነው፤ ሌላው ባሮ አኮቦ ነው፤ ግን ደግሞ በዚህ ወንዝም አልተጠቀምንበትም። ሌሎች ደግሞ በመጠኑም ቢሆን ለኤሌክትሪክ ማመንጫነት የሚውሉ ወንዞች አሉን። ይህ ቢሆንም የሀብታችንን ያህል ተጠቅመናል ብሎ መናገር የሚቻልበት ሁኔታ ላይ አይደለንም። ካልተጠቀምንበት የውሃ ማማ ነን አይደለንም እያሉ መከራከር ዋጋ የለውም። መሠረታዊው ጉዳይ ያለውን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከላይ እርስዎም እንዳሉት የብዙዎች ፍላጎት ያለበትን ዓባይን ጨምሮ ሌሎች ወንዞች አሉን። አንዳንዶች እንደሚሉት ዓባይን ትተን በሌሎች ውሃዎች እንጠቀም ብንል በቂ ውሃ አለን ብለን መናገር እንችላለን?**

**ዶክተር ያሲን፡-** አንደኛ እና ዋነኛው ነገር የምንጠቀመውም ሆነ የምንተወው እነሱ ስላሉ አይደለም፤ የዓባይን ውሃ በተለይም ሌሎች ጎረቤቶቻችንን ሳንነካ መጠቀም መብታችን እና ሕግም የሚፈቅድልን ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ ምድር ላይ የሚመነጨውን ውሃ በፍትሃዊነት የመጠቀም መብት አለን። አሁን እነሱ የሚሉት ሁሉንም እንደ ቀደመው ጊዜ ብቻችንን አግበስብሰን እንሙት ነው። ያላችሁ ይበቃችኋል ዓባይን ለእኛ ተውልን የሚሉት፤ ከዚህ የተነሳ ነው። እኛ ደግሞ ዓባይን የዓለም አቀፉ ሕግ በሚያዘው መንገድ እንጠቀማለን። ነገር ግን ሀገራችን ላይ ያሉ ውሃዎችን ዝናብን ጨምሮ ደግሞ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን እያፈለቅን በአግባቡ መጠቀም ይገባናል። ይህ በሆነ ልክ ደግሞ ውሃ የስልጣኔና የሀብት ምንጭ መሆኑን እያስመሰከርን እንሄዳለን ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እንደው እስከ አሁን በውሃ ሃብታችን ሳለመጠቀማችን ታሪካዊ ምክንያት ይኖረው ይሆን ?**

**ዶክተር ያሲን፡-** እስከ አሁን እንግዲህ ባለውና አቅም በፈቀደ መጠን ውሃዎቻችንን እያለማን ለተለያዩ ሥራዎች እያዋልን እየተጠቀምን ነው። ነገር ግን ከዚህ በበለጠ ሁኔታ መጠቀም ግን ይቻላልም ይገባልም ማለት እፈልጋለሁ። የውሃ ሀብታችንን በሚፈለገው ደረጃ ላለመጠቀማችን የውስጥ የአቅም ችግር እና ሰፊ የውጭ ተጽዕኖዎች ነበሩብን፤ አሁንም አሉብን። እነዚህን ችግሮች የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም እንዴት ባለው መንገድ ተቆጣጥረናቸው ቀጣዩን ሥራችንን መሥራት እንችላለን በሚለው ላይ በቀጣይ ከፍ ያለ ትኩረትን የሚፈልግ ጉዳይ ነው።

ለምሳሌ ኢትዮጵያ በውሃ ሀብቷ እንዳትጠቀም ካደረጋት የውጭ ጫና መካከል በቅኝ ግዛት ዘመን ቅኝ ገዢዎቹ አፍሪካን ብሎም ኢትዮጵያን ያዩበት መንገድ ነው። በእነሱ እይታ ኢትዮጵያ ወንዞቿንም ሆነ የባህር በሮቿን ከተጠቀመች እጅግ ታድጋለች፤ ተፅእኖ ፈጣሪ ትሆናለች ብለው አምነዋል። በመሆኑም ይህንን ሀብቷን ከተጠቀመች ታድጋለች ብለው በማሰብ፤ ከማሰብ አልፈው እንዳታድግ ለማድረግ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ለማደግ ዋነኛ መሠረት የሚሆነውን የባህር



> **የውሃ ሀብታችንን በሚፈለገው ደረጃ ላለመጠቀማችን የውስጥ የአቅም ችግር እና ሰፊ የውጭ ተጽዕኖዎች ነበሩብን፤ አሁንም አሉብን:: እነዚህን ችግሮች የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም እንዴት ባለው መንገድ ተቆጣጥረናቸው ቀጣዩን ሥራችንን መሠራት እንችላለን በሚለው ላይ በቀጣይ ከፍ ያለ ትኩረትን የሚፈልግ ጉዳይ ነው**

በር እንዳይኖራትም ሆነ የባህር በር እንድታጣ በስፋት ሠርተዋል።

ወንዞቿንም በማልማት ሕዝቡ ተጠቃሚ እንዳይሆን እና ከድህነት እንዳይወጣ ብዙ መንገዶችን በመጠቀም በስፋት ወደኋላ እንድንቀር ማድረግ ችለዋል። በመሆኑም ይህንን ሁኔታ የዘርፉ ባለሙያዎች እንዲሁም ፖለቲከኞች የተለያዩ መንገዶችን እንዲሁም ውይይቶችን በማድረግ ሊፈቱት የሚገባ ነገር ነው ብዬ አስባለሁ።

ሌላው ከውጭ ተፅዕኖ በተጨማሪ የውስጥ ችግራችን ደግሞ እኛው በእኛው የምንፈጥራቸው አንዳንድ መሰናክሎችም ለዘመናት በውሃ ሀብታችን እንዳንጠቀም እንቅፋት ሆነውብናል። በርግጥ ሌሎችም እነዚህ ናቸው ብሎ ለመዘርዘር ሰፋ ያለ ሥራንና ጥናትን ይጠይቅ ይሆናል። ግን በጠቅላላው ያሉብንን ችግሮች ፈተን የውሃ ሀብታችንን በሚገባ መጠቀሙ ላይ ትኩረት ተደርጎ ሊሰራ ይገባል። የውሃ ሀብታችንን በአግባቡ የምንጠቀምበትን ሁኔታ ካሰፋን እና በሀብታችንም በሚገባን ልክ የምንጠቀምበትን ሁኔታ መፍጠር ከቻልን ከድህነት መውጣትም ሆነ ሀገርን ማሳደግ አዳጋች አይሆንም።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያም የባህር በር ለማግኘት የሄደችበት ርቀት እንዴት ያዩታል ?**

**ዶክተር ያሲን፡-** ውሃ እንግዲህ የስልጣኔ መሠረት ነው ካልን፤ የምንጠቀመው ወደብን አማካይ አድርገን ነው። ሀገራችን ለረጅም ጊዜ ወደብ አልባ ሆና ቆይታለች። አሁን ላይ ደግሞ ወደብ ቢኖር ጥሩ ነው በሚል ጥያቄዎች እየተነሱ ናቸው። እኔ በበኩሌ እነዚህን ጥያቄዎች የምመለከታቸው በጣም በጥሩ ሁኔታ ነው። ጥያቄውም መቅረብ ያለበት ተገቢነት ያለው ጥያቄ ነው የሚል እምነት አለኝ።

ይህ ጥያቄ ቀርቦ መልስ ቢያገኝ ምናልባትም ጥቅሙ ለመንግሥት አልያም ለሆነ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያውያን ነው። በመሆኑም ጥያቄውን አግባብ ባለው ሁኔታ ማቅረብና ሥራውንም ከፍ ባለ ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ማስኬድ ደግሞ የሚለከታቸው አካላት ሚናና ኃላፊነት ነው።

በርግጥ የትኛውም ኢትዮጵያዊ ለሀገሩ ማሰብ እና መሥራት አለበት። ኢትዮጵያ ወደብ የምታገኝበት ሁኔታ እንዲኖርም ሆነ በወንዞቿ እንድትጠቀም የማይፈልግ ሰው አለ ብዬ አልገምትም። ምክንያቱም ውሃ የዕድገት መሠረት ነው። ይህንን ትልቅ መሠረት ለመጠቀም ሁኔታዎች ሲመቻቹ ከመቃወም እና ከማደናቀፍ ይልቅ መደገፍ እና ማበረታታት የተሻለ ነው።

ባለሙያዎች ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ኢትዮጵያ በውሃ ሀብት መጠቀም እንድትችል መደገፍ ይጠበቅባቸዋል። ሌላው ሕዝብም ውሃ ለሀገራችን እድገት እጅግ ወሳኝ መሆኑን በመረዳት የሚፈለግበትን ድጋፍ ማድረግ አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- በጠቅላላው የሁሉ ነገር መሠረት ነው የሚባለው የውሃ ጉዳይ መታየት ያለበት በምን መልኩ ነው ይላሉ?**

**ዶክተር ያሲን፡-** ውሃ የሕይወት እና የእድገት መሠረት ነው ካልን ሁሉም አካል ውሃ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይኖርበታል። ይህንን ማድረግ በተቻለ መጠን ደግሞ ውሃችንን ከብክነት ከማዳናችንም በላይ ሰፋ ያለ ጥቅምንም ለማግኘት ያግዛል። ሆኖም ግን በተለይም ወጣቱ ትውልድ ማንበብ ማወቅ የግድ ያስፈልገዋል። ኢትዮጵያ ምን ያህል ወንዞች አሏት? እነዚህን ወንዞች በምን መልኩ መጠቀም ትችላለች? ብትጠቀም ምን ያህል ማደግ ትችላለች? የሚሉትን እና ሌሎችም ጥያቄዎችን ለራሱ በማቅረብ እያነበበ ስለውሃ ሀብት እና ሊሠራበት ስለሚገባበት ሁኔታ ማሰብ አለበት።

ከላይ ደግሞ ቢቻል ልጆች ከአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ጀምሮ ስለውሃ እንዲማሩ በትምህርት ሥርዓት (ካሪኩለም) ውስጥ እንዲገባ መሥራት ያስፈልጋል። በዚህ ደረጃ ባሳወቅናቸው ልክ ደግሞ እያንዳንዷን የምትባክን ውሃ የመቆጣጠር ብሎም ስለውሃ ጥቅምና ጉዳት ይበልጥ የመረዳት አቅማቸው ይዳብራል። በመሆኑም ሁሉም ሰው ለውሃ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይኖርበታል።

ለውሃ ትኩረት ሲሰጥ ዕድገት እንደሚመጣ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ የለም። ምክንያቱም ዓለም ያደገው በውሃ ነው። ውሃ የዓለም ሀገራት የዕድገት መሠረት ነው። ኢትዮጵያ ግን በተቃራኒው አንደኛ የነበራትን ወደቧን አጥታለች። በሌላ በኩል ብዙ ወንዞች ቢኖሯትም በወንዞቿ በአግባቡ እየተጠቀመች አይደለም። እንዳትጠቀም የተለያዩ የውስጥ እና የውጭ ችግሮች ቢኖሩም፤ ችግሮቹን በማወቅ እና መፈታት ያለባቸውንም በአግባቡ በመፍታት መፍትሔ ማምጣት የግድ ነው።

በውሃ ሀብታችን እንዳንጠቀም ሲያደርጉ የቆዩ እንቅፋቶችን ማንሳት እና ችግሮቹን ማቃለል አንደኛው መፍትሔ ነው። ወደብ የሚገኝበትን ዕድል ማስፋት እና ሰፊ የዲፕሎማሲ ሥራ ማከናወን ሌላኛው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዘላቂ ዕድገት እንዲኖር ከታች ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ትውልዱ ውሃን በተመለከተ በጥልቀት እንዲያውቅ መሥራት ያስፈልጋል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም በጣም አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር ያሲን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## የጤናውን ዘርፍ ያሻሻለ የመረጃ ሥርዓት

**አስናቀ ፀጋዬ**

የጤናውን ዘርፍ አገልግሎት ከሚያሳልጡና ከሚያዘምኑ ሥራዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የመረጃ ሥርዓቱን ማሻሻልና ማዘመን ነው። በተለይ ደግሞ የመረጃ ሥርዓቱ ቴክኖሎጂ መር ሲሆን በጤናው ዘርፍ የሚታየውን የውሳኔ አሰጣጥ ክፍተት በመሙላት ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ይሆናል። የአገልግሎት ጥራቱንም ይጨምራል፤ የተገልጋይ ርካታንም ከፍ ያደርጋል።

ለዚህም ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት ኢትዮጵያ በሀገር አቀፍ ደረጃ የጤና መረጃ ሥርዓት አዘጋጅታ ወደሥራ ያስገባችው። ይህ ሀገር አቀፍ የጤና መረጃ ሥርዓት ታዲያ ላለፉት ስምንት ዓመታት የጤና ዳታዎች ሲሰበሰብበት ቆይቷል። የጤናውን ዘርፍ በማሻሻል ረገድም ጥሩ ውጤት እንደተገኘበት ተመስክሯል። በዚህ መነሻነት ይህንኑ የጤና መረጃ ሥርዓት ይበልጥ ለማሻሻል ምክክር ተደርጎበታል።

የአማራ ክልል ጤና ቢሮ በፕላንና ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት ውስጥ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ አቶ ትዛዙ ቢጋር እንደሚሉት፣ ሀገር አቀፍ የጤና ሥርዓቱ /ዲ ኤች አይ ኤስ/ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በክልሉም በሁለት መንገድ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። አንደኛው በኦን ላይን ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት በሚያገኙ ተቋማት ላይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ኦፍ ላይን ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት በማያገኙ ተቋማት ላይ ነው። ከመንግሥት ተቋማት በተጨማሪ በግል ተቋማት ላይም እየተሠራበት ይገኛል።

ይህ የጤና መረጃ ሥርዓት ተግባራዊ መደረግ ከጀመረ በኋላ ከወረቀት አሠራር ወደ ዲጂታል በመግባት ውሳኔ ሰጪ አካላት ወይም ጥናትና ምርምር የሚያደርጉ የተለያዩ አካላት መረጃውን በቀላሉ አግኝተው ለውሳኔ አሰጣጥ ምቹና ቀልጣፋ እንዲሆን አድርጓል። ሁሉም ተቋማት ወይም አገልግሎት ሰጪዎች ክፍተታቸውን በመለየት መገልገልና መጠቀም እንዲችሉ ያደረገ ሥርዓት ነው። በዚህ ረገድም ለውጦች እየታዩ መጥተዋል። በፊት ከነበረው አሠራር አንፃርም በብዙ መልኩ ወጪ ቆጣቢ ሆኖ ተገኝቷል።

ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ መድኃኒቶችን ወይም የሕክምና አገልግሎቶችን በሪፖርት ደረጃ የሚመለከተው አካል በቀላሉ ተደራሽ በማድረግ በዛ መረጃ መሠረት ግብዓት ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የሚያስፈልጉ የሕክምና ግብዓቶችን በቀላሉ ተደራሽ በማድረግ የማሳለጥ ሥራውን ሥርዓቱ ይከውናል። በዚሁ መሠረት መረጃውን በቀላሉ በማግኘት ለእነዛ መረጃዎች በቶሎ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የጤና መረጃ ሥርዓት አገልግሎት ማሳለጫ ሥርዓት ነው።

ይህ ሀገር አቀፍ የጤና መረጃ ሥርዓት ሲያድግ ደግሞ የጤና መረጃ መሰብሰቢያዎች ውስጥ ከዚህ በፊት ያልነበሩ እንደ አዲስ የተካተቱ አብረው በዚህ በሚሻሻለው የጤና መረጃ ሥርዓት ውስጥ ይካተታሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ በፊት ተጠቃሚዎች ሲገለገሉ ሪፖርቱን ለማውጣትና ለመጠቀም እንደ ችግር ሲያነሷቸው የነበሩ ችግሮች ይቀረፋሉ ተብሎ ይጠበቃል። በተጨማሪም የጤናውን ሥርዓት ለሚደግፉ አጋር አካላትና ድርጅቶች መረጃዎችን በማሳለጥ አስፈላጊውን ሪፖርት በሰዓቱ ማድረስ መድረስ የሚያስችልበትን አሠራር በማካተት ከዚህ በፊት የተነሱ ችግሮችን ያሻሽላል ተብሎ ይታሰባል።

አቶ አዳነ ለታ የሀብቴክ ሶሊዩሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። በተጨማሪም ድርጅቱ ከጤና ሚንስቴርና ቢል ኤንድ ሚሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን ጋር በሚሰሩት ፕሮጀክት ላይ የፕሮጀክቱ ዳይሬክተር ሆነው ያገለግላሉ። ሃብቴክ በኢትዮጵያ በአምስት ባለሙያዎች የተመሠረተ ሲሆን አምስቱም ዘርፎች የተለያዩ ልምዶች አሏቸው። በተለይ ሶፍትዌር ማልማት፣ የዳታ ሳይንስ፣ ዳታ አናሊቲክስና ህብረተሰብ ጤና ምርምር ጋር የተገናኘ ልምድ ያላቸው አምስት ባለሙያዎች ድርጅቱን አቋቁመዋል። ድርጅቱ ከተቋቋመም ሁለት ዓመታትን አስቆጥሯል። ነገር ግን ደግሞ በሁለት ዓመታት ጊዜው ውስጥ በርካታ ሥራዎችን ሰርቷል።

በተለይ የሀገር አቀፍ የጤና መረጃ ሥርዓትን ከጤና ሚንስቴር ጋር በመሆን አዘጋጅቷል። ከዚህ በተጨማሪም ዳታን መተንተን፣ የተተነተነውን ዳታ ደግሞ ለውሳኔ ጥቅም እንዲሰጥ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን ለጤና ሚንስቴርና




ሁለተኛው ሀገር አቀፍ የጤና መረጃ ሥርዓት የጤና ሚኒስቴር ኃላፊዎች በተገኙበት ተካሂዷል፣

ለክልል ጤና ቢሮዎች እየሰጠ ይገኛል። ድርጅቱ ሲቋቋም አላማው የጤና ሥርዓቱ ላይ ታማኝ የሆነና የተሰጠውን ሥራ በአግባቡ የሚያደርስ ድርጅት የለም ብሎ አስቦ ነው ድርጅቱ የተቋቋመው። ወደፊት ታማኝና ኃላፊነት የሚጣልበት በተለይ ጤና ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሴክተሮች ዲጂታል ኢትዮጵያን በ2025 እውን ለማድረግና ከዚህ በኋላ የሚመጡትን እንደ አርተፊሻል ኢንተለጀንስ ዓይነት ጋር የተገናኙ ሥራዎችን ይሠራል ተብሎ ይታሰባል። ኢትዮጵያ በዲጂታል ኢኮኖሚ ከፍ እንድትል ይፈለጋል። ለዚህም ደግሞ ድርጅቱ የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል። በዩኒቨርሲቲዎች አካባቢ ያሉ ወጣት የቴክኖሎጂ ባለሙያዎችን በመጠቀም የሀገርን ችግር የሚፈቱ የተለያዩ መፍትሔዎችን ከአብዛኛዎቹ የድርጅቱ አጋሮችና ከሚንስቴር መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆንና በመነጋገር ሥራዎችን ለመሥራት ታስቧል።

ሥራ አስኪያጁ እንደሚናገሩት የሀገር አቀፍ የጤና መረጃ ሥርዓት ፎረም እንደ አንድ የመማማሪያ መድረክ እንዲሆን ይፈለጋል። ፎረሙ ባለፈው ዓመት ይጀመር እንጂ ድርጅቱ ድጋፍ እያደረገ አይቀጥልም። ምክንያቱም ይህ ሀገራዊ ንቅናቄ እንዲሆን ነው ድርጅቱ የሚፈልገው። ጤና ሚንስቴር ከሌሎች አጋር አካላት ጋር መሆን እንዲያስቀጥለው ያስፈልጋል። ሃሳቡ በጤና ሚኒስቴር ደረጃ እንደ የጤና መረጃ ሥርዓት በሀገር ውስጥ የተተገበረ ሥርዓት የለም። ስለዚህ ድርጅቱ ይህ ሥርዓት እንዲቀጥል ይፈልጋል። ለሌሎችም መማሪያ እንዲሆን ይፈልጋል። ይህን ለማድረግ ደግሞ የመማሪያ ፎረም ያስፈልጋል።

ድርጅቱ የመማማሪያ ፎረም ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ስልጠናዎችንም ለጤና ሚንስቴርና ለክልል ጤና ቢሮዎች ባለሙያዎች ይሰጣል። አስራ አራት የሚሆኑ የበቁ ባለሙያዎች በየክልሎች በተለይ የዲ ኤች አይ ኤስ 2 ትግበራን የሚደግፉ ተቀጥረው እየሠሩ ይገኛሉ። አዳዲስ ተመራቂ ልጆችን በማብቃት ሀገራዊ ችግሮችን እንዲፈቱ ማድረግ ነው ድርጅቱ የሚፈልገው። ይህንኑ መድረክ አመቻችቶም ነው እየሠራ የሚገኘው።

ከጤናው ዘርፍ ውጭ ሃብቴክ በሌሎች ሴክተሮችም ውስጥ በቀጣይ ገብቶ የሚሠራ ይሆናል። ሀገር አቀፍ የመረጃ ሥርዓቱ ለጤናው ዘርፍ ብቻ ሳይሆን ለግብርናና ለሌሎችም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችም ሊሰራና ሊያገለግል የሚችል ነው። አሁን ላይ ከሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ጋር ውይይቶች አሉ። በተለይ የኢትዮጵያ ግብርና እድገት እንዲፋጠንና ችግርም እንዳይኖርበት ከተፈለገ እንዲህ ዓይነቱን መረጃ ሥርዓት በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል። ስለዚህ ዲ ኤች አይ ኤስ ለጤናው ዘርፍ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ሴክተሮች ሊሆን ይችላል። ድርጅቱም ያሉትን ባለሙያዎች ተጠቅሞ ዲ ኤች አይ ኤስ 2 ወደ ሌሎች ሴክተሮች ለመውሰድ ጥረት እያደረገ ነው። ስለዚህ ድርጅቱ አሁን በጤናው ዘርፍ ያከናወነው ሥራ ውጤት ወደፊት የሚታይ ይሆናል።

በጤና ሚኒስቴር የዲጂታል ጤና ክፍል አስተባባሪ

**‹‹በስምንት ዓመታት ውስጥ 1 ቢሊዮን የሚሆን ዳታ ተመዝግቧል። ይህን ዳታ እንዴት መጠቀም እንደሚቻልም ከተለያዩ የጤናው ዘርፍ ከተውጣጡ አካላት ጋር ውይይት ተካሂዷል።››**

አቶ ገመቺስ መልካሙ እንደሚናገሩት በጤና ሴክተር ውስጥ ከጤና ኬላ ጀምሮ እስከ ጤና ሚኒስቴር ድረስ የሚሰበሰቡ ዳታዎች አሉ። እነዚህ ዳታዎች ከዚህ በፊት በወረቀት ነበር የሚሰበሰቡት። ነገር ግን ከስምንት ዓመት ወዲህ ከኦስሎ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን ዲ ኤች አይ ኤስ 2 /District Health Information System 2/ የተባለ ሶፍትዌር በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። ሶፍትዌሩ ከወረዳ ጀምሮ ያሉ ዳታዎችን እንዲሰበስብ ተደርጎ የተሠራ ቢሆንም ከጤና ተቋማት ጀምሮ ይበልጥ እንዲሻሻል ተደርጎ ጥቅም እየሰጠ ይገኛል።

ይህ ሀገር አቀፍ የጤና መረጃ ሥርዓት ሥራ ላይ መዋል ከጀመረ ስምንት ዓመት ሆኖታል። እስካሁንም ዳታዎችን እየሰበሰበ ይገኛል። ምን ዓይነት ዳታዎች መሰብሰብ አለባቸው፣ የተሰበሰቡ ዳታዎች ምን ይመስላሉ የሚለውን ለማወቅ ወደ ማዕከል በማምጣት በሶፍትዌሩ ላይ በየዓመቱ ውይይት ይደረግበታል። በሶፍትዌሩ ብቃት፣ በሚይዛቸው ዳታዎች፣ ለውሳኔ አሰጣጥ አመቺነት ላይ ውይይት ይካሄዳል። በስምንት ዓመታት ውስጥ 1 ቢሊዮን የሚሆን ዳታ ተመዝግቧል። ይህን ዳታ እንዴት መጠቀም እንደሚቻልም ከተለያዩ የጤናው ዘርፍ ከተውጣጡ አካላት ጋር ውይይት ተካሂዷል።

እንደ ሀገር በሁሉም የመንግሥት ተቋማት በተለይ የመብራትና የኢንተርኔት አገልግሎት ያላቸው በቀጥታ ከተቋማቸው ዳታውን ሰብስበው ማስገባት ይችላሉ። የተወሰኑ የግል ተቋማት፣ ትላልቅ ሆስፒታሎችም የጤና መረጃ ሥርዓት ሶፍትዌሩን ተግብረዋል። በጤና ጣቢያ ደረጃ 3 ሺ 600 አካባቢ የሚሆኑ ጤና ጣቢያዎች ሶፍትዌሩን ተግበረዋል። 400 የመንግሥት ሆስፒታሎችም እንዲሁ ሶፍትዌሩን ተግብረዋል። የግል ሆስፒታሎች እንዳዛው ተግባራዊ አድርገዋል።

ከዚህ ውጭ በወረዳ የሚገኙ ጤና ቢሮዎች በሶፍትዌሩ አማካኝነት ዳታዎችን ሪፖርት ያደርጋሉ። የዞንና የክልል ቢሮዎችም በተመሳሳይ ዳታዎችን በዚህ ሲስተም አማካኝነት ይልካሉ። ሁሉም የጤና ተቋማት በዚህ ሥርዓት ውስጥ ገብተዋል። የጤና መረጃ ሥርዓቱ በትንሹ 35 የሚሆን ተጠቃሚ አለው።

እንደ አስተባባሪው ገለፃ እስካሁን ባለው ሂደት ዳታው በመረጃ ሥርዓቱ አማካኝነት ሪፖርት የሚደረገው ከወረቀት ላይ ተሰብስቦ ነው። ነገር ግን በቀጣይ ከየክፍሉ ዳታውን በመሰብሰብ ጥራት ያለው ዳታ ወደ ጤና መረጃ ሥርዓቱ የሚገቡበት አሠራሮች እየተከናወኑ ይገኛሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ከአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ጋር በማገናኘት የሚሰራበት ሁኔታ ላይም ጥናቶች እየተካሄዱ ነው። ስለዚህ በዚህ መሠረት ምን ያህል ታካሚዎች ወደ ሆስፒታል መጥተዋል፣ ምን ያህሎቹ ቲቢና ወባ አለባቸው፣ ምን ዓይነት መድኃኒት ታዞላቸዋል የሚለውን የስምንት ዓመት 1 ቢሊዮን ዳታ ተሰብስቧል።

ይህን ዳታ በአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ተጠቅሞ የሕክምናና የመድኃኒት አገልግሎት በትክክል አግኝተዋል፣ የትኞቹ በሽታዎች ናቸው እንደሀገር ላለፉት ስምንት ዓመታት የነበሩት የሚለውን ማየት የሚያስችል ሥራ መሥራት ይቻላል። ስለዚህ የዳታ አጠቃቀሙን ለማህበረሰቡና ለአጥኚዎች ጥቅም በሚሰጥ መልኩ እየተሠራ ነው።

ከዚህ በፊት በጤናው ዘርፍ ውሳኔዎች የሚሰጡት ከወረቀት በሚሰበሰቡ መረጃዎች ነበር። አሁን ግን በጤናው ዘርፍ በሁሉም ደረጃዎች ላይ የሚገኙ የሥራ ኃላፊዎች በቀላሉ ዳታ ማግኘትና ውሳኔዎችን፣ ማሳለፍ ይችላሉ። በዚህም ይህ ሀገር አቀፍ የጤና መረጃ ሥርዓት የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን አሻሽሏል። ተቋማትም የመታየት እድላቸው ጨምሯል። ያ ማለት አንድ ጤና ጣቢያ ምን እንደሚሠራ በሀገር አቀፍ ደረጃ መታየት ጀምሯል። የውድድር መንፈስ ይፈጥራል፤ የተሻለ ሥራ እንዲሠራ ያደርጋል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ ውጤታማ የሆነው ማህበር

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከሚያበረክተው የቡና ልማት የበለጠ ተጠቃሚ መሆን የሚያስችሉ ተግባሮች እየተከናኑ ይገኛሉ። የቡና ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲሁም የኤክስፖርት ንግዱን ማሻሻል ሀገር ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ውጤት እንድታገኝ ያስችላታል። በመሆኑም ከታች ከልማቱ ጀምሮ በቡና አዘገጃጀትና በኤክስፖርት ንግድ የተለያዩ ጥረቶች ይደረጋሉ። ይህ የቡና ልማትና ግብይት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንዲችል አርሶአደር ላይ መሥራት የግድ እንደሆነ ይታመናል።

የቡና ምርትና ምርታማነት ሲያድግ የኤክስፖርት መጠንም በዚያው ልክ ከፍ እንዲል መስራት ይገባል። ለዚህም የሀገሪቱን ቡና በዓለም ገበያ ለማስተዋወቅና የውጭ ምንዛሪ ግኝቱን የበለጠ ለማሳደግ ብዙ መሥራት ይጠበቃል። የቡና ባለቤት የሆነው አርሶ አደር ቡናውን በጥራት አዘጋጅቶ ለውጭ ገበያ እንዲያቀርብ የተለያዩ የድጋፍና ክትትል ስራዎች እንዲሁም ማበረታቻዎችን ማድረግ ያስፈልጋል ። ለዚህም ነው መንግሥትን ጨምሮ የተለያዩ በቡናው ዘርፍ የተሰማሩ የግል ድርጅቶች የቡና ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር፣ በጥራት እንዲመረትና እንዲዘጋጅ የተለያዩ ድጋፎችን የሚያደርጉት።

የኢትዮጵያን ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ ለማስተዋወቅና የተሻለ ገበያ እንዲያገኝ ከሚሠሩ ድርጅቶች መካከል "ኦርጋኒክ ፌር ትሬድ" የተባለ ዓለም አቀፍ ድርጅት አንዱ ነው። የድርጅቱን መስፈርት አሟልተው ሰርተፊኬት ያገኙ ማህበራት፣ ዩኒየኖችና የግል ቡና አምራቾች በየዓመቱ የቡና ቅምሻ ውድድር እንዲያደርጉ በመስራት ምርጥ አሰራሮችን በመለየት ቡናቸውንና እነሱን በዓለም ገበያ ያስተዋውቃል። ይህም የኢትዮጵያ ቡና ዓለም አቀፍ ገበያውን ሰብሮ እንዲገባና የተሻለ ዋጋ እንዲያገኝ ያደርጋል።

የዕለቱ የስኬት ዝግጅታችንም "ከኦርጋኒክ ፌር ትሬድ" ዓለም አቀፍ ድርጅት ዕውቅና ካገኙ ህብረት ሥራ ማህበራት መካከል አንዱ በሆነው በሲዳማ ቡና አምራች የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር ላይ ትኩረት አድርጓል። ማህበሩ ቡናቸው ተወዳድሮ "የኦርጋኒክ ፌር ትሬድ "የዕውቅና ሰርተፊኬት ካገኙ ቡና አምራች ህብረት ሥራ ማህበራት መካከል አንዱ ነው። ኦርጋኒክ የሆነ ጥራት ያለው ቡና አምራች የሆነው ማህበሩ፣ በዘንድሮው ኦርጋኒክ ፌር ትሬድ" ዓለም አቀፍ የቡና ቅምሻ ውድድር ተሳትፎ የአምስተኛነት ደረጃን ይዟል።

የሲዳማ ቡና ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር ፕሮጀክትና ሰርተፊኬሽን አስተባባሪ አቶ ኤርሚያስ ደስታ እንዳሉት፤ ማህበሩ ስፔሻሊቲ ቡና ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ በመሆኑ የሲዳማ አካባቢ ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ እጅግ ተፈላጊና ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ ችሏል። ቡናው ከምርት ጀምሮ በጥራት የሚዘጋጅና ተፈጥሯዊ ጣዕሙን እንደጠበቀ ለዓለም ገበያ የሚቀርብ በመሆኑም የተሻለ ዋጋ የሚያወጣ በማውጣት ጠቀም ያለ የውጭ ምንዛሪ ያስገኛል።

አቶ ኤርሚያስ እንዳብራሩት፤ የሲዳማ ቡና ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር በ1993 ዓ.ም በ12 አባላትና በ36 ሚሊዮን መነሻ ካፒታል ነው የተመሰረተው። ማህበሩ አሁን ላይ 67 ማህበራትና ከአንድ መቶ ሺ በላይ አባላትን ማፍራት ችሏል።

ማህበሩ በሁለት የተከፈለ ነው፤ በአሁኑ ወቅት 41ዱ ማህበራት "በፌር ትሬድና ኦርጋኒክ" ሰርተፊኬት አግኝተዋል፤ ቀሪዎቹ 26 ማህበራት ደግሞ "የፌር ትሬድ ኦርጋኒክ" ምስክር ወረቅትን ለማግኘት እየሠሩ ይገኛሉ። ቡናን በጥራት በማምረት "የፌር ትሬድ ሰርተፊኬት" ያገኙት 41 ማህበራትም ከ72 ሺ በላይ አባላት አሏቸው።

የማህበሩ አባላት በቡና ጥራት ላይ እየሠሩ እንደሆነ የገለጹት አቶ ኤርሚያስ፤ ከጥራት ባለፈ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግም እንዲሁ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ ሲሉ ይገልጻሉ። በተለይም በአለም አቀፉ "ኦርጋኒክ ፌር ትሬድ" ዕውቅናን ያገኙ ማህበራት ከድርጅቱ የሚያገኙት ማበረታቻ በመኖሩ ተነሳሽነታቸውን ጨምሯል ነው ያሉት። የሲዳማ ቡና ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በየጊዜው የምርት መጠንና ጥራት እየጨመረ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ማህበሩ ስፔሻሊቲ ቡና ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ እንደመሆኑ ሥራው ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል። ገዢ አገራት ውል የሚገቡት ቡናው እንዴት እንደሚመረት፣እንዴት እንደሚዘጋጅና ቀጣይነት ያለው የእሴት ሰንሰለት መኖሩን እያረጋገጡ ነው። ለእዚህም ምርታማነትና ጥራት ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት የግድ ይሆናል። አንድ ዓመት ልኮ ቀጣይ ዓመት ላይ አለመላክ አይቻልም። ከደንበኞች ጋር በሚኖር የውል ስምምነት መሰረት በየዓመቱ የሲዳማ ስፔሻሊቲ ቡና ለደንበኞቹ ይቀርባል።

ማህበሩ ስፔሻሊቲ ቡናን ለረጅም ጊዜ ደንበኞቹ ማቅረብ በመቻሉ ቡናውን ተደራድሮና ከዓለም አቀፍ ዋጋ በበለጠ ከፍ አድርጎ የመሸጥ ዕድል አለው። ከዚህ በተጨማሪም "ከኦርጋኒክ ፌር ትሬድ" የዕውቅና ሰርተፊኬት ያገኘ በመሆኑና በዚህም ቡናውን በዓለም አቀፍ የገበያ ዋጋ ከፍ አድርጎ ከመሸጥ ባለፈ በኪሎ ከ20 እስከ 40 ሳንቲም ጭማሪ ያገኛል። አብዛኞቹ ገዢ አገራት የሚፈልጉት ቡና የፌር ትሬድ የዕውቅና ሰርተፊኬት ያገኘና ኦርጋኒክ ቡና በመሆኑ ማህበሩ ትልቅ የገበያ ዕድል ተፈጥሮለታል።

እሳቸው እንዳሉት፡- በአሁኑ ወቅት የሲዳማ ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ በመሆን የተሻለ ዋጋ እያገኘ ነው። የምርትም፣ ኤክስፖርት መጠኑም ከዓመት ዓመት እየጨመረ መጥቷል፤ ለዚህም የኦርጋኒክ ፌር ትሬድ ዓለም አቀፍ ድርጅት አባል መሆኑና የዕውቅና ሰርተፊኬት ማግኘቱ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቶለታል። ማህበሩ ከአባላቱ የሚሰበስበውን ቡና በየዓመቱ ለውጭ ገበያ እያቀረበ ሲሆን፤ አዳዲስ ገዢ ሀገራትም የሲዳማ ቡናን ምርጫ እያደረጉ ነው።

ማህበሩ ከአባላቱ የሰበሰበውን ቡና በራሱ ማበጠሪያና መፈልፈያ ማሽን አዘጋጅቶ ወደ ውጭ ገበያ ኤክስፖርት ያደርጋል። በአብዛኛው ለአሜሪካና አውሮፓ ገበያዎች ቡናውን ያቀርባል።

አመታዊ የኤክስፖርት አቅሙም ከአራት ሺ እስከ አምስት ሺ ቶን እንደሆነ አቶ ኤርሚያስ አስታውቀዋል። በውጭ ምንዛሪ ግኝቱም ከ20 እስከ 25 ሚሊዮን ዶላር ገቢ እንደሚያስገኝ ጠቅሰው፤ ከዚህ የተሻለ ገቢ ለማግኘት ቡናን በጥራት አምርቶና አዘጋጅቶ ለዓለም ገበያ ማቅረብ እንደሚገባው አስታውቀዋል፤ ለዚህም አርሶ አደሩ ላይ በመሥራት ተነሳሽነቱን ከፍ ማድረግ አለበት ባይ ናቸው።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ በ2016 በጀት ዓመት ማህበሩ አራት ሺ ሜትሪክ ቶን ቡና ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ ዕቅድ ይዞ እየሠራ ሲሆን፤ ከዚህም ከ22 እስከ 25 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት ይችላል። የውጭ ምንዛሪ ገቢ ግኝቱን ተደራድሮ የሚሸጥበትን ዋጋም ማህበሩ ይወስናል፤ ዘንድሮ የተመረተው ቡና በተወሰነ መጠን ቅናሽ ማሳየቱን አቶ ኤርሚያስ ጠቅሰው፣ እንዲያም ሆኖ ግን ስፔሻሊቲ ቡና ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ በመሆኑ እስከ 25 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ይጠበቃል ሲሉ አስረድተዋል።

አርሶ አደሩ ያመረተውን ቡና በማህበራቱ አማካኝነት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ሆኖ መሸጥ መቻሉ ትልቅ ጥቅም እያስገኘለት ነው ያሉት አቶ ኤርሚያስ፤ ማህበሩ የሚያገኘውን ትርፍም እንዲሁ ለአባላቱ በማከፋፈል የአባላቱን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ ነው ብለዋል። ለአብነትም ባለፈው ዓመት ብቻ ከ180 ሚሊዮን ብር በላይ የትርፍ ትርፍ ክፍያ በማድረግ ለአባላቱ ማከፋፈል መቻሉን አስታውሰዋል። ይህም ቡናው በዓለም አቀፍ ገበያ ተዋውቆ በተሻለ ዋጋ መሸጥ በመቻሉ የተገኘ ውጤት መሆኑን አስታውቀው፣ ማህበሩ በአካባቢው በሚሰራቸው የተለያዩ የልማት ሥራዎቹ አርሶ አደሩን ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑንም አመላክተዋል።

እንደ አቶ ኤርሚያስ ማብራሪያ፤ አብዛኛው የሲዳማ ክልል አርሶ አደር ቡና አምራች እየሆነ መጥቷል ።በቀድሞው ሲዳማ ዞን በአሁኑ ሲዳማ ክልል የሚገኙ ወይናደጋማ አካባቢዎች ጭምር አሁን ላይ ቡና በስፋት ይመረትባቸዋል። ዳራ፣ ዳሌ፣ ጩኮ፣ በንሳ፣ ጭሬና ሌሎች የክልሉ ወረዳዎች ቡና እንደሚመረትባቸው አቶ ኤርሚያስ ጠቁመዋል። የሲዳማ ቡና አምራች ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር የተመሰረተውም በእነዚሁ ቡና አብቃይ አካባቢዎች በሚገኙ አባል አርሶ አደሮች መሆኑን ተናግረዋል።

በየወረዳው የሚገኙ አባል አርሶ አደሮች የሚያለሙትን ቡና ለማህበራት በመሸጥ ማህበሩም ከአርሶ አደሩ የሰበሰበውን ቡና አጥቦና አድርቆ በማዘጋጀት ለዩኒየኑ እንደሚያስረክብ የገለጹት አቶ ኤርሚያስ፤ ዩኒየኑም ገበያ አፈላልጎ ቡናውን ወደ ውጭ ገበያ እንደሚልክ አጫውተውናል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ህብረት ሥራ ማህበሩ ለአርሶ አደሩ የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ቡናን በጥራት ማምረት እንዲችል ድጋፍና ክትትል ያደርጋል። አርሶ አደሩም ስልጠናውን ተግባራዊ በማድረግ ከዓመት ዓመት አበረታች ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል።

በመሆኑም በ36 ሚሊዮን ብር የተመሰረተው የሲዳማ ቡና ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር በአሁኑ ወቅት የካፒታል መጠኑ አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ደርሷል። ካፈራቸው ሃብቶች መካከልም ሀዋሳ ከተማ መናኸሪያ አካባቢ የገነባውና ወደ ስራ ያስገባው ትልቅ ህንጻ አንዱ ሲሆን፣ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሁለት የኤክስፖርት ቡና ማዘጋጃ ጣቢያዎችንም ገንብቷል። በእነዚህ ጣቢያዎች እና አጠቃላይ በኤክስፖርት ግብይት ዙሪያ ተሳታፊ ለሆኑ 36 ሠራተኞችም የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል።

የሲዳማ ቡና አምራች ገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር አርሶ አደሩ ቡናውን በተሻለ ዋጋ መሸጥና ከቡናው የበለጠ ተጠቃሚ መሆን እንዲችል ድጋፎችን እንደሚያደርግ የገለጹት አቶ ኤርሚያስ፤ ቡናውን ለሚገዙ ማህበራት የፋይናንስ አቅርቦቱን በማስፋት ማህበራቱ ከማህበሩ ብድር ወስደው ቡናውን ከአምራቹ መግዛት የሚችሉበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል ነው ያሉት። በዚህ የተነሳም ማህበራቱ ብድር ፍለጋ ወደ ባንክ አይሄዱም ያሉት አቶ ኤርሚያስ፣ ማህበሩ ራሱ ባንክ ሆኖ በማገልገል ከወለደ ነጻ ብድር ያቀርብላቸዋል ብለዋል።

ማህበራቱ ቡናውን ከአርሶ አደሮቹ ሲገዙ አርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ባረጋጋጠ መንገድ መሆኑንም በመግለጽ፤ አንድ ኪሎ ቀይ ቡና ለሚያቀርብ አንድ አርሶ አደር ከመደበኛ ዋጋው በተጨማሪ ማህበራቱ ከአምስት እስከ አስር ብር ተጨማሪ ክፍያ ይከፍላል ብለዋል። ይህም የሚፈጸመው አርሶ አደሩን ለማበረታታትና ተነሳሽነቱን ለመጨመር እንደሚረዳ ጠቅሰው፣ ማህበሩም ከማህበራቱ የሰበሰበውን ቡና በጥራት አዘጋጅቶ ገበያ በማፈላለግ ለውጭ ገበያ ሲያቀርብ የሚያገኘው ትርፍ በመኖሩ ነው ብለዋል። ከሚያገኘው ትርፍ እያንዳንዱ አባል አርሶ አደርም እንዲሁ ተከፋይ መሆኑን አስረድተው፤ ይህም ማህበሩ የቡና ባለቤት የሆነውን አርሶ አደር ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ እየሰራ ለመሆኑ ማሳያ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ማህበራቱ በሚያገኙት የትርፍ ክፍያም ከማህበሩ ጋር በአካባቢው የልማት ሥራዎችን የሚሠሩ ሲሆን፤ ከሚሠሯቸው የልማት ሥራዎች መካከልም ትምህርት ቤቶች፣ መንገድ፣ ድልድይ፣ የጤና ተቋማት፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃና የመብራት ዝርጋታ ይገኙበታል። እነዚህን የልማት ሥራዎች ለአካባቢው በመሥራት ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ። ማህበሩ ከእነዚህ ስራዎች በተጨማሪ ማህበሩን ተጠቃሚ በሚያደርጉ ስራዎች ላይ "ከፌር ትሬድ አፍሪካ "ጋር በመተባበር እየሠራ ይገኛል። ለአብነትም ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዎችን ለአካባቢው ማህበረሰብ በማቅረብ የአርሶ አደሩን የኑሮ ጫና እያቀለለ የሚገኝ ትልቅ ፕሮጀክት ዕውን ተደርጓል።

የአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት በመጠበቁ በአካባቢው የቡና ምርትና ምርታማነት እየጨመረ ነው ያሉት አቶ ኤርሚያስ፤ አርሶ አደሩ የቡና ልማቱን እያስፋፋ ጥራትም ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል። በዚህም የምርት መጠኑ እያደገና ተነሳሽነቱም እየጨመረ መምጣቱን ገልጸዋል። በቀጣይም አርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነትን እንዲያሳድግና ጥራት ያለው ቡና እንዲያመርት ከማድረግ ባለፈ ቡናን በጥሬው ለዓለም ገበያ ከማቅረብ በተጨማሪ እሴት ጨምሮ በማዘጋጀትና ወደ ውጭ ገበያ በመላክ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት አቅዶ እየሠራ ነው ሲሉ አቶ ኤርሚያስ ጠቁመዋል።



አቶ ኤርሚያስ ደስታ

ማህበሩ ከአባላቱ የሰበሰበውን ቡና በራሱ ማበጠሪያና መፈልፈያ ማሽን አዘጋጅቶ ወደ ውጭ ገበያ ኤክስፖርት ያደርጋል:: በአብዛኛው ለአሜሪካና አውሮፓ ገበያዎች ቡናውን ያቀርባል

## ተናጋሪው ዶሴ

# የቅናት ዛር

አስመረት ብስራት



ይወዳታል ከልቡ። ፍቅር እንዲህ ከሆነ በአፍንጫዬ ይውጣ በሚባል ልክ ያፈቅራታል፡፡ ፍቅር መገለጫው ሳይገባው ግን ያፈቅራታል። ዓይኑ ስር ሆና ምን እያሰበች ይሆን ብሎ በቅናት የሚቃጠል ዓይነት ሰው ነው። በሁለቱ መካከል ያለው የእድሜ ልዩነት ግን ፍቅሩን በአግባቡ እንዳያጣጥም አድርጎታል።

አይደለም ወጣ ገባ ብላ ቤት ውስጥም ብትሆን አምሮባት ሲመለከት በቅናት እርር ድብን ይላል። የመዋደድ ሚዛኑ ግራ ገብቶት በስጦታ እያንበሸበሸ ሚስቱን የሚቀጠቅጠው አባ ወራ አሁንም ለዱላው ምክንያት አድርጎ የሚያቀረብው ይህንኑ ፍቅር ነው። ቅናት በተቃራኒ ፆታ ግንኙነት ውስጥ በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር የሚችል ቢሆንም ለእርሱ ግን የሚወደውን ሰው ከማጣት ጋር የተያያዘ የስጋት እና ሽብር ስሜት ፈጥሮበታል፡፡ ለዚህም ይመስላል እራሱ ገዝቶ አልብሶ ለብሳ ሲመለከታት ተናዶ ወደ ዱላ የሚገባው።

ፍቅር መልካም ስሜት ሊፈጥርበት ሲገባው በሽብር ስሜት ይሰቃያል። ይህ በተለያዩ ምክንያቶች ቢፈጠርበትም የፍቅሩን ጫና እያሰበ በቀላሉ ሊያልፈው ሲታገል ሰነባብቷል። በፍቅሯ የወደቀላትን ልጅ እጁ ካስገባም በኋላ ምንም ልቡ ሊያረፍለት አልቻለም።

ወዳና ፈቅዳ የትዳር አጋሩም ብትሆን ቅሉ የእርሱ ልብ ግን ትታኝ ትሄዳለች በሚል ስጋት ተወጥሮ ትኩሱን ፍቅሩን እንዳያጣጥም እግር ከወርች አስሮታል። ይህ የቅናት ስሜት በሚፈጠርበት ወቅት ስሜቱን ለመግለፅ ቃላትን ሳይሆን ጉልበትን መጠቀም እንዲጀምር አድርጎታል። በግልፅ ስለጉዳዩ ከመወያየት ይልቅ ባለቤቱ ላይ ለዱላ ሲጋበዝ መታየት የተለመደ ሆነ፡፡

ቤት ውስጥ ተቀምጣ የምትውለው የትዳር አጋሩ ‹‹ምን እያደረገች ይሆን?›› በማለት ቀኑን ሙሉ እየተብሰለሰለ መዋል አልፎ ተርፎም ቀኑን ብቻ ሳይሆን ሌሊትም ኮርኒስ እየቆጠረ ነገር መብላት ሥራው ሆነ።

የእሱ የቅናት ስሜት ከፍቅር የመነጨ ሳይሆን ከእምነት ማጣት የመጣ እንደሆነ መረዳት ተስኖታል፤ እሷም ለትዳር አጋሯ ውሎዋን ለመናገር ወይም አንተ በሌለህበት ሰዓት የተፈጠሩ ነገሮችን እነዚህ ናቸው ማለት ከብዷታል።

በቅናት ምክንያት ባለቤቷ ለምግብ ያለው ፍላጎት ቀንሷል። እሷም በእርሱ ምክንያት ጭንቀት ውስጥ ከገባች ሰነባብታለች። ባለቤቷ ወደቤት ሲገባ እንደ መደሰት ፈንታ በጭንቀት የልብ ምቷ የሚጨምርበት ሁኔታ ተፈጠረ።

እሱን ስታይ በጭንቀት ከልክ በላይ ያልባት ገባ። ጭንቀቱ ነው መስል ቶሎ ቶሎ መድከምም መገለጫዋ ሆነ። በመጨረሻም ቅናት ከትዳር አጋሯ ጋር ያላት ግንኙነት ላይ ክፍተት እየተፈጠረ መጣ፡፡

አባወራው ይሄ ቅናት የዕለት ተዕለት ኑሯቸው ጋር እየተጋጨ መሆኑን ቢረዳም የሚያፈቅራትን ሴት እያሳዘነ እና እየጎዳ እንደሆነ ቢገነዘብም ቅናቱ እርሱ ራሱን ከምቆጣጠረው በላይ እሱ ተቆጣጥሮት ነበር።

የባልየው ቅናት ባለቤቱ በሥራ ብዙ ሰዓቷን የምታሳልፍ ወይንም ብዙ ጊዜዋን በማንበብ የምታሳልፈው ሆን ብላ ከእኔ ለመራቅ ብላ ነው በማለት በቅናት እርር ድብን ሲል ይታያል፡፡ በቅናቱም ምክንያት የፍቅር ግንኙነቱን እየሻከረ መምጣት ጀመረ።

ሰውየው ‹‹እርር ድብን ማለት አንገሽግሾኛል፤ ጨጓራዬን ልተፋው ነው፤ አንድ በሉኝ›› በማለት ወዳጅ ዘመዱን ቢያማክርም ምንም ዓይነት መፍትሔ ሊያገኝ አልቻለም። ውስጥ ውስጡን እየበላ ከቁጥጥር ውጭ ያደረገው ቅናትን ፈፅሞ ልያጠፋው አለመቻሉ ከብዶታል።

የሚገርመው የአስራ አምስት ዓመት ሴት ልጁም ውጭ ቆይታ ከመጣች ከእናቷ ባልተናነሰ ሁኔታ ይቀጠቅጣታል። ከሁሉ በላይ "እንደ እናትሽ መሆን ፈለግሽ ?" እያለ የሚያወጣው የስድብ ቃል አፍላዋ ልጁ ጀርባዋን እንድትሰጠው ካደረጋት ሰነባብቷል። የልጅና የእናትዬው በሁኔታው መሰላቸትና ውጭ ውጭ ማለት ይበልጥ እያሳበደው ራሱን መቆጣጠር የማይችልበት ደረጃ አደረሰው።

### አስከፊው ቀን

በትዳር በርካታ ዓመታትን አሳልፈዋል። የባልዬው አመል ከሠርጉ ቀን አንስቶ የነበረ ቢሆንም እለት እለት ተግተው ለፍተው ያፈሩት ጥሪት ሲበረክት ቤታቸው በሀብት ሲሞላ አናኗራቸው ሲቀየር ቅናቱ ተባብሶ ቀጠለ። ዘይኑ ፈረጃ ምራ ይባላል። ይህ ሰው ሚስቴ ትታኝ ልትሄድ ነው በሚል ምክንያት ጥቅምት 6 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ላይ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ቤቴል ወይራ ሰፈር አካባቢ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በር ላይ የትዳር አጋሩ ጋር ፀብ ውስጥ ይገባል።

ይህች የትዳር አጋሩ የሆነችውን ወይዘሮ ጀሚላ ሰኢድ መኪና ውስጥ ተቀምጣ እያለ ነበር ባል ሌላ ባል አግብተሽ ልጆቹን ይዘሽ ወደ ውጭ ልትሄጂ ነው እያለ መጮህ የጀመረው። በኃይለ ቃል ሲናገር የቆየው ባልም በእጁ ይዞት የነበረውን የምንጣፍ መቁረጫ እያሳየ በዚህ ቆራርጬ ነው የምጥልሽ እያለ ይጮህ ነበር።

በመቀጠል እጁን ወደ መኪናው ጋቢና በማስገባት እንዳትጮህ አፏን ካፈናት በኋላ ከተር እየተባለ በሚጠራ ስለታማ የምንጣፍ መቁረጫ የተለያዩ የሰውነት አካሏን በመውጋት ከፍተኛ ጉዳት አደረሰባት። ከዛ በኋላ ከመኪና ውስጥ ጎትቶ በማውረድ መሬት ላይ ጥሏት በወደቀችበት በያዘው ስለት ጀርባዋን እና ትከሻዋን ደጋግሞ በመውጋት የግድያ ሙከራ በማድረስ ሊያመልጥ ሙከራ አደረገ።

### የአባትና ልጅ ጦርነት

አባትዬው ከእናቷ ጋር በተጣላ ቁጥር ልጁን የንዴት ማብረጃ ማድረግ ከጀመረ ሰነባብታል። ልጅቷን በሰብበ አስባቡ የሚቀጠቀጣትም ቢሆን እናት ገበናዋን ለመሸፈን በሚል ልጁን እያባበለች ነገሩ ከቤታቸው ውጭ እንዳይሰማ ስታደርግ ቆይታለች።

የትዳሯ ህልውና እንዳይናጋ በተቻላት መጠን መልካም ነገሮችን በጥንቃቄና በትእግስት እያደረገች ብትቆይም ምንም ዓይነት የባህሪ መሻሻል ባለቤቷ ላይ መመልከት አልቻለችም ነበር። ከሁሉ በላይ ገና ሮጣ ያልጠገበች ሴት ልጃቸው ላይ የሚያደርገው ነገር ትእግስቷን እያስጨረሳት ነው።

በታኅሣሥ 14 ቀን 2014 ዓ.ም ቀኑን ሙሉ ሚስቱን እየተከተለ በነገር ሲሸነቁጣት የዋለው ባል በግምት ከቀኑ 9፡30 አካባቢ ሲሆን መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ የ15 ዓመት ልጅ የሆነችው ልጃቸውን ከትምህርት ቤት ስትመለስ አርፍደሻል በሚል ምክንያት በመጥረጊያ እንጨት እና በመጋረጃ መስቀያ ብረት ደጋግሞ በመምታት እጇ፣ ጭንቅላቷ እና እግሯ እንዲያብጥ አድርጓት የነበረ ቢሆንም የሆዳቸውን በሆዳቸው ይዘው በሰላም መኖር ጀምረው ነበር።

በተመሳሳይም በነሐሴ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት አካባቢም ይህች የ15 ዓመት የሆነችው ልጁ ያለምንም ምክንያት በኤሌክትሪክ ገመድ ጀርባዋ እና እግሮቿን ደጋግሞ በመምታት ጀርባዋ እና እግሮቿ እንዲቆስሉና እንዲያብጡ አድርጓትም ነበር።

እናትና ልጅን በየተራ ሲያሰቃይ የቆየው ባልና አባት ለቤተሰባቸው ደህንነት ሲሉ በዝምታ የሚያልፉትን ሚስትና ልጁን መቀጥቀጥ መብቱ እንደሆነ በማድረግ ሲያደርስ የነበረው ድብደባ አልበቃ ብሎት ባለቤቱን ክፉኛ በማቁሰል ከአካባቢው ይሰወራል።

### የፖሊስ ምርመራ

ወይዘሮ ጀሚላ ክፉኛ ቆስለው ሆስፒታል መግባታቸውን የሰማው ፖሊስ በመኖሪያ ቤታቸውና ወይዘሮዋ በተኙበት ሆስፒታል ባደረገው ምርመራ መሠረት የገዛ ባለቤታቸው ጉዳቱን በማድረግ የተሰወረ መሆኑን ይረዳል። ፖሊስ ወንጀለኛው መሰወሩን ከሰማ በኋላ በክትትል ተይዞ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶበት እንዲቀርብ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል።

ተጠርጣሪው በሕዝብና በፀጥታ ኃይሎች ርብርብ በቁጥጥር ሲል ቢውልም "የተፈጠረው ተራ ግጭት እንጂ በዚህ ልክ እኔ ጉዳት አላደረስኩም" በማለት የእምነት ክህደት ቃል ቢሰጡም፤ የዓይን አማኞች ምስክርነት፤ የተበዳዮች ቃልን በመቀበል ሰውዬው ለፈፀመው ወንጀል ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኝ ለማድረግ ፖሊስ መረጃውን አጠናቀረ።

መረጃውንና ማስረጃውን በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በማቅረብም ወንጀለኛው ክስ እንዲመሰረትበት አደረገ።

### የዐቃቤ ሕግ ክስ ዝርዝር

በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በወ/ሕ/አ በ27/1/ እና 539/1/ሀ/ እንዲሁም በወ/ሕ/አ 556/2/ሀ እና /ሐ/ ላይ በተደነገገው መሠረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ያቀረበው የክስ ዝርዝር።

ዘይኑ ፈረጃ ምራ የተባለ ተከሳሽ ጥቅምት 6 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ቤቴል ወይራ ሰፈር አካባቢ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በር ላይ የትዳር አጋሩ የሆነችውን የግል ተበዳይ ጀሚላ ሰኢድ መኪና ውስጥ ተቀምጣ እያለ ሌላ ባል አግብተሽ ልጆቹን ይዘሽ ወደ ውጭ ልትሄጂ ነው በሚል ምክንያት ቆራርጬ ነው የምጥልሽ እያለ እጁን ወደ መኪናው ጋቢና በማስገባት እንዳትጮህ አፏን ካፈናት በኋላ ከተር እየተባለ በሚጠራ ስለታማ የምንጣፍ መቁረጫ የተለያዩ የሰውነት አካሏን በመውጋት ከፍተኛ ጉዳት ካደረሰ በኋላ ከመኪና ውስጥ ጎትቶ በማውረድ መሬት ላይ ጥሏት በወደቀችበት በያዘው ስለት ጀርባዋን እና ትከሻዋን ደጋግሞ በመውጋት የግድያ ሙከራ በማድረስ ወንጀል፤

በተጨማሪም በታኅሣሥ 14 ቀን 2014 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 9፡30 ከላይ በተጠቀሰው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ የ15 ዓመት የሆነችው ልጁ ከት/ቤት ስትመለስ አርፍደሻል በሚል ምክንያት በመጥረጊያ እንጨት እና በመጋረጃ መስቀያ ብረት ደጋግሞ በመምታት እጇ፣ ጭንቅላቷ እና እግሯ እንዲያብጥ በማድረግ እንዲሁም በነሐሴ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት አካባቢም ይህች የ15 ዓመት የሆነችው ልጁ ያለምንም ምክንያት በኤሌክትሪክ ገመድ ጀርባዋ እና እግሮቿን ደጋግሞ በመምታት ጀርባዋ እና እግሮቿ እንዲቆስሉና እንዲያብጡ በማድረግ ከተሰወረ በኋላ በክትትል ተይዞ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶበት በፍትህ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በወ/ሕ/አ በ27/1/ እና 539/1/ሀ/ እንዲሁም በወ/ሕ/አ 556/2/ሀ እና /ሐ/ ላይ በተደነገገው መሠረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ የሰው ግድያና ከባድ ውንብድና ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቦበት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል፡፡

### ውሳኔ

በክርክሩ ሂደትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ ያሰማ ቢሆንም በዐቃቤ ሕግ የቀረበውን ክስ መከላከል ባለመቻሉ ምክንያት ፍርድ ቤቱ በተከሳሽ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠት በ11 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

መዝናኛ

## ማረፊያ/ ትዝብት

# መለስ ቀለስ !

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

እግሬ እስኪንቀጠቀጥ ሰልፍ ይዤ የተሳፈርኩበት ታክሲ ውስጥ ነኝ። እስካሁን ድንጋጤው አለቀቀኝም። ከደቂቃዎች በፊት እስከ አናቱ ድንጋይ የቆለለ አንድ ሲኖትራክ እንደዋዛ እየታከከን ማለፉን እያስታወስኩ ነው። አሽከርካሪው ምን እንደነካው ባላውቅም አሁንም ፍጥነቱን አልቀነሰም። ይሮጣል፣ ይከንፋል…

ቀዥቃዣው ሾፌር ባገኘው ቀዳዳ ሁሉ ሾልኮ ለማለፍ ከመኪኖች ይጋፋል። የእኔን ያህል ባይሆንም አብዛኛው ተሳፋሪ ሊደርስ በነበረው አደጋ ሲጮህና ሲንጫጫ ነበር። አሁን ሁሉም በድንጋጤ ዝም ያለ ይመስላል። ግዜው ገና ጠዋት ቢሆንም መንገዱ መዘጋጋት ጀምሯል። ይህን ስመለከት እንዲያ ሲሮጥ የነበረው ሾፌር ውል አለኝና በመስታወቱ አሻግሬ ፊቱን ለማየት ሞከርኩ። ከወንበሩ እንዳለ ከወዲያ ወዲህ ይቁነጠነጣል። በረጅም ሰልፍ የተዘጋውን መንገድ ደጋግሜ ቃኘሁት። ፈጽሞ ጫፉ አይታይም።

አሁን በጠዋት የተነሳሁበት ጥብቅ ጉዳይ ከንቱ መቅረቱ ነው።ተስፋ ቆረጥኩ። «ዶሮ ርቃ ላትሄድ ማልዳ ትነሳለች » ይሉት አባባል ትዝ አለኝ። በረጅሙ ተነፈስኩና «እንግዲህ ምንም ማድረግ አይቻልም» አልኩ። ደግነቱ ይህን ያልኩት በልቤ ነው።

ከፊትና ከኋላ መደርደር የጀመሩት መኪኖች ወዴትም መውጣትና ማምለጥ የእነሱ ምርኮኞች ከሆንን አንድ ሰዓት ሊሞላ ነው። አሁንም ንቅንቅ የሚል ነገር አይታይም።ይህ ቀዥቃዣ ሾፌር በጠዋቱ እያቅለበለበ ያጣደፈን ለዚህ ኖሯል። ምን ዋጋ አለው ወይ ይዞን አላመለጠ ወይ አላሳፍራችሁም ብሎ አልከለከለን ይኸው ጉድ ሠርቶናል።

አብዛኛው የታክሲ ተሳፋሪ በያለበት አሸልቧል። እኔም አልዋሸም ጥቂትም ቢሆን ተኝቻለሁ። ብንን ስል ግን አንዳች ለውጥ አልነበረም። መኪኖቹም ተሳፋሪዎቹም በቦታቸው እንዳሉ ነው። ሁሉም ነገር ስልችት ይላል። ደግነቱ ዓይን አያርፍም፡ ከወዲያ ወዲህ መለስ ቀለስ እያለ ብዙ ይታዘባል። የእኔም ዓይኖች ከዚህ አላለፉም።አሻግረው ይቃኙና ተመልሰው ቦታቸው ይደርሳሉ።

አሁን ዓይኖቼ ርቀው ተሻግረዋል። አንዳች ነገር ላይ በማተኮሬ እነሱም ዒላማቸውን አልሳቱም።ከመንገዱ ባሻገር ሁለት ሰዎች ይታዩኛል። ሁለቱም በልመና ዓለም ስለመኖራቸው ነጋሪ አያሻም። አንደኛው በዕድሜ የገፉ ሽማግሌ ናቸው። ሌላው ደግሞ ከጎልማሳነት ያልደረሰ ወጠምሻ ይሉት አይነት ጎረምሳ ነው።ሰዎቹ ቁጭ ካሉበት ስፍራ ታላቅ ቁምነገር የያዙ ይመስላል።

ሁኔታቸው እየማረከኝ ነው።አሁን የታክሲውን ጉዳይ፣ የመንገዱን መዘጋጋት ዘንግቼ ትኩረቴን በእነሱ ጥያለሁ። ሽማግሌው የለበሱትን ብርድ ልብስ መሳይ ፎጣ ገለጥ ከማድረጋቸው ወጣቱ በእጁ የታሰረውን ረብጣ አስተካክሎ ከእጃቸው ላይ አኖረው።

ዓይኔን ማመን እያቀተው ቢሆንም ግርምታዬ አልተቋጨም። አሁንም በጥቁር ፌስታል ቢጤ የተጠቀለለ አንዳች ነገር ወደኪሳቸው ሲደርስ አስተዋልኩ። ሽማግሌው ጥቂት ገልመጥ ብለው ቃኙና የተቀበሉትን እስር ከኪሳቸው ከተው ፎጣቸውን ደረቡበት። ወዲያው በቀስታ ርምጃ አስፓልቱን ተሻግረው እኛ ወዳለንበት አቅጣጫ አማተሩ። የፈራሁት አልቀረም። በሚያሳዝን ገጽታ እጃቸውን ለልመና ዘረጉ። በጣም ደነገጥኩ።

ከደቂቃዎች በፊት በዓይኔ ያረጋገጥኩት የታሰረ ገንዘብ ኪሳቸው መቀመጡን ነበር። ሰውዬውን እንደእኔ አስተውሎ ያላያቸው ማንም ሰው አይጨክንባቸውም። ሽምግልናቸው፣ የቆሸሸ ልብሳቸውና አሳዛኙ ገጽታቸው እጅን ለምፅዋት ያዘረጋል። ደግነቱ እኔ ያለሁበትን ታክሲ ዘለው ወደሚቀጥለው መኪና አልፈው ሄዱ። ኧረ! እንኳንም አልመጡብን።በጣም ታዘብኳቸው። በጣም!

አሁንም የመኪናችን ልብ እየመታ ነው። ሾፌሩ መነጫነጩን ትቶ በዝምታ ተኮፍሷል። ገና ጠዋት ቢሆንም የታክሲው ውስጥ ወበቅ ግሎ ያነደን ይዟል። «ወይ አንዳንድ ቀን በቃ ካሰቡበት አያውልም» ጮክ ያለ ድምፅ ከውስጤ ሲያልፍ ተሰማኝ። አሁንም ግን ያወራሁት ከራሴ ጋር ነበር ።

ከታክሲው ወጣ ብዬ መለስ ከማለቴ ዓይኖቼ ጎኔ ካለች አንዲት ሴት ጋር ተላተሙ።ለአፍንጫዬ ደመቅ ያለ የለውዝ ሽታ ሲደርስ ቢቆይም እስካሁን እሷ እየበላች መሆኑን ልብ አላልኩም። ሴትየዋ ለውዙን ስታኝክ በእልህ ይመስላል።ሁኔታዋ ሥርዓት የለሽ ቢሆንብኝ ዞር ብዬ አስተዋልኳት።

እሷ እቴ ማንም ቢያይ ቢያፈጥባት ደንታ ያላት አይመስልም። ከእጇ ያለውን ለውዝ እየፈለፈለች ታላምጠዋለች፣ ብቻ ሳይሆን ታመነዥጋለች ማለት ያስደፍራል። ምንአልባት የቁርስ ሰዓት ደርሶባት ሊሆን ይችላል ብዬ ከራሴ ጋር ቀለድኩ። ሁኔታዋን በዋዛ መለፍ አልተቻለኝም። እንደምንም ብዬ ገጽታዋን ለማየት ሞከርኩ።

ባለ ለውዟ ሴት ጥርሶቿ ከከናፍሯ ወጣ ብለው የሚታዩ ናቸው። በተለይ ከፊት ጥርሶቿ የላይኞቹ የታችኛውን ከንፈሯን ረግጠው የያዙ በመሆናቸው ገጽታዋን ቀይረውታል። በዛ ላይ ያለፋታ የምታደቀው ለውዝ ከከናፍሯ ደጃፍ ተዝረክርኮ ይታያል። ይህን አስተውሎ ለሚያይ ማንም ሰው ሁኔታዋ ያናድዳል። የሆነውን ሁሉ ባስተዋልኩ ግዜ እህል ያልሻረው ሆዴ ተገላበጠብኝ ።

ደግነቱ መስኮት ጥግ መሆኔ በጀኝ። በሙቀቱ አሳብቤ አየር ወደውስጥ አስገባሁ። ትርክርኳ ሴት አሁንም ለውዟን ማድቀቁን ቀጥላለች። እስቲ አሁን ምን አግብቶኝ ነው እሷ ላይ ማፍጠጤ? ራሴን እየታዘብኩ ዓይኖቼን አነሳሁና ወደውጭ ማማተር ጀመርኩ።

መኪናችን እምብዛም እየሄደ አለመሆኑ ዙሪያ ገባውን ለመቃኘት አይቸግርም። ከውስጥ ሀሳቤ መለስ ብዬ ወደ ውጭ ቀለስ እያልኩ ነው። የገባሁበት ታክሲ ካሰብንበት ደርሶ እግሬ መቼ መሬት እንደሚነካ አላወቅም። ዓይኖቼ ግን ሥራ አልፈቱም። መለስ ቀለስ እያሉ መታዘባቸውን ቀጥለዋል።

አሁን ከፊት ከኋላ ያሉት መኪኖች እንደምንም ወደፊት እየተሳቡ ነው። እንዲያም ሆኖ አካሄዳቸው የልብ አያደርስም። በእኔ በኩል የዕለቱ ጉዳዬ እንደታሰበው ባይሆንም ለመመለስ አላሰብኩም። የሌሎችን ግን አላውቅም። እንግዲህ ሁኔታዎች እንደሚሆኑ ይሆናሉ። ምርጫ የለም።ይህን እያሰብኩ ዓይኖቼን መልሼ አሻገርኩኝ።

በርቀት ሁለት ፖሊሶች አጥብቀው የያዙት አንድ ወጣት ላይ ትኩረቴ አረፈ። ከሁለቱ ፖሊሶች አንደኛው ጎረምሳውን እንደ ቅሪላ ይነርተዋል። ተደብዳቢው ደግሞ ምት ያረፈበት አይመስልም። ጥቂት እንደመለማመጥ ይልና የሚሰጠውን ዱላ በአክብሮት ይቀበላል። ሁኔታው ያናደደው የሚመስለው ፖሊስ እጁን ማሳረፍ የፈለገ አይመስልም። እየደጋገመ ባለ በሌለ ኃይሉ ይነርተዋል።

እኔ ከልቤ ተናደድኩ። ወጣቱ ግን አሁንም ምንም የተሰማው አይመስልም። መቺውም ተመቺውም በዙሪያው ከከበቧቸው እግረኞች ጋር ቀስ እያሉ ወደ እኛ አቅጣጫ ቀረቡን። የታክሲው ተሳፋሪ ጉዳዩን ለማወቅ ጆሮና ዓይኑን ወደውጭ ጣለ።ድንገት አንዲት ቃል ሸው ብላ ለጆሮዬ ደረሰች፡ ፡«ሌባ ነው፣ሌባ ነው» የሚል ድምፅ ተደጋግሞ ተሰማኝ።

በርቀት ሸሽግ ብለው የቆሙ ወጣቶችን ዓይኖቼ አነጣጠሯቸው።። «በአዩኝ አላዩኝ» ስጋት ጥግ ይዘው ሁኔታውን በሞባይላቸው ይቀርፃሉ። ፖሊሶቹና ወጣቱ ተያይዘው ባጠገባችን እያለፉ ነው። ወዲያው በአዕምሮዬ ሁኔታው ሁሉ በማኅበራዊ ሚዲያ ሲለቀቅ ታየኝና በድንጋጤ አፌን ያዝኩ።

የመንገዱ መዘጋጋት ብዙ ነገሮችን መለስ ቀለስ ብዬ እንድታዘብ አድርጎኛል። አብዛኞቹ ያየኋቸው አስገራሚም አሳዛኝም ናቸው። በነበረው ግዜ ሁሉን ታዝቤ ዓይኖቼን ወደውስጥ ስመልስ ደግሞ ከታክሲው ጣራ ዝቅ ብሎ ይህን አባባል እንዲህ አነበብኩ «ዛሬ ቀኔ ብሩህ ነው » ይላል።

ጥቅሱን ቃል በቃል እየደጋገምኩ ራሴን ጠየኩት። በማለዳ መነሳቴን፣ አሰብኩና የታክሲውን መንቀዥቀዥ ሊያደርስ የነበረውን አደጋ አስታወስኩ። የሁለቱን ሰዎች የገንዘብ ልውውጥ ትዝ ብሎኝ እጃቸው ለልመና መዘርጋቱን ታዘብኩ። የሴትዬዋ ለውዝ አበላል ውል ብሎኝ ሁኔታውን በጎ ባልሆነ ዕይታ ገመገምኩ። የፖሊሶቹ ዱላና የልጁ ሁኔታ ትዝ ብሎኝ የወጣቶቹ የቪዲዮ ቀረጻ ከህሳብ እንደጣለኝ አስታወስኩ።

አሁን ደግሞ የመኪናው ላይ ጥቅስ ከዚህ ሁሉ እይታ በኋላ ቀኔ ብሩህ ነው ብዬ ራሴን እንዳሳምን እየነገረኝ ነው።እኔ ከነዚህ ሁሉ አጋጣሚዎች በኋላ ቀኔን ብሩህ ነበር ለማለት አልተቻለኝም። ለምን ካሉ አሁንም ከታክሲው አልወረድኩም። ደቂቃዎች እየቆጠርኩ መለስ ቀለስ እያልኩ ነው። መቼ ደርሼ እንደምወርድ እንጃ ። የሌላውን እንጃ እኔ ግን አሁንም ቀኔ ብሩህ ለመሆኑ እርግጠኛ አልሆንኩም።

## ዓለም አቀፍ

### በኬንያ በደረሰ የሄሊኮፕተር አደጋ የአገሪቱ ኤታማዦር ሹም እና ሌሎች መኮንኖች ሞቱ

የኬንያ ጦር አዛዥ ጄኔራል ፍራንሲስ ኦሞንዲ ኦጎላ በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍል ይበሩበት የነበረው ወታደራዊ ሄሊኮፕተር ተከስክሶ ሕይወታቸው ማለፉን ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ አስታወቁ። ኦጎላ ከሌሎች 11 ወታደራዊ መኮንኖች ጋር ሆነው በሄሊኮፕተሩ ሲጓዙ ነው አደጋው የደረሰው። ከአደጋው የተረፉት ሁለት ሰዎች ብቻ ናቸው።

ፕሬዚዳንት ዊሊያም ሩቶ ሐሙስ ምሽት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አደጋው ለሀገሪቱ "ትልቅ ኀዘን" ነው ብለዋል። ፕሬዚዳንቱ ቀደም ብለው የሀገሪቱ የፀጥታ ምክር ቤት አባላቶቻቸውን ለአስቸኳይ ስብሰባ ጠርተው ነበር። አደጋው የደረሰው ሐሙስ ሚያዝያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም. ከቀኑ 8፡20 ላይ መሆኑን ሩቶ ተናግረዋል። የኬንያ አየር ኃይል የአደጋውን መንስኤ ለማጣራት የምርመራ ቡድን አሰማርቷል።

ሄሊኮፕተሯ ከተነሳች ከደቂቃዎች በኋላ የተከሰከሰችው ከዋና ከተማዋ ናይሮቢ በስተሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ 400 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ኤልጌዮ ማራክዌት መሆኑን ፕሬዚዳንት ሩቶ ተናግረዋል። የአየር ኃይል አዛዥ እና የመከላከያ ሠራዊት ምክትል አዛዥ ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩት ጀነራል ኦጎላ ከአንድ ዓመት በፊት ነበር የጦር አዛዥ ሆነው የተሾሙት።

ሩቶ ዋና የጦር አማካሪያቸውን በግዳጅ ላይ እያሉ ሕይወታቸው ማለፉን ገልጸዋል። "እናት ሀገራችን ከጄኔራሎቿ መካከል አንዱ የሆነውን ጀግናዋን አጥታለች" ሲሉ ዊሊያም ሩቶ ለሀገራቸው ሕዝብ ተናግረዋል። በኬንያ ከትናንት ዓርብ ጀምሮ ሦስት የብሔራዊ ሐዘን ቀናት የታወጀ ሲሆን፣ የሀገሪቱ ሰንደቅ ዓላማም ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ ይደረጋል።



ጄኔራል ኦጎላ ለመጀመሪያ ጊዜ የኬንያ መከላከያ ሠራዊትን የተቀላቀሉት ሚያዝያ 1976 (እአአ) እንደነበር የኬንያ መከላከያ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ዘግቧል። ሥራቸውን የጀመሩት በሀገሪቱ አየር ኃይል ውስጥ ሲሆን፣ ከአሜሪካ አየር ኃይል ጋር በተዋጊ አውሮፕላን አብራሪነት ሠልጥነዋል። የአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር ሙሳ ፋኪ ማሃማት "አሳዛኙን የሄሊኮፕተር አደጋ ተከትሎ ለኬንያ ፕሬዚዳንት፣ መንግሥት እና ሕዝብ" ኀዘናቸውን ገልጸዋል።

ከአደጋው የተረፉት ሁለት ግለሰቦች በአስጊ ሁኔታ ላይ መሆናቸው እና ሕክምና እየተከታተሉ እንደሆነ ተገልጿል። የጦር መኮንኖቹ ተደጋጋሚ ጥቃት የሚደርስበትን ሰሜን ኬንያን ጎብኝተው ሲመለሱ ነው አደጋው የደረሰባቸው። በሽፍቶች ጥቃቶችን ምክንያት የተዘጉ አንዳንድ ትምህርት ቤቶችን ለማስከፈት ተልዕኮ ላይ ነበሩም ተብሏል። አካባቢውን ለማረጋጋት የተሰማሩ የጦር መኮንኖችንም መጎብኘታቸው ተገልጿል።

እአአ ሰኔ 2021 በዋና ከተማዋ ናይሮቢ አቅራቢያ ሊያርፍ የነበረ ሄሊኮፕተር ተከስክሶ ቢያንስ 10 ወታደሮች መሞታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

### በቦኮሃራም የታገተችው ናይጄሪያዊት ተማሪ ከ10 ዓመት በኋላ ሦስት ልጆችን ወልዳ ነፃ ወጣች

ከአስር ዓመት በፊት በቦኮሃራም ታጣቂዎች ታግተው ከነበሩ ሴቶች መካከል አንዷ የሦስት ልጆች እናት ሆና በናይጄሪያ መንግሥት ወታደሮች ነፃ ወጣች። በአውሮፓውያኑ ሚያዝያ 2014 ቦርኖ ከምትባለው ከተማ የቦኮሃራም ታጣቂዎች 276 ተማሪ ሴቶችን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤታቸው አፍነው መውሰዳቸው ይታወሳል።

እነዚህ የቺቦክ ትምህርት ቤት ሴት ልጆች መታገት መላው ዓለምን አስደንግጦ በወቅቱ የአሜሪካ ቀዳማዊ እመቤት የነበሩትን ሚሼል ኦባማን ጨምሮ ዓለም አቀፍ የማስለቀቅ ዘመቻ እንዲጀመር ምክንያት ሆኖ ነበር። ታፍነው ተወስደው ከነበሩት 280 ከሚጠጉት ልጃገረዶች መካከል እስካሁን ድረስ 100 የሚሆኑት በታጣቂዎቹ ቁጥጥር ስር ናቸው ወይም የደረሱበት አልታወቀም።

ሐሙስ ዕለት ደግሞ የናይጄሪያ ሠራዊት ከአስር ዓመት በፊት ከታፈኑት ተማሪዎች መካከል አንዷን ከሦስት ልጆቿ ጋር ከታጣቂዎቹ ነፃ ማውጣቷን አስታውቋል። ታጋቿ ሦስት ልጆቿ በተጨማሪም የአምስት ወራት ነፍሰ ጡር መሆኗን ሠራዊቱ ገልጿል። በቦኮሃራም ቡድን ታፍነው ከተወሰዱ ሴት ተማሪዎች መካከል እስካሁን ከ180 በላይ የሚሆኑት በሰሜን ምሥራቅ ናይጄሪያ ውስጥ ከምትገኘው ቦርኖ ግዛት የቡድኑ መደበቂያ ሳምቢሳ ጫካ በፀጥታ ኃይሎች ነፃ ወጥተዋል ወይም ከቡድኑ አምልጠዋል።

እስካሁን ከቡድኑ ነፃ ከወጡ ልጃገረዶች መካከል አንዳንዶቹ ወደ ቤተሰቦቻቸው ሲመለሱ ማርገዛቸው ወይም ልጅ መውለዳቸው ተዘግቧል። የቦኮሃራም ታጣቂዎች ጠልፈው የሚወስዷቸውን ተማሪዎች በወሲብ ባርነት ስር ያቆዮዋቸዋል የሚሉ ዘገባዎች በተደጋጋሚ ሲወጡ መቆየታቸው ይታወሳል።

ወደ ቤታቸው ከተመለሱት መካከልም የተወሰኑት የናይጄሪያ ባለሥልጣናት የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ እና ድጋፍ እንዳላደረጉላቸው በመግለጽ መንግሥትን ይተቻሉ። በናይጄሪያ ውስጥ አሁንም የጅምላ አፈና ተማሪዎችን እና ወላጆችን የሚያሳስብ ጉዳይ ሆኖ ቀጥሏል። የተለያዩ ወሮበላ ቡድኖች ተማሪዎችን ዒላማ በማድረግ ጠልፈው እየወሰዱ ማስለቀቂያ እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው የተለመደ ነው።

በሴቭ ዘ ችልድረን በጎ አድራጎት ድርጅት መረጃ መሠረት ከአውሮፓውያኑ 2014 እስከ 2022 ድረስ በናይጄሪያ ውስጥ ከአንድ ሺህ 680 በላይ ተማሪዎች ታግተዋል። ባለፈው መጋቢት ወር ከናይጄሪያዋ ሰሜን ምዕራብ ግዛት ካዱና ትምህርት ቤት ከ130 በላይ ተማሪዎች በታጣቂዎች ተጠልፈው የተወሰዱ ሲሆን፣ ይህም በቅርብ ዓመታት ውስጥ የተፈጸመ ከፍተኛው ጠለፋ ነው መባሉን የቢቢሲ ዘገባ አመልክቷል።



ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# በእምነት እንጂ በፍርሃት አትኑሩ!

**አስናቀ ፀጋዬ**



በዚህ ዓለም ዋጋ ሳንከፍል የምናገኘው ምንም ነገር የለም። ሁሉም ነገር የራሱ የሆነ ዋጋ አለው። ልክ እንደምንፈልገው ነገር ማለት ነው። ታዲያ ዋጋው ምንድን ነው? ብዙ አይነት ነገር ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በመጀመሪያ በማሰብም ሆነ በስሜት ደረጃ ያሰብነውን ነገር እንደምንሆን ማወቅ አለብን። በሌላ አባባል መድረስ የምንፈልግበትን ቦታ ማወቅና እዛ ቦታ ላይ መድረስ ከፈለግን በቅድሚያ ሃሳቦቻችንን ልንቆጣጠር ይገባል።

የዘራነውን ነው የምናጭደው። አእምሯችሁ ውስጥ የተቀመጡና ወደኋላ የሚጎትቷችሁን ነገሮች ቆራርጣችሁ አስወጧቸው። ምክንያቱም አእምሯችሁ የተፈጠረው እናንተን ወደላይ ከፍ ለማድረግና ያለምንም ገደብ እንድታስቡ ነው።

ነገር ግን እናንተ አእምሯችሁ ያለገደብ እንዳያስብ ገድባችሁታል። አእምሯችሁ ውስጥ ገብተው ሁሉንም ነገር የሚገድቡባችሁ ነገሮች ከየት ነው የመጡት? ካላችሁ ከራሳችሁ ነው እንጂ ከሌላ ከየትም አይደለም። ይህ ማለት እናንተ ፊት የተቀመጡ እድሎች በጣም ብዙና ከምታስቡትና ከምታምኑት በላይ ናቸው።

ከጠባብ አስተሳሰብና ከጭፍን ጥላቻም የራቁ ናቸው። በችግሮቻችሁ ላይ ቀና አመለካከትና አስተሳሰብ እንዲኖራችሁ ራሳችሁን ማስገደድ ወይም ምንም ያህል በችግር ብትከበቡ አዎንታዊ ነገሮችን እንድታስቡ ራሳችሁን ደፋር ማድረግ ይኖርባችኋል። ትላልቅና ልታሳኳቸው የምትፈልጓቸውን ግቦች ቁጭ ብላችሁ አንድ በአንድ መጻፍና የምትፈልጉትን ነገር በሚገባ ልታውቁ ይገባል።

አእምሯችሁ እስከጥግ ድረስ ሄዶ የፈለገውን ነገር እንዲያስብ ፍቀዱለት። ለአእምሯችሁ ነፃነት ልትሰጡት ይገባል። በሃሳባችሁም የትም ቦታ ልትደርሱ ትችላላችሁ። ያ ነው ነፃነት ማለት። ልታሳኳቸው ያሰባችኋቸውን ነገሮች ከሚከለክሏችሁ ነገሮች ዞር ትላላችሁ። እንዲህ አይነቱ ሃሳብ በአእምሯችሁ ከመጣባችሁ አእምሯችሁን ሃሳብ ውስጥ ታስገቡትና ሃሳቡን ከአእምሯችሁ ወዲያውኑ ማውጣት ትችላላችሁ። ማንኛውንም ነገር በሃሳብ ውስጥ ሆናችሁ ልታዩ ትችላላችሁ። ማሰብ ምስሉን መመለከት ማለት ነው።

ከምታገኙት ገቢ ላይ ቢያንስ 10 በመቶ ያህሉን መቆጠብ ይኖርባችኋል። የተሰማራችሁበት የሥራ መስክ ምንም ይሁን ምን እናንተ ካሰባችሁና ካመናችሁ ልታዩት ያልቻላችሁትን ትልቅ እድል ትመለከታላችሁ። ለማደግ ሁሌም ቦታና እድል አለ። ይህ ግን የሚሆነው ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ከሆናችሁ ብቻ ነው።

ምንም አይነት ጥሩ ሃሳብ ቢኖራችሁም ተግባር ከሌላችሁ ባዶ ነው። ህይወት ቀያሪ ናቸው ያላችኋቸው ሃሳቦች ዋጋ ቢስ ይሆናሉ። የሰው ልጅ ሁሉ ሁለት ነገር ሲባሉበት ይሰማል። አንደኛው በጣም አጥብቀን የምንፈልገውን ነገር እናውቃለን። ሁለተኛው ነገር ደግሞ አጥብቀን የምንፈራውን ነገር ይኖራል። ስለዚህ አንድ ትንሽዬ ወረቀት አውጡና ከምንም ነገር በላይ በጣም የሚያስፈልጋችሁን ነገር ፃፉ። የገንዘብ ችግር ላይ ከሆናችሁ ምናልባት ለእናንተ ቀዳሚው ነገር ገንዘብ ሊሆን ይችላል። ህይወታችሁንም ማሻሻል ከፈለጋችሁ ገቢያችሁን ማሳደግ አእምሯችሁ ይሆናል።

ምንም ችግር የለውም። ተጨማሪ ገቢ እፈልጋለሁ ትላላችሁ። ነገር ግን በቁጥር ይህን ያህል ነው የምፈልገው ብላችሁ ያችን ቁጥር ለይታችሁ ማወቅ አለባችሁ። መኖሪያ ቤት ከሆነ ፍላጎታችሁና ራሳችሁ የገዛችሁት ቤት ውስጥ መኖር ከሆነ ቤቱ ምን አይነት እንደሆነ በአእምሯችሁ ሳሉት፤ እወቁት። በስራ ቦታም ስኬትን እየፈለጋችሁ ሊሆን ይችላል። በህይወቴ እዚህ ደረጃ ላይ እደርሳለሁ እያላችሁ ካሰባችሁ እሱም ይሳካል።

እንደማንኛውም ሰው ደስተኛና በፍቅር የተሞላ ቤተሰብ እፈልጋለሁ ካላችሁ ያም የእናንተ ፍላጎት ነውና እውን ይሆናል። ብቻ በህይወታችሁ ማሳካት የምትፈልጓቸው ነገሮች በዛች ትንሽዬ ወረቀት ላይ ያስፍሩ። የምትፈልጉትን ነገር በደንብ አድርጋችሁ እሳካወቃችሁ ድረስ ማንኛውንም ነገር የማሳካት እድላችሁ ከፍ እያለ ይሄዳል። ስለዚህ የምትፈልጉትን ነገር በደንብ አድርጋችሁ ለዩ፤ግለፁ።

ለጊዜው አንድ ግብ ነው የሚያስፈልጋችሁ። ምክንያቱም መጀመሪያ ይህ ግብ እንደሚሰራና እንደማይሰራ ትሞክሩታላችሁ። በመቀጠል ደግሞ የምትፈልጉትን ሌሎች ግቦች እየጨመራችሁ ትሄዳላችሁ።

እምነታችሁ እየጠነከረ እንዲመጣ መጀመሪያ በቀላል ነገር ጀምሩ። ይህ ሲባል ግባችሁን ትቀንሳላችሁ ማለት አይደለም። ምንም ያህል ግባችሁ ትልቅ ቢሆን አንድ ቢሆን ግን ይመረጣል። የፃፋችሁትንም ግብ በወረቀት ላይ አስፍራችሁ በየቀኑ ብዙ ጊዜ እያነሳችሁ ታነቡታላችሁ።

በጠዋት ስትነሱም ስለፃፋችሁት ግብ ማሰብ በቂ ነው። የፃፋችሁትን ግብ ዘወትር ጠዋት ታነቡታላችሁ። በመቀጠል ደስ በሚል ስሜት ውስጥ ሆናችሁ ፃፋችሁት ነገሩን በደንብ ማብሰልሰል ትጀምራላችሁ። ይህ ለራሳችሁ አእምሮ ምልክት ነው። የምትሮጡበት ነገር አላችሁ ማለት ነው። በህይወት ደግሞ የሚያስፈልገን የምንሮጥለትና ልንቆምለት ሚገባ አላማ ያስፈልገናል። ያንን አላማ ካገኛችሁ ወዲያውኑ ከአልጋችሁ መነሳታችሁ አይቀርም። ምክንያቱም ስራችሁ ያ እንደሆነ ታውቃላችሁ። ልባችሁም ወደዛ ይሆናል።

በቀናችሁ ውስጥ ሰአት ካገኛችሁ አላማችሁን የፃፋችሁበትን ወረቀት አንስታችሁ አንብቡ። የፃፋችሁትን ግብ ባነበባችሁ ቁጥር የሰው ልጅ የሚያስበውን እንደሚሆን እወቁ። ይህ ህግ ነው። እናንተም ቁጭ ብላችሁ ግባችሁን ባነበባችሁ ቁጥር ትዝ የሚላችሁ ግባችሁ ነው። ግባችሁ ላይም እንደምትደርሱ ታውቁታላችሁ። ውስጣችሁም በደንብ ያምናል። እውነት ከተባለ በፃፋችሁት ሰአት ላይ እናንተ እዛ ቦታ ላይ ናችሁ።

አላያችሁትም እንጂ መሆን የምትፈልጉትን ሰው እሆናለው ብላችሁ የወሰናችሁ ሰአት ላይ ያንን ሰው ሆናችኋል። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ሁሉም ነገር እያበበና ፍሬ እያፈራ ይመጣል። ስለዚህ ግባችሁን ፃፉት። ከፃፋችሁት በኋላ ስለግባችሁ በደንብ አድርጋችሁ አስቡ። ዞር ዞር ብላችሁ ህይወታችሁን ተመልከቱ። ያንን ግብ እንዳሳካ ሰው ተውኑ።

ዛሬን እየኖራችሁ ትቀጥላላችሁ። አይናችሁ መትረፍረፍን እንጂ ሌላ ነገር እንዲመለከት አታድርጉ። ደስታን ከሆነ ደስታን ብቻ ልብ እንዲል አድርጉ። ልክ እንደማንኛውም ፍጡር እናንተም የምትልጉትን ነገር የማግኘት መብት አላችሁ። የእናንተ የመጀመሪያው ኃላፊነት መጠየቅ ነው። የምትፈልጉትን አውቃችሁ መጠየቅ።

በብዙ ሰዎች ዘንድ አስቸጋሪና ፈታኝ የሚሆነው አዲስ ልማድ መገንባት ነው። አዲስ ልማድ በቀላሉ ሊገነባ አይችልም። ብዙ ጊዜን ይጠይቃል። ነገር ግን እናንተ ያንን ልማድ አንዴ ከፈጠራችሁ በኋላ እድሜ ልካችሁን በዛ ልማድ ውስጥ ሆናችሁ ልትቀጥሉ ትችላላችሁ። ያ ልማድ ሊያሳርፍነም ይችላል፤ ሊያሰቃየንም ይችላል። ስለዚህ መፍራት አቁሙ! ፈሪ መሆንም የለባችሁም። የሆነ ነገር ይከሰታል ብላችሁ ስትፈሩ ወይም አሉታዊ ሃሳብ በአእምሯችሁ ላይ ሲመላለስ ወዲያውኑ ነው የአእምሯችሁን ምስል ማስተካከል እንዳለባችሁ አእምሯችሁ እያስጠነቀቃችሁ ነው።

አወንታዊ ምስል በአእምሯችሁ ውስጥ እያመላለሳችሁ ራሳችሁን ማየት የምትፈልጉበት ቦታ ላይ ተመልከቱ። አይናችሁን ምን ጊዜም ቢሆን ከግባችሁ ላይ እንዳትነቅሉ። እዛ ቦታ ላይ እንደደረሳችሁ አድርጋችሁ አስቡ። ይህ ሲባል ግን መንገዳችሁ ሁሉ ይለሰልሳል ማለት አይደለም። የራሳችሁን መንገድ ትታችሁ ሁሉም ሰው በሚሄድበት

**‹‹አወንታዊ ምስል በአእምሯችሁ ውስጥ እያመላለሳችሁ ራሳችሁን ማየት የምትፈልጉበት ቦታ ላይ ተመልከቱ፡፡ አይናችሁን ምን ጊዜም ቢሆን ከግባችሁ ላይ እንዳትነቅሉ፡፡ እዛ ቦታ ላይ እንደደረሳችሁ አድርጋችሁ አስቡ፡፡ ይህ ሲባል ግን መንገዳችሁ ሁሉ ይለሰልሳል ማለት አይደለም፡፡››**

የተለመደና ተራ በሚባል መንገድ መሄድ ትችላላችሁ። እንደዚህ አይነት ስሜቶችም ይመጡባችኋል። ተስፋ የመቁረጥ ወይም ሁሉንም ነገር እዚህ ጋር ርግፍ አድርጌ ልተው የሚል ሃሳብ ይመጣባችኋል። ይህ የተለመደ ነው። የሰው ልጅ ደግሞ ከአወንታዊ ይልቅ አሉታዊ ሃሳቦችን ማሰብ በጣም ይቀሉታል። ወይም በአሉታዊ ሃሳቦች የመሳብ እድሉ ከፍ ያለ ነው።

በዓለማችን በጣም ስኬታማ የሚባሉ ሰዎች 5 በመቶውን የዓለም ህዝብ ይሆናሉ። ሌላው ቀሪው 95 በመቶ የዓለም “ የሚሆነው የዓለም ህዝብ ተራ ወይም ደግሞ መካከለኛ ነው። ለዚህም ነው ራሳችሁን አወንታዊ ነገር ላይ እንድታስቡ ማስገደድ ያለባችሁ። ራሳችሁን እነዛ 5 በመቶ የሚሆኑ ስኬታማ ሰዎች ውስጥ ማግኘት አለባቸው። ይህን ለሰላሳ ቀን ሞክሯቸው። አእምሯችሁን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠሩት። እናንተ በምትፈልጉት ነገር ላይ ብቻ አእምሯችሁን እንዲያተኩርና ከቁጥጥራችሁ ውጪ እንዳይሆን አድርጉት።

ማድረግ ከሚጠበቅባችሁ በላይ በደንብ አድርጋችሁ ልትሰሩ ይገባል። ለሰላሳ ቀናት ከአቅማችሁ በላይ እንድትሰሩና እንድትለፉ ይጠበቃል። ይህን ስታደርጉ ግን አንድ ነገር መርሳት የለባችሁም። ቀና አመለካከት ሊኖራችሁ ይገባል። አእምሯችሁ ሁሌም አወንታዊ አመለካከት ሊኖረው ያስፈልጋል። እያማረራችሁና መስራት የማትፈልጉትን ስራ እየሰራችሁ መቀጠል አትችሉም።

እስከዛሬ አድርጋችሁ በማታውቁት ደረጃ በደንብ አድርጋችሁ ስሩ። ይህን ስታደርጉ ግን አንድ ነገር ልብ በሉ። ይኸውም የምታደርጉት ነገር እንዳለ ፍሬ እያፈራ መምጣቱ አይቀርም። ምክንያቱም በዚች ዓለም ላይ የልፋታችሁን ያህን እያገኛችሁ ትመጣላችሁ። ህግ ነው!

አንድ ግብ ስታችሁ እዚህ ነገር ላይ ጠንክሬ እሰራለሁ፣ እዚህ ነገር ላይ እለፋለሁ ብላችሁ ከወሰናችሁ እሆናለሁ ብላችሁ ያሰባችሁትን ሰው ሆናችኋል። ምክንያቱም የሚሄዱበትን ቦታ የማያውቁ በጣም ብዙ ሰዎች አሉ። ከነዚህ ሰዎች የተለያችሁ የምትሆኑበት ግባችሁን ማውጣታችሁና ወደዛ እየሄዳችሁ እንደሆነ መገንዘባችሁ ነው።

አሁን በዚህ መንገድ ላይ እያላችሁ የሆነ አንድ ወጥመድ ውስጥ ራሳችሁን ልትከቱ ትችላላችሁ። እሱም እንዴት ነው የማሳካው የሚለው ጥያቄ ነው። ትኩረታችሁን ሙሉ በሙሉ በዚህ ጥያቄ ላይ ማንሳት አለባችሁ። ምክንያቱም የእናንተ አስተዋፅኦ እዛ ጋር አይደለም። እንዴት የሚለውን የሚያመቻችላችሁ በየእምነታችሁ የምታምኑት ፈጣሪያችሁ ነው። ያን ለእርሱ ተውለት። ከእናንተ የሚጠበቀው ነገር ቢኖር የት መሄድ እንደምትፈልጉ ማወቃችሁ ነው። መንገዱን ፈጣሪያችሁ ያሳያችኋል።

በዚህ ዓለም ላይ የሚያስፈልገው አላማና እምነት ነው። ከዚያ የምትፈልጉትን ነገር ታገኛላችሁ። ነገር ግን ቢያንስ ለሰላሳ ቀናት በደንብ ስሩ። እስከዛሬ ሰርታችሁ በማታውቁት ደረጃ ምንም ነገር በምላሹ አገኛለሁ ብላችሁ ሳትጠብቁ የቻላችሁትን ያህል በደንብ አድርጋችሁ ልፉ። ምን አይነት የሚገርም ህይወት መኖር እንደምትጀምሩ ልብ እያላችሁ ትመጣላችሁ። ለሰላሳ ቀን ፅኑ መሆን አይከብዳችሁም።

ላላመናችሁበትና እምነታችሁን ላልጣላችሁበት ነገር በፍፁም ፅኑ ልትሆኑ አትችሉም። ስለዚህ ለአላማችሁ ፅናትና እምነት ሊኖራችሁ ይገባል።

በዚች ሰላሳ ቀናት ውስጥ ልትወድቁ ትችላላችሁ። የድሮ አመላችሁ ተነስቶ ቀደምት ልማዳችሁን ልተገብሩ ትችላላችሁ። ያኔ ቀናችሁን እንደገና ወደኋላ መልሳችሁ አንድ ብላችሁ መጀመር አለባችሁ። ይህን የምናደርገው ልማድ ለመፍጠር ነው። ምንም አይነት ልማድ ካላችሁ ደግሞ አዲስ የሆነ ልምድ ! የምንፈልገውን አዲሱን ልማድ የራሳችን ማድረግ ከፈለግን እዛ ነገር ላይ ፅኑና ወጥ ልንሆን ይገባል። ሁለቱን ነገሮች አንድ ላይ ካመጣን እምነትም አለን ማለት ነው። ልክ እንደተግባሮቻችሁ ሁሉ ፅፋችሁ የያዛችሁትን ግብ እንዳትረሱ።

ይህን ሁሉ እያደረጋችሁ ትርፍ ሰአት ሊኖራችሁ ይችላል። ባላችሁ ትርፍ ሰአት ለግባችሁ ገንቢ የሆኑ መጽሐፍቶችን አንብቡ። ከሁሉ በላይ ደግሞ ጭንቀትን አስወግዳችሁ ራሳችሁን ዘና ለማድረግ ሞክሩ። ፍራቻን አስወግዱ። በትናንሽ ነገር ዘና በሉ። በእምነት እንጂ በፍርሃት አትኑሩ!

# ርዕሰ አንቀፅ

## የንግድ ሥራ ዘርፎች ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት መሆናቸው ሀገራዊ ተጠቃሚነት ያጎለብታል!

መንግሥት ሁለንተናዊ ሀገራዊ እድገት ለማምጣት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፣ በዚህም እየተመዘገበ ያለው ስኬት እንደ ሀገር ካለንበት ፈተና አንጻር የብዙዎችን ቀልብ የሳበ ነው። ይህንንም በየወቅቱ የሚወጡ ዓለም አቀፍ መረጃዎች በተጨባጭ የሚያመላክቱት ነው።

ባለፉት አምስት ዓመታት ጦርነት እና ግጭቶች፣ አለመረጋጋት እና ዓለም አቀፍ ጫናዎች በበዙበት ሀገራዊ ዓውድ ውስጥ ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ችለናል፣ በዚህም እየፈተኑን ያሉ ችግሮች የበለጠ አቅም ገዝተው የከፋ አደጋ ውስጥ እንዳይከቱን መከላከል ችለናል።

ለዚህም ሲባል ወቅቱን የሚዋጁ የተለያዩ የፖሊሲ አማራጮችን ከመጠቀም ጀምሮ፣ የምንመኘውን ለውጥ በምንፈልገው ፍጥነት ማሳካት የሚያስችሉ የቀደሙ ሕጎችና መመሪያዎችን የማሻሻል ሥራዎች በስፋት ተሠርተዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ እየተመዘገቡ ያሉ ውጤቶች ተስፋ ሰጭ ናቸው ።

በለውጡ ማግስት ተግባራዊ የሆነው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ለዚህ በዋነኛነት ተጠቃሽ ነው። ይህንን ተከትሎም በተለይም ንግድና ኢንቨስትመንትን የተመለከቱ የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፎችን የማሻሻል ሥራዎች በስፋት ተከናውነዋል።

ከዚህ ውስጥ ሰሞኑን በተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ወደ ሥራ የገባው ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ ሆነው የቆዩት የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ዘርፎች ክፍት ያደረገው የኢንቨስትመንት ማሻሻያ ደንብ ተጠቃሽ ነው።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከትናንት በስቲያ በጋራ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በኢንቨስትመንት ደምብ 474/2012 ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ተከልለው የቆዩት የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላና የችርቻሮ የንግድ ሥራ ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆኑ ተደርጓል።

እንደሚታወቀው፣ መንግሥት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን ለማበረታታት ለረጅም ጊዜያት የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ዘርፎችን ከውጭ ኢንቨስትመንት ውድድር ተከልለው እንዲቆዩ የሚያስችለው ፖሊሲ ባለበት እንዲቆይ አድርጓል፡፡ ባለሀብቶች ፖሊሲው በሰጣቸው ዕድል ተጠቅመው ራሳቸውን እና ሀገራቸውን መጥቀም እንዲችሉ ሰፊ ርቀት ተጉዟል ።

በርግጥ፣ ፖሊሲው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በብዛት እና በጥራት ለማፍራት፤ ከዓለም-አቀፉ የንግድ ትስስር ሥርዓት ጋር ይበልጥ እንዲተዋወቁ ለማስቻል፤ በሂደትም እሴትን ወደሚጨምሩ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሸጋገሩ በማድረግ በሀገር ውስጥ አቅሞች ላይ የተመሠረተ ዘላቂ ሀገራዊ ኢኮኖሚ መገንባትን ታሳቢ ያደረገ ነበር ።

እንደ ሀገር በፖሊሲው አፈጻጸም የታየው ውጤት ግን፣ የሚጠበቀውን ዓላማ በሚፈለገው መጠን ማሳካት ያስቻለ አይደለም ፤ ከዚህ ይልቅ ከለላ የተሰጣቸው የንግድ ዘርፎች ሰፊ የአገልግሎት ተደራሽነት፣ የጥራት እና የብቃት ችግሮች የሚታይባቸው ፣ ለሕገ-ወጥ ድርጊት የተጋለጡበት ሁኔታ በስፋት ተስተውሏል ።

ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት የፖሊሲ እሳቤውን ማሻሻል አስፈልጓል። ዘርፎቹ ፍላጎትና አቅሙ ላላቸው የውጭ ባለሀብቶች ደረጃ በደረጃ እንዲከፈቱ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ አራቱ የንግድ ሥራ ዘርፎች ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት እንዲሆኑ ተደርጓል ።

የንግድ ሥራ ዘርፎች የውጭ ባለሀብቶች እንዲሳተፉ በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቶ በፀደቀው አዲስ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ቅድመ ሁኔታዎችን እስካሟሉ ድረስ የውጭ ባለሀብቶች በጥሬ ቡና፣ በቅባት እህሎች፣ ጫት፣ ጥራጥሬ፣ ቆዳና ሌጦ፣ የደን ውጤቶች፣ ዶሮና የቁም እንስሳት መላክ የወጪ ንግድ ላይ መሳተፍ እንደሚችሉም ተመልክቷል ።

በገቢ ንግድ ከማዳበሪያና ነዳጅ ንግድ በስተቀር የውጭ ባለሀብቶች በሁሉም የገቢ ንግድ ኢንቨስትመንት ላይ መሰማራት፣ በጅምላ ንግድ ከማዳበሪያ ጅምላ ንግድ በስተቀር መሳተፍ እንደሚችሉ ተወስኗል። በችርቻሮ ንግድ የውጭ ባለሀብቶች ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተከልለው በቆዩት በሁሉም የችርቻሮ ንግድ መሠማራት እንደሚችሉም ተገልጿል ።

ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መሆናቸው፤ ዘርፉን በውድድር እንዲመራ በማድረግ ሀገራዊ ተጠቃሚነትን በተሻለ መልኩ ማሳደግ የሚያስችል ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ በዘርፉ ያሉ እውቀቶችን፤ ክህሎቶችን እና ሥርዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እንደ መልካም አማራጭ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ሀገር ውስጥ አቅሞችን አሟጦ ለመጠቀም ከማስቻል ባለፈ፤ የሀገር ውስጥ ምርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆኑበትን መልካም አጋጣሚ በመፍጠር ሀገርና ሕዝብን ተጠቃሚ ማድረግ ያስችላል። ለጀመርነው ልማት ስኬትም ትልቅ አቅም እንደሚሆን ይታመናል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአራዶቹ ሰፈር ከስማቸው በላይ ገዝፈው ሲታዩ ነው

ሰብሥራት

ከተመሠረተች ከ135 ዓመታት በላይ የሆናት አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መናኸሪያ፤ የሀገሪቱ ዋና ከተማ የአፍሪካ መዲና፣ የተለያዩ አሕጉራዊ እና ዓለም አቀፉዊ ተቋማት፤ ከ90 በላይ ኤምባሲዎችን መገኛ በመሆን ሦስተኛ የዲፕሎማሲ ከተማ ነች። ከተማ እንደ ስሟ አዲስ ልትሆን ሀያ አራት ሰዓት እየተሠራ መሆኑን ስመለከት አንዳች የደስታ ስሜት ልቤን ይሞላዋል።

በከተማዋ መሐል ከተገነቡ ዘመናትን የተሻገሩት ቤቶች የሚያድሳቸው ጠፍቶ በእርጅና ምክንያት ጎብጠው፤ ግድግዳዎቻቸው ፈራርሶ፤ የጣራዎቻቸው ቀለም ወይቦ የከተማዋን ውበት አደብዝዘው ቆይተዋል፤ የነዋሪዎቿንም ሕይወት የማይመች አድርገውታል።

በእነዚህ የአረጁ ቤቶች ውስጥ በበጋም ሆነ በክረምት መኖር ስቃይ ነው። ቤቶቹ ከተማዋ ስትቆረቆር ጀምሮ የነበሩ በመሆናቸው የሚያፈርሳቸው ወይም የሚያድሳቸው አካል ቢያጡ አገልግሎት በቃኝ ያሉ ይመስል በራሳቸው እየፈረሱ እባካችሁ አንሱኝ ማለት ከጀመሩ በርካታ ዓመታትን አሳልፈዋል።

ባለ አንድ ክፍል የሆኑት አብዛኞቹ ቤቶች ሳሎንም መኝታም ምግብ ማብሰያም ሆነው ኖረዋል። ባስ ሲልም በአንድ ክፍል ውስጥ ደባል በመሆን ሁለት አባ ወራ የሚያስተናግዱ ቤቶችም አልታጡም። እናትና አባትን ልጆችም ሆኑ ሌሎች ተጨማሪ እንግዶች ይህችኑ አንድ ክፍል ይጋራሉ። ተጠጋግቶ መኖር ፍቅርን ያጠነክራል የሚል አባባል ቢኖርም አኗኗሩ አስተዳደግ ላይ የሚኖረው አሉታዊ የሥነ ልቦና ተፅዕኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

የቀደሙት ሰፈሮች ቤት በቤት ላይ ተደጋግፈው ችምም ብለው የተሠሩ፤ ከዘመኑ ጋር ያልዘመኑ፤ ከ135 ዓመታት በፊት ከነበሩበት ዲዛይናቸው ተቀይሮ ቤት ሲጠብ ሌላ ቤት ተቀጥሎበት፤ መፀዳጃ ቤትን ለሠላሳና ከዛ በላይ የሆኑ ሰዎች የሚጠቀሙባት ሻወር መውሰድ ቅንጦት የሆነበት፤ የቆረቆዘች የድህነት መገለጫ የሆኑ ሕዝቦች ከተማ መሆኗ ቀርቶ በውበቷ የምታማልል ሽቅርቅሪቱን አዲስ የምናየበት ቀን እሩቅ አይሆንም።

ቤቶቹ የአዲስ አበባን የኋሊት ጉዞ የሚያሳዩ፤ ከተማዋ ተመልካች አልባ ሆኗ ስለመኖሯ አመላካቾች፤ ጎዳና ተዳዳሪነት፤ ሴተኛ አዳሪነት፤ ማጅራት መቺነትና የመሳሰሉት ወንጀልና ነክ ድርጊቶች የሚፈጸምባቸው፤ የቁማር፤ የጫት፤ የሺሻ እና የአረቄ ቤቶች መገኛ፤ ወጣቶች በገዛ ፈቃዳቸው ለሱሰ ተገዥ የሆኑባት ከተማ፤ ቤቷን አድሷ ጓዳ ጎድጓዳዋን ሰታፀዳ የፀዳ ከተማ ከፀዳ አዕምሮ ጋር አይኖራትም ትላላችሁ?

እነ ዶሮ ማነቂያ፤ እሪ በከንቱና ውቤ በረሃን ያየ ከገናና ስማቸው ጀርባ የዋልጌዎች መናኸሪያ መሆናቸውን መረዳት አይከብድም። ፒያሳም ብትሆን ስሟ የደመቀ ያሸበረቀ ቢሆንም፤ የስሟን ያህል የፀዳች ሥርዓት ያላቸው ሕዝቦች መኖሪያ ልትሆን ያልቻለችበት ምክንያት ያው አሮጌ በመሆና የተነሳ ነው።

በእውነት የልጅነትና የወጣትነት ትዝታን በውስጣቸው የያዙ የካፌዎች፤ ኬክ ቤቶች፤ ሲኒማ ቤቶች መገኛም ቢሆንም ከዘመኑ ጋር የዘመኑ መሆን ግድ ይላልና እድሳቱ አይቀሬ ነው። አሮጌው በሙሉ በአይቀሬው እድሳት አዲስ ሆኖ በአዲስ ሊተካ ሥራው ተጧጡፏል።

ስማቸው ከገናኖች በላይ የገነኑት እነዚህ ሰፈሮች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በአንዲት ክፍል ውስጥ ቆጥና ምድር ሠርተው ፤ መፀዳጃ ቤት ተጋርተው፤ በአንዲት ክፍል አስር፤ አስራ አምስት ሆነው ተደራርበውና ተነባብረው የሚኖሩባቸው የድህነት ጥግ የሚታይባቸው ቦታዎች መሆናቸውንስ ማን ያምናል?

አካባቢዎቹ መሠረተ ልማት አርጅቶ አፍጅቶ አገልግሎት መስጠት ላቁም አላቁም ብሎ የሚወዛገብባቸው ናቸው። የአሌክትሪክ መስመር ዝርጋታው እጅግ ኋላ ቀር ከመሆኑ በላይ እጅግ የተወሳሰበና ለአደጋም የተጋለጠ ሲሆን ዝናብና የንፋስ ሽውታ ሲያገኘው በቀላሉ የሚበጠስ፤ በሰበብ አስባቡ ከአገልግሎት ውጪ የሚሆንበት ሰፈር ነው።

ቆሻሻ ልዩ ምልክቷ እስኪመስል ድረስ በየቦታው አፍንጫን የሚወጋ ሽታ ባለቤት የሆነችው ይች ከተማ ይህ ችግር እስከ ወዲያኛው ሊቀረፍላት ሽር ጉዱ ቀጥሏል። የውሃ ማስተለለፊያ መስመሮችና የቆሻሻ ማስወገጃ ቱቦዎች የተቀበሩበት ሁኔታ የጤና ችግርም የሚያስከትል ከመሆኑም ባሻገር አብዛኞቹ ውሃ መስመሮች ከቱቦዎች ውስጥ ወይም አጠገብ የተቀበሩ በመሆናቸው ከመፀዳጃ ቤት የሚወጣው ፍሳሽ ከሚጠጣው ውሃ ጋር እየተደባለቀ ለከፋ የጤና ችግር ሲዳርግ ቆይቷል።

**ቆሻሻ ልዩ ምልክቷ እስኪመስል ድረስ በየቦታው አፍንጫን የሚወጋ ሽታ ባለቤት የሆነችው ይች ከተማ ይህ ችግር እስከ ወዲያኛው ሊቀረፍላት ሽር ጉዱ ቀጥሏል**

ይህን ችግር ታሪክ ለማድረግም እየተሠራ ነው። በአንድ ጎን ፍሳሽ ማስወገጃው፤ በሌላ ገጽ የጎርፍ መውረጃው፤ የውሃና መብራት መስመሮች ሁሉም ውቢቱን አዲስ በሚመጥን ልክ እየተሠራ ነው። አዲስ እንደ ስሟ ልትታደስ አሮጌዎቹ የከተማዋ ሰፈሮች ስማቸውን የሚመጥን ዘመናዊነት ሊላበሱ ርብርብ እየተደረገ ነው። የአራዶቹ ሰፈር ከስማቸው በላይ ገዝፈው ሊታዩ ፤ ነበር እንዲህ ቅርብ ነው ወይ ! ሊያስብሉ ቀናትን በፍጥነት እየተጓዙ ነው።

ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ በመገናኛ ወደ ሲኤምሲ፣ ከቦሌ ተርሚናል ወደ ጎሮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ወሎ ሠፈር፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ኤምባሲ ወደ አራት ኪሎ የሚወስዱ ኮሪደሮችን የሚመለከተው ይህ የኮሪደር ልማት፤ እርጅና ያጎበጣት ከተማ ዝቅ ማለቷ ቀርቶ ቀና ብላ እንግዶቿን የምትቀበለው፤ በውበት አሸብርቃ የምትታየው ዕድል ፈጣሪ ነው ።

ማንም ሰው ከለመደው የመለየት ነገር እንደ ሞት ቢከብደውም ልማቱ ነገን የተሻለ ለማድረግ ነውና ኅብረተሰቡም ይህን ተረድቶ ተባባሪነቱን ቢያሳይ፤ የልማት ተነሽዎችን ጉዳይ የያዛችሁ የመንግሥት አካላትም ሁሉን ባማከለና ባገናዘበ መልኩ አገልግሎቱን በቅንነትና በፍጥነት በመስጠት ከተማይቱ ተውባ የምትታይበትን ቀን እናሳጥር እላለሁ። አዱ ገነትን ቤት ለአንቦሳ የምንልበት ቀን እንዲቀርብ እመኛለሁ። ቸር ይግጠመን።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፣ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፣ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፣ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፣ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፣ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፣ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ተስፋን ያዘለ ትከሻ ...

መልካምሥራአፈወርቅ

### ልጅነት ደጉ..

ደብረማርቆስ ጎዛምን አካባቢ ከምትገኝ አንዲት ቀበሌ ተወልዳ አድጋለች። ልጅነቷ እንደማንኛውም የገጠር ልጅ ነበር። ከእናት አባቷ ጉያ አልራቀችም። ወላጆቿ በስስት እያዩ እንደአቅማቸው ያሻትን ሁሉ ሞልተውላታል።

ትንሽዋ ትርንጎ ጫኔ ነፍስ ማወቅ ስትጀምር አካባቢዋን ልትርቅ ግድ ሆነ። ጎዛምን ለቃ ዓባይ በረሀን ስታቋርጥ ምክንያቷ የአዲስ አበባ ህይወት ነበር። በዚህ ከተማ አክስቷ ይኖራሉ። ከእናት አባቷ ስትለይ እሳቸው እንደ ልጅ ሊያሳድጓት ሊያስተምሯት ቃል ገብተዋል። ትርንጎ ይህን ካወቀች ጀምሮ በውስጧ ደስታ ሰፍኗል።ከዚህ በኋላ የአክስቷና የአዲስ አበባ ልጅ ትሆናለች።

### አዲስ አበባ...

አዲስ አበባና ትርንጎ ከተላመዱ ሰነባብተዋል። ይህ ቦታ ለእሷ ካደገችበት ቀዬ በብዙ ይለያል። እንዲያም ሆኖ እንግድነት አልያዛትም። ልጅ መሆኗ ሁሉን ለምዳ ከብዙዎች እንድትቀርብ አግዟታል። አሁን ትርንጎ የአክስቷ ልጅ ሆናለች። በቤቱ ካሉት ልጆች ብቸኛዋ ሴት ናትና ከሌሎች ልቃ መወደዷ አልቀረም። ይህ እውነት በቀላሉ ሰፈር ቀዬዋን አስረሳት፣ እንደልጅ እየታዘዘች፣እያገለገለች ኑሮን ቀጠለች።

ትርንጎ ጫኔ ትምህርት ቤት ገብታ ቀለም መቁጠር ስትጀምር ጉብዝናዋ ከተማሪዎች ሁሉ የላቀ ሆነ። ከእኩዮቿ በላይ የምታመጣው ውጤት በመምህራኖቿ የሚያስወድድ፣ የሚያስመሰግናት ነበር። ሁሌም የአስተማሪዎቿ አድናቆት ብርታት ጉልበቷ ነው። ‹‹አይዞሽ ባሏት ቁጥር ስለነገዋ ታልማለች። ዶክተር የመሆን ፍላጎቷ፣ ያይላል። ወገኖቿን የመርዳት፣ህይወትን የመታደግ ሀሳቧ ይበረታል።

አሁን ትርንጎ በትምህርቷ ገፍታለች። ዛሬም ቢሆን አብሯት የኖረው ምኞት አልራቃትም። አስረኛ ክፍል ስትደርስ ግን ባሰበችው አልተጓዘችም።አቅጣጫዋ ተለወጠ። ፍላጎቷን በውስጧ እንደያዘች በአካውንቲንግ ተምራ ተመረቀች። እንዲያም ሆኖ ሀኪም የመሆን ህልሟ አልከሰመም። አንድ ቀን ካሰበችው ደርሳ የልቧን እንደምትሞላ ታውቃለች። ትርንጎ በህክምናው መስከ ተምራ ካሰበችው ባትደርስም ለትምህርት ያላት ፍቅርና ብርታት ከማንነቷ አልጠፋም።

አሁን ትርንጎ ልጅነቷ አልፎ ወጣትነቷ አብቧል። ይህ ዕድሜ የሚያምሩበት፣ የሚዋቡበት ነው። አጋጣሚው ደግሞ ብዙዎችን ከብዙዎች ዓይን ይጥላል ። በዚህ ጊዜ በርካቶች ሁኔታቸው ይለያል ።ባህሪያቸው ይለወጣል። አርቀው ያሰቡ ርቀው ይራመዳሉ። ዕድሜ ፈተና የሆናቸው ደግሞ ከመንገድ ይሰናከላሉ።ይህ እውነት የብዙ ወጣቶች የህይወት ገጠመኝ ነው።

ትርንጎ በአንድ አጋጣሚ የወጣትነት ዕድሜዋ ከፍቅር አጋሯ አጣመራት።፡ ወጣቱ አይቶ ገምቶ፣ወዷታል። እሷም ብትሆን ከልብ ወዳዋለች። ቆይታቸው ከፍቅር አልፎ ከቁምነገር ደርሷል። ከአንድ ዓመት ቆይታ በኋላ ሁለቱም ትዳርን አሰቡ። አብሮ መኖርን ተመኙ። ይህ ይሆን ዘንድ የአሳደጊ አክስት ይሁንታ ግድ ይላል። ትርንጎ ወግና ደንቡን አልጣሰችም ። ፍቅረኛዋ ባህሉን ጠብቆ ፣ በሽማግሌ አስጠይቆ እንዲያገባት ፈቅዳለች። የታሰበው አልቀረም። አሳደጊ አክስቷ፣ የሀገር ቤት ቤተሰቦቿ አውቀውና መርቀው በሠርግ ተዳረች። ትርንጎ ወጣትነቷ ሳይፈትናት ለቁምነገር መብቃቷ አስደሰታት ።

### ሶስት ጉልቻ...

አሁን ልጅነት ይሉት የለም። የልብ ሀሳብ ለጎጆ ያደላል። የራስ ዕቅድ ለትዳር ይከፈላል።እንዲያም ሆኖ ትርንጎ ዓላማዋን አልሳተችም፣ ትምህርቷን በወጉ ቀጠለች፤ በአቅሟ እየሰራች ቤት ጓዳዋን መደጎም ያዘች። አሁንም አብሯት ያደገው ዶክተር የመሆን ምኞት ከውስጧ እንዲጠፋ አትሻም።

ባለቤቷ ፖሊስ ነው። ሙያው ከብዙዎች ያውለዋል። ከድካሙ የሚያርፈው ፣ ቤቱ ደርሶ ሚስቱን ሲያገኝ ነው። ትርንጎ በኑሮዋ ደስተኛ ነች።እየሰራች ትማራለችና ስለምንም አታስብም። ቶሎ ላለመውለድ በክንድ የሚቀበረውን የእርግዝና መከላከያ ትጠቀማለች። እንዲህ ማድረጓ ለትምህርት በማሰቧ፣ ለነገ ዓላማዋ በማቀዷ ነው።

ይህ እውነት ግን በብዙዎች አልተደገፈም።ትርንጎ ቶሎ ወልዳ ልጅ መሳም የፈለጉ ቤተሰቦቿ በጨቅጭቅ አላኖሯትም። ነጋ ጠባ ስለምን ብለው ሞገቷት።ለነፍስ አባት ነግረው አስወቀሷት። ትርንጎ በምትሰማው ሁሉ ተሳቀቀች።አሁን ለእሷ ሳይሆን ለእነሱ ፍላጎት ማደር ሊኖርባት ነው። በጉዳዩ ደጋግማ አሰበች።በክንዷ የተቀበረውን የእርግዝና መከላከያ ስታስወጣ


ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

በይሁንታ ለማርገዝ፣ ወስና ነበር።

እንዲህ ከሆነ ጊዜያት በኋላ ወዳጅ ዘመድ ሆዷን ማየት፣ እርምጃዋን መቁጠር ያዘ። አብዛኞች እንዳሰቡት አልሆነም። ያለምንም ለውጥ ወራት ተቆጠሩ። አለማርገዟን ያወቁ አንዳንዶች አሁንም በጥያቄ አዋከቧት። መልሱ ከእሷ ሳይሆን ከጊዜው ላይ ነበር። ጋብቻቸው አንድ ዓመት ደፍኖ ሶስት ወራት እንደተቆጠሩ ትርንጎ ነፍሰጡር መሆኗን አወቀች።

ይህ የምስራች ከእሷ አልፎ ለቤተሰቡ ደስታን አቀበለ። እርግዝናው እንደጀመረ ግን የትርንጎ ጤና መቃወስ ጀመረ። ሁኔታው የተለመደ ቢመስልም ለእሷ መቋቋም ተሳናት። በቀን ከአንዴ በላይ ሆስፒታል መመላለስ ልምዷ ሆነ።እንዳሻት ምግብ አለመውሰዷ አቅሟን ፈተነው። ስራና ትምህርቷን ትታ ከቤት ዋለች። ትርንጎ በየጊዜው ደሟን እየተለካች አልትራሳውንድ ትነሳለች። ሽንቷ እየተመረመረ፣ የልብ ምቷ ይታያል። ከህክምናው የቀረባት ምርመራ የለም። እንዲያም ሆኖ ጤና አይሰማትም። ሁኔታው እየከበደ ሲሄድ ገጠር ወላጆቿ ዘንድ ልትሄድ ወሰነች።

### ወደ ሀገር ቤት

አሁን ትርንጎ አዲስ አበባን ርቃ ትውልድ ቀዬዋ ገብታለች። የጀመረችውን የህክምና ክትትል ብትቀጥልም ጤና አላገኘችም። አዲስ አበባ ሳለች የታዘዘላትን መድኃኒት አቋርጣለች።ይህ የሆነው በአንዲት ሴት ምክር ነበር።ሴትየዋ በእጇ ያለውን እንክብል እያስተዋለች ሁለተኛ እንዳትወስደው ነግራታለች።

ትርንጎ በወቅቱ ለምን ማለቷ አልቀረም።ነጋሪዋ መድኃኒቱን የምትውጥ ከሆነ በልጇ ጭንቅላት ላይ ችግር እንደሚያስከትል እርግጠኛ ሆና አሳስባታለች። ይህን አምና የተቀበለችው ትርንጎ የሴትየዋን ቃል አክብራ የተሰጣትን መድኃኒት አርቃ ጥላለች። ቀድሞ የነበሯት ተጨማሪ ምርመራዎች እንደ ጅማሬያቸው አልቀጠሉም። አሁን ደግሞ መገኛዋ ‹‹ጎዛም›› ገጠሩ ላይ ሆኗል። ባመማት ቁጥር ጤና ጣቢያ እየሄደች ትታያለች። የእግሯ ማበጥ ፣ የውስጧ አለመመቸት የእርግዝናው የተለመደ ባህሪ መሆኑ ተነግሯታል።

ከቀናት በአንዱ ትርንጎ ድንገቴ ምጥ አጣደፋት። ፈጥኖ ከሀኪም ለመድረስ ጊዜ አልነበረም።እናቶች ተሰባስበው የ‹‹ማርያምን›› ስም እየጠሩ ሊያዋልዷት በር ዘጉ። ጥቂት ጊዜ ከቆየው ምጥ ለመገላገል ብዙ አልቆየችም። በአንድ ሰአት ውስጥ ሴት ልጅ ወልዳ ታቀፈች።

እንዲህ ከሆነ አፍታ በኋላ እንግዴው ልጅ ቦታውን እንዲለቅ ተጠበቀ። በታሰበው ጊዜ መውጣት አልቻለም። ትርንጎ አብዝታ ተጨነቀች፣ ስቃይዋ በረታ። ራሷንም ሳተች። ሁኔታው ያስደነገጣቸው አዋላጆች ሕፃኗን ከቤት ትተው እናትን ጤና ጣቢያ ለማድረስ ተጣደፉ። ሀኪሞች እጅ ስትደርስ ባለሙያዎቹ ህይወቷን ለማትረፍ ተሯሯጡ።ለመሞት ጥቂት የቀራት ወላድ እንደምንም ትንፋሽዋ ተመለሰ።

ቤተሰቦቿ የልጃቸውን ህይወት መትረፍ እንዳወቁ ጨቅላዋን ከነበረችበት አንስተው ወደ እናቷ ዕቅፍ አመጧት። ልጅቷ እንደተወለደ ህጻን የእናቷን ጡት አልፈለገችም።ያለ አንዳች እንቅስቃሴ በዝምታ ቆየች።ሁኔታዋን ያስተዋሉ ሀኪሞች ለተሻለ ህክምና በአምቡላንስ ወደ ደብረማርቆስ ሆስፒታል ላኳት።

ህጻኗ ማሞቂያ ክፍል ገብታ ቀናትን ቆጠረች። በጭንቀት ከልጇ ጎን የከረመችው እናት ጥቂት ጠብታ ትልቅ ተስፋ አገኘች። የህጻኗ ጤና ተመልሶ መንቃቷ ሲታወቅ ልጇን ከነርሶቹ እጅ ተረከበች። እፎታ ተሰማትና ጡቷን አውጥታ ሰጠቻት። ጨቅላዋ እንደፊቱ አልሆነችም። ትንሽዬ አፏን ከፍታ ከወተቱ ማገች ። እናት ደስ አላት። ፊቷ በስስ ፈገግታ ተሸፈነ።

### የእናት ዓይኖች...

ትርንጎ ብዙ ዋጋ የከፈለችባትን ልጇን እያጠባች አስተውላ አየቻት።ህጻኗ ክብደቷ ቀለለባት።ቅጥነቷ ከሌሎች ልጆች ተለይቶ ታያት።መላ ሰውነቷ እንደ ወረቀት የነጣ፣የገረጣ መሆኑን አወቀች።እናት ዝም እንዳለች ብዙ አሰበች።ለጊዜው እንዴት ለምን የሚሉት ጥያቄዎች አልተመለሱላትም።ከወለደች በኋላ ድካሟ ቀጥሏል፣ራሷን ስለሚያዞራት ብዙ አትራመድም። በወጉ ያልበረታው ጎኗ ህመም እያስተናገደ ነው።እንዲያም ሆኖ ስለ ልጇ ብዙ እያሰበች ትተክዛለች።

አሁን ትርንጎ ከወለደች ሁለተኛ ወሯ ነው። ከትናንቱ ዛሬ የተሻለ ቢሆንም ከአልጋ አልተነሳችም። ልጇን ታቅፋ ተኝታ ትውላለች። አንድ ቀን እናት እንደ ሁልጊዜው ህጻኗን አተኩራ አስተዋለቻት። ከፉኛ ስትደነግጥ አፍታ አልቆየችም ።ልጅቷ በሚገርም ፍጥነት ጭንቅላቷ እያደገ ፣ከፍታው እየጨመረ ነው።

የህፃኗን ጭንቅላት ደግማ ደጋግማ ዳሰሰችው። ከእኩዮቿ በተለየ ‹‹ትምቡክ›› የሚልና ለመንካት የሚያስፈራ ነው። ብትደነግጥም ዝም አላለችም።ለቤተሰቦቿ ፈጥና አሳየቻቸው። ሁሉም ጭቅላትዋን እያዩ ሀሳባቸውን ሰጡ። አጋጣሚው ከዘር ሊሆን እንደሚችል የገመቱ በረከቱ። ሁኔታው ግን በዚህ አልቆመም። ከምልክቱ በኋላ ህጻኗን ወደ ላይ ወደታች የሚላት ህመም ተባባሰ።ቤተሰቦቿ ከእናቲቱ ጋር ይዘዋት ጤና ጣቢያ ደረሱ።በወቅቱ ያገኟት ሀኪሞች ሁኔታው የተለመደ መሆኑን ነግረው መለሷት።

ትርንጎ የልጇን ክርስትና አጠናቃ የአራስነት ወጉን ጨርሳ ወደአዲስ አበባ ተመለሰች።ወደ ጎጇዋ ስትገባ ደስታዋ እንደ እናት ሙሉ አልሆነም፡፤በልጇ ላይ ያስተዋለችው ምልክት እረፍት እየነሳ አስጨነቃት። ለመጀመሪያው ክትባት ጤና ጣቢያ ስትሄድ በህጻኗ ጭንቅላት በጉልህ የሚታይ ደምስር ዓይን ይስብ ነበር።

በሀኪሞች እጅ የገባችው ህጻን አልጋ ይዛ ለመታከም አልዘገየችም።ለእናት ትርንጎ ያየችው ምልክት ህመም ስለመሆኑ የምታውቀው አልነበረም። ውሎ አድሮ ሙሉ መረጃው ተነገራት። የልጇ ህመም ‹‹የነርቭ ዘንግ ክፍተት›› ወይም ‹‹ሀይድሮሴፋለስ›› የተባለ የጭንቅላት ውስጥ ውሃ መቋጠር ስለመሆኑ አወቀች።

### ህክምናው...

ለከፍተኛ ህክምና ወደተለያዩ ሆስፒታሎች የተላከችው ህጻን አልጋ በያዘችበት አጋጣሚ የእሷን መሰል ችግር ያለባቸው ልጆች ጋር ልትሆን ግድ አለ።ይሄኔ ትርንጎ የልጇን ህመም ጠንቅቃ ለማወቅ አጋጣሚውን አገኘች። ህጻን ኤልዳና የመጀመሪያው የጭንቅላት ቀዶ ህክምና ሲደረግላት ገና የሶስት ወር ጨቅላ ነበረች።

እናት ትርንጎ ህጻኗን ለሀኪሞች አሳልፋ ስትሰጥ ከፈጣሪዋ ተማጽኖ ጋር ነበር። ልጇ ያገኘቻት በምክንያት መሆኑን ታውቃለች። ‹‹ትረፊ›› ካላት ከሀኪሟ እንዲያገናኛት ፣ መልሶም በዕቅፏ እንዲያውላት በመሪር ዕንባና ሀዘን እየተማለደች ነው። አራት ሰአታት የፈጀው የቀዶ ህክምና ሲጠናቀቅ ካልነቃችው ልጇ ጀርባ ታላቅ ተስፋን ጠበቀች።

ማግስቱን ኤልዳና በሚጠበቀው ለውጥ ላይ ተገኘች።ንቃቷና የዓይኗ ጥራት መልካም የሚባል ሆነ። ይህ እውነት በብቻኝነት ተኮራምታ ለምታስታምመው እናት ብሩህ ተስፋን አቀበለ። ትርንጎ ልጇ ከሆስፒታል ከወጣች በኋላ ስለህመሙ የሚያስረዳትን የፅሁፍ መረጃ ማንበብ ልምዷ ሆነ። አጋጣሚው በዚህ ህይወት ውስጥ ያሉ ልጆች ተጓዳኝ አካላዊ ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል አሳወቃት። እናት ይህን እያሰበች የልጇን ለውጥ ጠበቀች። ኤልዳና እንደእኩዮቿ አይደለችም። ግዜዋን ጠብቃ ለመዳህ፣‹‹ወፌ ቆመች›› ለመባል ተስፋ አይጣልባትም። ትርንጎ በልቧ ይህ እንዳይሆን ተመኘች።

ውሎ ሲያድር እናት በልጇ ቆሞ መሄድ ተስፋ ቆረጠች። የኤልዳና ችግር ጭንቅላቷ ብቻ አይደለም።ወገቧን ጨምሮ መላ አካሏ እንዳይንቀሳቀስ ተይዟል። የአንደኛ ዓመት ሻማዋን ስትለኩስ ህጻኗ ለመቆም ወንበር አልያዘችም፡ለመራመድ አልሞከረችም ።ከመሬት ሳትነሳ በሆዷ ለመሳብ እየታገለች ነው።

አመት አልፎ ሁለተኛው ሲተካ ኤልዳና ለውጥ አልታየባትም። የጭንቅላቷ ከፍታ እንዳለ ቢቆይም እግሮቿና ወገቧ አልተስማሙም። እናት ትርንጎ ሁሌም ቢሆን ልጇን ከሌሎች ጋር አታወዳድርም።ይህ እንዲሆን ታውቃለችና ራሷን በጽናት ታበረታለች።አንዳንዴ ልጇን ስታይ በሀሳብ ትርቃለች። ከአሁኑ የተሻለ ህክምና ፣እንደሚያሻት ይገባታል። መንቀሳቀሻ ዌልቸር እንደሚያስፈልጋት ታስባለች።የምኞቷን ለማሳካት አቅሙ የላትም ።እሷን አዝላና ታቅፋ ከመዋል የዘለለ ምርጫ አላገኘችም።እንደ እናት ልጇ በእግሯ ተራምዳላት እጇን ይዛት ብትሄድ ትወዳለች።

አሁን ኤልዳና ሶስት ዓመት ሆኗታል።በዚህ ዕድሜ ራሷን መቻል የምትጀምርበት ነው። ፍላጎቷን ማሳየት፣የወደደችውን መጠየቅ፣ የጠላችውን ማራቅ ይጠበቅባታል። በእሷ ህይወት ግን እነዚህ ጉዳዮች ሩቅ ናቸው። ሁሉም ጎዶሎዎች የሚሞሉት በእናቷ ትከሻና እጆች ብቻ ሆኗል።

ህጻን ኤልዳና እናቷ ከአጠገቧ እንድትርቅ አትፈልግም።አባቷን ስታይ ደግሞ ከልብ ደስ ይላታል። ልጅቷ በተፈጥሮዋ ንቁ የምትባል ነች።ዜማ እያወጣች ራሷን ታጫውታለች። ጥቂት ቃላቶችን ትሞክራለች። እናት አስባ ካላጎረሰቻት በቀር ራበኝ፣ጠማኝን አታወቅም። መሬት በተቀመጠች ጊዜ በልቧ ለመዳህ የምታሳየው ጥረት ልብ ይነካል።

### ንፍሮ ሻጪ ...

ትርንጎ ከልጇ ወዲያ ሌላ ጉዳይ የላትም። ዛሬ ተምሮ ዶክተር ስለመሆን፣የምታስብበት አይደለም።ወጣ ብላ ለመስራት የሚያስችል ዕድልና አጋጣሚ አልተቸራትም። ቀኑን ሙሉ ልጇን ስትንከባከብ ትውላለች። ከጥቂት ጊዜያት ወዲህ ግን ከቤት ወጣ ማለቷ አልቀረም። ይህ መሆኑ አእምሮዋን መልካም አድርጓል።

አሁን ትርንጎ በቀና ሰዎች እገዛ የባቄላ ንፍሮ እየሸጠች ነው።ከንፍሮው የሚገኘው ጥቂት ገቢ ቤት ጓዳዋን ይደጉማል። ቀድሞ ጨርቅ ሆኖ የምትቸገርበትን የዳይፐር ወጪ ይሸፍናል።ልጇን አዝላ ንፍሮ ስትሸጥ የሚያዩ በርካቶች ስለእሷ ልባቸው እንደተነካ ነው። ሁሌም ልጅነቷ ያሳዝናቸዋል።ልፋት ድካሟ ይሰማቸዋል።

አብዛኞቹ የተሻለ ስራ ሊያስገቧት ይጠይቋታል።እሷ ግን ይህን ታደርግ ዘንድ አይቻላትም።ልጇን ለሰራተኛ መስጠት ይከብዳታል።በህጻናት ማቆያ ለመስጠት ይፈትናታል።ትርንጎ አንዳንድ ሰዎች በጎ ያልሆነ እሳቤ እንዳላቸው አይጠፋትም። እሷን ግን አይዞሽ በርቺ የሚሏት ይበረክታሉ።በዚህ መልካምነት ደግሞ ሁሌም ትበረታለች።

### ያልደበዘዘ ተስፋ

ትርንጎ ስለልጇ ጤና የአቅሟን ሁሉ ትሞክራለች።በዚህ ጥረቷ የወንድማማቾች በተሰኘ ድርጅት ኤልዳና ፊዚዮ ቴራፒ እንድታገኝ አድርጋለች።ይህ ሙከራ ለእናት ትርንጎ ታላቅ ተስፋ ሆኖ ነገን በመልካም እንድታስብ ምክንያት ሆኗል።

እሷ አንድ ቀን ልጇ ቆማ እንደምትሄድ ታስባለች።እንዲህ የሚሆነው ግን የመልካም ሰዎች እጅ ሲታከልበት፣ ነው።ትርንጎ የልጇን ቆሞ መሄድ ስታልም ዓይኖቿ በትኩስ እንባ ይሞላሉ፡ የውስጧ ጥንካሬ ይፈተናል፣ ይሄኔ የእኩያ ልጆች ሩጫና ደስታ ወለል ብሎ ይታያታል።ለእሷ ልጇን እያሰበች ስሜቱን መቋቋም፣ከባድ ነው። ያባራ በማይመስል እንባ ፊቷ ይታጠባል።

የዛኔ የታዘዘላትን መድኃኒት እንዳትወስድ የመከረቻት ሴት፣. ገጠር ስትሄድ ያቋረጠችው ህክምና ተዳምሮ ለዛሬው ችግር ምክንያት እንደሆነ ታስባለች።ዛሬ ሁሉም ቢያልፍም ለማያልፍ ጸጸት ዳርጓታል።

የትርንጎ ህልም ይፈታ ዘንድ የለጋስ እጆች በረከት፣የቀና ልቦች መልካምነት የግድ ይላል። ዛሬ የዚህች ሴት ትከሻ ልጅን ብቻ አላዘለም።የነገ ተስፋንም ደርቧል። በህመም ባለች ጨቅላ ታስራ ነገን በተስፋ ለምትጠብቅ ወጣት እናት ‹‹አይዞሽ ባይነት›› የነገውን ዓለም ከህልም ያሳልፋል፣ ከምኞትም ያሻግራል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

# የኮሪደር ልማቱንም በግዙፍ ፕሮጀክቶች የግንባታ ፍጥነት

በኃይሉ አበራ

ከተሞች የአንድ ሀገር የእድገት ደረጃ የት እንደደረሰ በአጭር ጊዜ ጉብኝት ብቻ መግለጽ የሚቻልባቸው፣ የሀገሮች የእድገታቸው፣ የብልጽግናቸው፣ የኢኮኖሚያቸው መሻሻል፣ የፖለቲካቸው እሳቤ እድገታቸውና የማህበራዊ ስልጣኔያቸው መገለጫ ተደርገውም እንደሚወሰዱ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ የሚካሄደው የኮሪደር ልማትም ኢትዮጵያን የምትገልጽ ከተማ መገንባትን ያለመ ነው፡ ፡ የኮሪደር ልማቱ ከተማዋን እንደ ስሟ ውብና አዲስ ማድረግን፣ ከአፍሪካ ዋና ዋና ከተሞች ተርታ እንድትሰልፍ ማድረግን እንዲሁም ከተማዋ ባለፉት አመታት የገነባቻቸውን ግዙፍ መሰረተ ልማቶችን ማገናኘትም ያለመ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ እንደ ሀገር የነበረው የግንባታ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጥሩ አልነበረም፤ የግንባታ ፕሮጀክቶች በእጅጉ ሲጓተቱ ቆይተዋል፡፡ ይህን ተከትሎም የፕሮጀክቶች ሀብት ለመልካም አስተዳደር ችግሮች የመጋለጥ እድሉ ሰፊ ሆኖ ቆይቷል።

በሀገሪቱ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ግንባታ ግን እነዚህን ችግሮች ማስቀረት እየተቻለ ሲሆን፣ አሁን እየተካሄደ ያለው የኮሪደር ልማት ፍጥነትም የዚሁ ለውጥ ሌላው ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በፕሮጀክቶች አፈፃፀም አዲስና መልካም ባህል እየተገነባ ነውና። የዚህ ፕሮጀክት ግንባታም በፍጥነት እየተካሄደ ይገኛል፡፡

የኮሪደር ልማቱ አዲስ አበባ ከተማን ለኑሮ የተመቸች ማድረግን እንዲሁም አካባቢያዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፍ ተሞክሮን መሰረት ባደረገ መልኩ እየተሰራ ይገኛል። የከተማ አስተዳደሩም በመዲናዋ የተለያዩ አካባቢዎች የተሠሩ ግዙፍ መሰረተ ልማቶችን ለማገናኘት የሚያስችሉ አምስት የኮሪደር ልማቶችን በማስጠናት ወደ ኮሪደር ልማቱ ሥራ ገብቶ ልማቱን እያካሄደ ይገኛል። እነዚህ ስራዎች የመንገድ፣ የመብራት፣ የቴሌኮም እና የውሃና የፍሳሽ መሰረተ ልማቶችን ጨምሮ የሚከናወኑ ግንባታዎች ከተማዋን ለነዋሪዎች ምቹ ማድረግ የሚያስችሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ የከተማዋን እንግዶችና ጎብኚዎችንም ለማስናገድ ብቃት እንዲኖራቸው ተደርገው እየተገነቡ ናቸው።

የኮሪደር ልማቱን አላማ፣ በልማቱ የተካተቱ አካባቢዎችን፣ በልማቱ የሚከናወኑ ተግባሮችን፣ ልማቱ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ተከናውኖ የሚጠናቀቅ ስለመሆኑ በአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አበቤና በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በተደጋጋሚ ተብራርቷል፡፡ ፕሮጀክቱ በከተማ አስተዳደሩ የካቢኔ አባላት መሪነት እየተፈጸመ የሚገኝና በጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር የሚመራም ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የዲሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞገስ ባልቻ ባለፈው ሳምንት የኮሪደር ልማቱን እንቅስቃሴ አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንዳስረዱት፤ የመዲናዋ የኮሪደር ልማት ሥራ በአንድ ጀምበር የተጀመረ አይደለም፤ ከባለፈው 2015 ዓ.ም ግንቦት ወር አንስቶ በሀገር ውስጥ በሚገኙ አንጋፋ አጥኚዎች፣ አማካሪዎች እንዲሁም በከተማ አስተዳደሩ የሚመለከታቸው ተቋማት በቅንጅት ዝርዝር እቅድ ወጥቶለት ሲጠና የቆየ ነው።

ይሄን መሰል ሰፊ ሥራ ሲካሄድ ኅብረተሰቡንና የሚመለከታቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች እና ግለሰቦች የማወያየት ሥራ ተሰርቷል፤ ወደ ተለያዩ ጉዳዮች ገባ ብሎ በመመልከትም መረጃ ተወስዷል። ፕሮጀክቱ ሲጀመርም ምን ያህል ነዋሪዎችን እና መሰረተ ልማቶችን ሊነካ እንደሚችል፣ ምን ያህል ተጨማሪ ሀብት እና ጊዜ እንደሚፈልግ ጭምር በዝርዝር ተጠንቶ ያንን ታሳቢ ባደረገ መልኩ እየተሰራ መሆኑን አቶ ሞገስ አብራርተዋል።

የሚመለከታቸው ባለሙያዎች አስተያየት እንደሰጡበት፤ አመራሮች እና የተቋማት ኃላፊዎች እንደተሳተፉበት የገለጹት አቶ ሞገሰ፤ እነዚህ ጉዳዮች ሰብሰብ ብለው በከተማ አመራር ውይይት ተደርጎባቸው እና ህጋዊ አካሄድን ተከትሎ ወደ ሥራ እንደተገባም አስታውቀዋል፡፡


ፎቶ- ዳኜ አበራ

የኮሪደር ልማቱ ጉዳይ በዚህ መልኩ ሂደቱን እየጨረሰ መምጣቱን አብራርተው፤ ማህበረሰቡም በሂደቱ ውስጥ ያለፈና ዓላማውን እየተረዳ የመጣ መሆኑን ነው ያመለከቱት። ኅብረተሰቡ እስካሁን በከተማ አስተዳደሩ ተገንብተው ለአገልግሎት ከዋሉ ፕሮጀክቶች ግንዛቤ በመውሰድ የከተማ አስተዳደሩ ባቀረባቸው አዳዲስ የልማት ፍላጎቶች ላይ ተባባሪ መሆኑን እንዳረጋገጠም አስታውቀዋል።

የቅድመ ዝግጅት ሥራውም በአግባቡ የተሄደበት እና የኅብረተሰቡን መረዳት ታሳቢ ባደረገ መልኩ እረፍት አልባ በሆነ ሂደት የተሠራ መሆኑን አቶ ሞገስ ገልጸዋል፡ ፡ እነዚህን ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ መጨረስ ሌሎች ድህነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶች ላይ በማተኮር ለመስራት ጊዜ እንደሚሰጥም አስታውቀዋል፡፡ የልማቱ መፍጠን ድህነት ለማስወገድ ያለንን ቁርጠኝነት ያሳያል ሲሉም አቶ ሞገስ አመላክተዋል።

እንደ አቶ ሞገስ ማብራሪያ፤ የመዲናዋ ኮሪደር ልማት ሰፊ ሥራ የተካተተበት ከመሆኑ በስተቀር በከተማዋ ከለውጥ ጊዜ ጀምሮ በመስቀል አደባባይ፣ በአንድነት ፓርክ፣ በወዳጅነት ፓርክ፣ በእንጦጦ እንዲሁም በሌሎች ፕሮጀክቶች በርካታ ሰፋፊ ሥራዎች ተከናውነዋል። እነዚህ መሰረተ ልማቶች በለውጡ መንግሥት ቁርጠኛ አመራርነት የተሠሩ ናቸው። የለውጡ መንግሥት ቃል የገባውን የሚፈጽም ነው። የአሁኑ የኮሪደር ልማት ሰፋ ባለ መልኩ ማንቀሳቀስ ከመቻሉ ውጪ የመሰረተ ልማት ሥራው በከተማዋ ከለውጡ ወዲህ እረፍት በሌለው ሁኔታ ሲከናወን ቆይቷል።

መዲናዋን እንደ ስሟ የማስዋብ እና የማልማት ሥራው በተጠናከረ መልኩ ሲከናወን መቆየቱን ጠቅሰው፤ በካዛንቺስ፣ ቸርችል ጎዳና፣ ብሔራዊ በመንገዶች አስተዳደር አካባቢ፣ የተሰሩትን ሥራዎች በአብነት አንስተዋል፡፡ የአሁኑን የኮሪደር ልማት ሥራ ልዩ የሚያደርገው ሰፊ እና በርካታ አካባቢዎችን የሚዳስስ በመሆኑ ነው ብለዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የኮሪደር ልማቱ በአምስት አካባቢዎች ላይ እየተካሄደ ነው። በፒያሳ እና ዙሪያው፣ ከፒያሳ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ ቀበና፣ ከቀበና በኬንያ ኤምባሲ በጀርባ በኩል መገናኛ አደባባይ፣ ከቀበና በዋናው መንገድ ተከትሎ መገናኛ አደባባይ፣ ከቦሌ አደባባይ በመስቀል አደባባይ አልፎ እስከ አራት ኪሎ፣ ከቦሌ በኢምፔሪያል በኩል እስከ መገናኛ፣ ከመገናኛ ሲኤምሲ ባሉት አካባቢዎች የከተማ አስተዳደሩ በሰፊው የመሰረተ ልማት ግንባታውን እያካሄደ ይገኛል።

በሌሎች አካባቢዎች ላይ በቀጣይ የሚሰሩ የመሰረተ ልማት ሥራዎች ሲኖሩ ለኅብረተሰቡ የማሳወቅ ሥራ ይሰራል ያሉት አቶ ሞገስ፣ የእናንተ ኮሪደር ሊለማ ነው፤ ከዚህ ውጡ፤ ይሄንን ሸጡ እያሉ የሚያደናግሩ አካላት መኖራቸውንም ጠቁመዋል። የከተማ አስተዳደሩ ሌሎች የልማት ሥራዎችን በተመሳሳይ በጥናት ላይ ተመስርቶ እንደሚያከናውን አስታውቀዋል፡፡ ይህም ህብረተሰቡንና የሚመለከታቸውን አካላት በማወያየት እንጂ በስማ በለው እና በአደናጋሪዎች እንደማይሠራ አመልክተዋል። ኅብረተሰቡ በየደረጃው የሚገኙ የከተማ አስተዳደሮችን ማናገር እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል።

ስራውን ለማከናወን የሚያስችሉ የገንዘብ እና የማቴሪያል አቅርቦቶችም አብረው ተቀናጅተው ሥራው እየተመራ በመከናወን ላይ መሆኑንም ተናግረዋል። በርከት ያሉ ኮንትራክተሮች እና ማሽነሪዎች በፕሮጀክቱ እንዲንቀሳቀሱ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ የከተማ አስተዳደሩ የመንገዶች ባለሥልጣን ቡድን፣ በአንዳንዱ ላይ ደግሞ ሌሎች ኮንትራክተሮች መሰማራታቸውን አመልክተዋል፡፡

ሀገራችን ካለባት የድህነት ጫና በመነሳት እያንዳንዱ የመሰረተ ልማት ሥራ በፍጥነት እና በጥራት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ጠቅሰው፤ ቀደም ሲልም በዚህ ተግባቦት ላይ በመመስረት በርካታ የመሰረተ ልማት ሥራዎች ተከናውነዋል ብለዋል። ከዚህ በፊት 10 እና 15 ዓመት የሚወስዱ፣ አንዳንዶቹም ተጀምረው የማይከናወኑ ፕሮጀክቶች እንደነበሩ አስታውሰው፣ አሁን የፕሮጀክቶች ግንባታ በተያዘላቸው ጊዜ እየተፈጸመ የሚጠናቀቁበት ሁኔታ መፈጠሩን ገልጸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከዚህም ባጠረ ጊዜ የተጠናቀቁ፣ ለሀገር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ፣ የከተማዋን ገጽታ በትልቁ የቀየሩ ግዙፍ ፕሮጀክቶች እንዳሉም አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ አዲስ አበባ ከተቆረቆረች ጊዜ ጀምሮ ከ10 በላይ የተለያዩ ስትራክቸራል ፕላኖች በተለያየ ጊዜ ተዘጋጅተዋል። አብዛኞዎቹ ፕላኖች ግን ትውልዱን ታሳቢ ያደረጉ፣ ዘመኑን የዋጁ፣ የዓለምን የከተሞች እድገት እና ስልጣኔ መሰረት ያደረጉ አልነበሩም።

መዲናዋ ካላት ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተልዕኮና ኃላፊነት አኳያ ከስር ከስር እየተሰሩ እያደጉ ባለመምጣታቸው ዛሬ ላይ ላለው የከተማ አስተዳደር ውዝፍ የቤት ሥራ ጥለው አልፈዋል ሲሉም አመልክተዋል። ይህ በመሆኑም አዲስ አበባ የስም ብቻ በመሆን የማይታይ አበባ እና የማይታይ አዲስነት ይዛ ቆይታለች ያሉት አቶ ሞገስ፣ የደከሙ ቤቶችና መንገዶች፣ ያልተሟሉ መሰረተ ልማቶች፣ ለኅብረተሰቡ ምቹ ያልሆኑ መንደሮች የበዙባት፣ ነገር ግን በስም ተንቆጥቁጣ አዲስ አበባ ስንላት የቆየች ከተማ ናት ሲሉ አዲስ አበባን ገልጸዋታል።

ከአምስቱ የኮሪደር ልማት ሥራዎች መካከል አንዱ ከሜክሲኮ ሳር ቤት ወሎ ሰፈር ያለው የኮሪደር ልማት ነው። የዚህን ኮሪደር ልማት ሥራ የሚከታተሉት አቶ ሞገስ እንዳብራሩት፤ ከሜክሲኮ ሳር ቤት ወሎ ሰፈር ያለው የኮሪደር ልማት ከሜክሲኮ ሳር ቤት፣ ከሳር ቤት ጎተራ እና ከጎተራ ወሎ ሰፈር በሶስት ምዕራፍ ተከፍሎ እየተሰራ ነው።

በዚህም የመጀመሪያው ምዕራፍ ከሜክሲኮ ሳር ቤት ያለው የኮሪደር ልማት 70 በመቶ በላይ የሚሆነው ሥራ እየተጠናቀቀ መሆኑን በወቅቱ ገልጸዋል። በመንገድ አካፋዩ ላይ የነበሩ ዛፎችና መሰረተ ልማቶችን በማንሳት በዲዛይኑ መሰረት የሳር ልባስ ተደርጎለት የዛፍ ተከላ ሥራው እየተጠናቀቀ ይገኛል ያሉት አቶ ሞገስ፤ በግንባታው ምክንያት የተቆፈረው የአስፋልቱ መንገድ ተመልሶ የአስፋልት ሥራው ተጠናቋል።

እንደ አቶ ሞገስ ገለጻ፤ የዚህ ምዕራፍ አብዛኞዎቹ ሥራዎች እየተጠናቀቁ ናቸው። በ60 ቀናት ውስጥ ሥራውን ለማጠናቀቅ እየተሰራ ነው። ሥራው ለ24 ሰዓት እየተከናወነ በመሆኑ ባጠረ ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል። የጎንና ጎን የአፈር ሥራውና በውስጥ የሚገነቡት የመሰረተ ልማት ሥራዎች ተጠናቀው የእግረኛ ንጣፍ እየተሰራ ነው። ከዚህም ባለፈ የሳይክል መንገድ እየተሰራ ይገኛል።

ከሳር ቤት ጎተራ ያለው መንገድ ከተመረቀ ቅርብ ጊዜው ቢሆንም፣ በአረንጓዴ ቦታዎቹ እና በእግረኛ መንገዶቹ ላይ የዲዛይን ማሻሻያ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከቀድሞ ኮንትራክተር ጋር ውይይት ተደርጓል ያሉት አቶ ሞገስ፤ የዚህም የወሰን ማስከበር ሥራው የተጠናቀቀ በመሆኑ በቀሪዎቹ ጊዜያት የማሻሻያ ሥራው ሙሉ ለሙሉ እንዲጠናቀቅ ይደረጋል ብለዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ከጎተራ ወሎ ሰፈር ያለው የኮሪደር ልማት ትልልቅ ሕንፃዎች፣ ከፍተኛ ኃይል የሚያስተላልፉ የኤሌክትሪክ መስመሮች እንዲሁም የቴሌኮም ፋይበር መስመሮች እና የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ከታችና ከላይ ያሉበት በመሆኑ የልማት ሥራው በሚጠበቀው ፍጥነት ሊሄድ አልተቻለም። እነዚህን ጉዳዮች በጥንቃቄ በመመልከትም ሥራውን በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ እየተሰራ ነው፤ አሁን በመሬቱ ስር የሚያልፉ መስመሮችን የማስተካከል ሥራ፤ የእግረኛና የሳይክል መንገድ ንጣፍ እየተከናወነ ነው። ይህኛው ምዕራፍም ከሜክሲኮ ሳር ቤት ቀጥሎ ይጠናቀቃል ።

መንግሥት በኮሪደር ልማቱ የሚሰራቸው ሥራዎች ድህነት፣ ኋላቀርነት እና ውስብስብ የሆኑ ማህበራዊ ጫናዎችን የሚያቃልሉ ናቸው። የልማት ሥራዎቹም በፍጥነትና በጥራት ይከናወናሉ።

# ስፖርት



# የዳይመንድ ሊግ ውድድሮች ዛሬ ይጀምራሉ

**ዓለማየሁ ግዛው**

ባለፈው ዓመት መጨረሻ ላይ በአሜሪካዋ ዩጂን በኢትዮጵያዊቷ እንቁ አትሌት ጉዳፍ ፀጋይ የ5ሺ ሜትር የዓለም ክብረወሰን ደምቆ የተጠናቀቀው የዳይመንድ ሊግ ውድድር የ2024 የውድድር ዘመኑን ዛሬ አንድ ብሎ ይጀምራል። በዚህም መሠረት በ2024 በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልልቅ የመም እና የሜዳ ተግባራት የአንድ ቀን ውድድሮች ዛሬ በቻይና ዚመን መካሄድ ይጀምራሉ። ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም በሦስት የመድረኩ የተለያዩ ርቀቶች ለማሸነፍ ይሮጣሉ።

ውድድሩ ዛሬ በቻይናዋ ዚመን ከተማ መካሄድ የሚጀመር ሲሆን የዛሬ ሳምንት በሻንጋይ ቀጥሎ የሚካሄድ ይሆናል። ኢትዮጵያውያኑ ከሚጠበቁባቸው ርቀቶች አንዱ የሆነው የወንዶች 5ሺ ሜትር፣ አምስት አትሌቶች ፉክክሩን በድል ለመጀመር ከኬንያውያን ጋር የሚያደርጉት ትንቅንቅ ይጠበቃል።

ከነዚህም መካከል የለንደን እና የዶሃ የዓለም ሻምፒዮናዎች ባለድሉ አትሌት ሙክታር እድሪስ አንዱ ነው። አትሌቱ ርቀቱ 12፡54.3 በመሮጥ የግል ምርጥ ሰዓት ባለቤት መሆኑ ይታወሳል። ከእሱ የበለጣ ፈጣን ሰዓት ያላቸው የሀገሩ ልጅ ንብረት መላክ እና ኬንያዊው ኪፕኮር ኒኮላስ ብቻ ናቸው። ኬንያዊው አትሌት 12፡46.33 ፈጣን ሰዓት ያለው ሲሆን ንብረት ደግሞ 12፡54.22 በሆነ ሰዓት ይከተላል። ባላቸው ፈጣን የግል ሰዓት ምክንያት እነዚህ አትሌቶች ለአሸናፊነት ቅድሚያ ግምትን ይወስዳሉ። ይሁኔ አዲሱ፣ ለሜቻ ግርማ እና ግርማ ኩማ ሌሎች ጥሩ ሰዓት ያላቸው ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው።

የ1500 ሺ ሜትር ሴቶች ሌላው ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሚሳተፉበትና ለአሸናፊነት የሚጠበቁበት




**ጉዳፍ ፀጋይ የውድድር ዓመቱን የዳይመንድሊግ የመክፈቻ ውድድር በድል ለመጀመር ትሮጣለች፣**

ርቀት ሲሆን 9 ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ተፎካካሪ ይሆናሉ። ከነዚህም መካከል ስድስቱ አትሌቶች ርቀቱን ከ 4 ደቂቃ በታች ሮጠዋል። ድሪቤ ወልተጂ ርቀቱን 3፡53.93 በመሮጥ ቀዳሚ ስትሆን የ2023 ዩጂን ዳይመንድ ሊግ አሸናፊና የክብረወሰን ባለቤት ጉዳፍ ፀጋይ 3፡54.01 ሮጣለች። ብርቄ ኃየሎም፣ ፍሬወይኒ ኃይሉ፣ ወርቅነሽ መሰለ እና አክሱማይት አምባዬ ርቀቱን በጥሩ የግል ሰዓት ማጠናቀቅ የቻሉ ናቸው።

ኬንያዊቷ የርቀቱ ፈርጥ ፌዬዝ ኪፕየጎን በውድድሩ አለመሳተፏ የፉክክሩን ደረጃ በጥቂቱም ቢሆን ይቀንሳል ተብሎ ቢጠበቅም ኢትዮጵያውያኑ ኮከቦች ከሌሎች የርቀቱ አትሌቶች ጋር የሚያደርጉት ፉክክር አጓጊ ነው።

በዚህም የዓለም ሻምፒዮናዋ ጉዳፍ ፀጋይ፣ የማይል ውድድር ክብረወሰን ባለቤት ድርቤ ወልተጂ እና የዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮናዋ ፍሬወይኒ ኃይሉ የሚያደርጉት ፍልሚያ የዓለምን ቀልብ መሳብ ችሏል።

በ3 ሺ ሜትር መሰናክል ሴቶች በሚካሄደው ውድድር ሦስት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ይሳተፋሉ። በርቀቱ አትሌት ሲንቦ ዓለማየሁ፣ ፍሬሕይወት ገሰሰ እና ሎሚ ሙለታ ከሌሎች ሀገራት አትሌቶች ጋር ይፎካከራሉ።

ወጣቷ አትሌት ሲምቦ ዓለማየሁ በ2022 የዓለም ከ18 ዓመት በታች ውድድር 9፡18.98 ሰዓትን በመሮጥ ተይዞ የነበረውን ክብረወሰን አሻሽላለች። በዚህም መድረክ ከሁለት ዓመት በፊት ሮጣ 9፡21.10 መግባት ችላለች። በአምናው ውድድር ተሳትፋም 9፡05.83 በመሮጥ የራሷን ምርጥ የግል ሰዓት አስመዝግባለች።

እንደ ከዚህ ቀደሞቹ ዓመታት ሁሉ አትሌቶች በ14 ተከታታይ የዳይመንድ ሊግ መዳረሻ ከተሞች ነጥብ ለመሰብሰብ የሚፎካከሩ ሲሆን በእያንዳንዱ ርቀት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት አትሌቶች በውድድር ዘመኑ መጨረሻ ለዳይመንድ ሊግ የፍጻሜ ውድድር የሚፋለሙ ይሆናል። ቀጣዮቹ ውድድሮች በዶሃ፣ ራባት እና ዩጂን ከተደረጉ በኋላ፣ ተከታዮቹ ወደ ኦስሎ እና ስቶክሆልም በግንቦት መጨረሻ እና ሰኔ መጀመሪያ ላይ ተካሂደው ወደ አውሮፓ ትልልቅ ከተሞች ያቀናሉ።

በሐምሌ ወር በፓሪስ፣ ሞናኮ እና ለንደን የሚደረጉ ውድድሮች ለአትሌቶች ለፓሪስ 2024 ኦሊምፒክ እንዲዘጋጁ እድል ይሰጣቸዋል። ከኦሊምፒክ በኋላ እአአ ከመስከረም 13 እስከ 14 ባለው ጊዜ ውስጥ የውድድር ዘመኑ ከመጠናቀቁ በፊት በሉዛን፣ ሲሌሲያ፣ ሮም እና ዙሪች ነጥቦችን ለማግኘት አራት ተጨማሪ ውድድሮች ይካሄዳሉ። እ.ኤ.አ. ከ2019 በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የዳይመንድ ሊግ የፍፃሜ ውድድር ወደ ቤልጂየም ብራስልስ ሲመለስ፣ ከመስከረም 13-14 ባለው ቀን ውስጥ 32ቱ የዳይመንድ ሊግ ቻምፒዮኖች በመጨረሻው ሳምንት ውድድር የሚለዩ ይሆናል።

በውድድሩ 8 አትሌቶች እንደየደረጃቸው ነጥብ በመሰብሰብ ለዓመቱ መጨረሻ የፍጻሜ ውድድር ለማለፍ የሚያደርጉት እልህ አስጨራሽ ትግል አስደናቂ እንደሚሆን ይጠበቃል። አትሌቶች በሴቶችና ወንዶች በ16 የአትሌቲክስ ውድድሮች በማሸነፍ ለውድድሩ የተዘጋጀውን የዳይመንድ ዋንጫ እና 30 ሺ የአሜሪካን ዶላር ሽልማትን የግላቸው ለማድረግ ይፋለማሉ።

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም Abarra Kibruu Turaa የሠሌዳ ቁጥር OR-02-63878 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሠሌዳ ወድቆ ጠፋብኝ ብለው በ7/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት የመኪና ሠሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ካላቀረቡ ለአመልካች ሠሌዳ በምትክ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የአዳማ ከተማ ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

## አማራ ክልል

ከሳሽ ደ/ማ/ከ/ወተት/ል/ግብይት ተወካይ አቤቱ መሀሪ በተከሳሽ አቶ/ወ/ሮ/ሪት ጣሰው ህብስቱ መካከል ስላለው የገንዘብ ክርክር ጉዳይ አቶ/ወ/ሮ/ሪት ጣሰው ህብስቱ ይጠሩልኝ ስላሉ በህይወት ካሉ ለ21/08/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ 3፡30 ሰዓት ደ/ማ/ከ/ወ/ፍ/ቤት ድረስ እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን ክርክሩ በሌሉበት ቀጥሎ የሚወሰን መሆኑን ፍርድ ቤቱ አዟል።

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደብረ ማርቆስ ከተማ አስ/ወረዳ የፍታ/ዳ/አገ/አሰ/ዋና የሥራ ሂደት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ/ የፌ/ጠ/ዐ/ሕግ እና በተከሳሽ ብዙአየሁ ስጦታው አበረ መካከል ስላለው የወንጀል ክርክር ጉዳይ ክሱን ለመስማት ለ22/8/2016 ዓ.ም ስለተቀጠረ ተከሳሽ ብዙአየሁ ስጦታው አበረ በተጠቀሰው ቀነ ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ፌ/ከ/ፍ/ቤት ቃሊቲ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ ነገር ግን በተጠቀሰው ቀነ ቀጠሮ ካልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንደሚቀጥል ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቃሊቲ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ የፌ/ጠ/ዐ/ሕግ እና በተከሳሽ በእምነት ሰሙንጉስ ጌታነህ መካከል ስላለው የወንጀል ክርክር ጉዳይ ክሱን ለመስማት ለሚያዝያ 24 ቀን 2016 ዓ.ም ስለተቀጠረ ተከሳሽ 1. በእምነት ሰሙንጉስ ጌታነህ በተጠቀሰው ቀነ ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ፌ/ከ/ፍ/ቤት ቃሊቲ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ ነገር ግን በተጠቀሰው ቀነ ቀጠሮ ካልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንደሚቀጥል ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቃሊቲ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ወሰን ዳምጠው እምሩ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B15381 የተሽከርካሪው ዓይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H9M7P00724 ሞዴል NPR71L የሞተር ቁጥር 4HG1-0ET268 የሊብሬ ቁጥር 259134 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ8/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገለጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ልደታ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ፉአድ ጀማል ሻፊ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-98678 የተሽከርካሪው ዓይነት ማሽን የተገጠመበት ተሽከርካሪ የሻንሲ ቁጥር LZFF25R45JD009307 ሞዴል CQ5254GJBHTG414 የሞተር ቁጥር F2CE0681C*B05218H00217672 የሊብሬ ቁጥር 0207045/0257366/0235450 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ8/8/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገለጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

### የጨረታ ቁጥር DCE/BM/30/2024 እና DCE/SM/37/2024 መክፈቻ ቀን ማራዘሚያ እና ቦታ ማሳወቂያ ማስታወቂያ

የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ለጎፋ አፓርትመንት ፕሮጀክት ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ የTerrazzo Floor Tile, Window sill,Copping, Tread & Riser የ PPR & UPVC Pipes and Fittings አቅርቦት ግዥን አስመልክቶ በግልጽ ጨረታ ቁጥር DCE/BM/30/2024 እና DCE/SM/37/2024 ዓ.ም ጨረታ መውጣቱ እና የጨረታው መክፈቻ ቦታ በቀድሞ ወሎ ሰፈር የሚገኘው የዋና መ/ቤት ቢሮ መሆኑ መጠቀሱ ይታወሳል፡፡ ሆኖም ግን የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ዋና መ/ቤት አዲሱ ቢሮ ቃሊቲ ቶታል ስታዲየም ጀርባ ወይም ኮማንደር አትሌት ደራርቱ ቱሉ ት/ቤት አጠገብ የተዘዋወረ በመሆኑ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ በተስተካከለው የጨረታ መክፈቻ ቀንና ሰዓት መሠረት በኢንተርፕራይዙ የግዥና አቅርቦት አስተዳደር መምሪያ አዲሱ ቢሮ በመቅረብ ጨረታውን መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

| ተ.ቁ | የሥራ ዝርዝር | ፕሮጀክት | የጨረታ ቁጥር | የጨረታ መዝጊያ ቀን | የጨረታ መክፈቻ ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Terrazzo FloorTile, Window sill, Copping,Tread & Riser | ጎፋ አፓርትመንት | DCE/ BM/30/2024 | 18/08/2016 ከጠዋቱ 5፡00 | 18/08/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 5፡15 |
| 2 | PPR & UPVC Pipes and Fittings | ጎፋ አፓርትመንት | DCE/ SM/37/2024 | 30/08/2016 ከጠዋቱ 4፡45 | 30/08/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 5፡00 |

**አድራሻ፡-** የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ
የቀጥታ ስልክ ቁጥር 0911171751/0913297297 /ፖ.ሳ.ቁ 3414 ፋክስ
WWW.dce-et.com/Email:-info@dce-et.com
ቃሊቲ ቶታል ስታዲየም ጀርባ ወይም
ኮማንደር አትሌት ደራርቱ ቱሉ ት/ቤት አጠገብ

**የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ**